አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ
አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

መሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው [illegible]
በውጤቶቻቸው መካከል ያለው [illegible]

በ
አበበ ከበደ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የመሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለው ዝምድና

በ

አበበ ከበደ

ሰኔ 2003 ዓ.ም

# የመሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለው ዝምድና

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

አበበ ከበደ

ሰኔ, 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የመሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለው ዝምድና

በ

አበበ ከበደ

LIBRARY

## የፈተና ቦርድ አባላት

ዶ/ር ጌታቸው አዱኛ ____ 27/10/03
አማካሪ ፊርማ ቀን

ዶ/ር ጌታሁን አማሬ ____ 27/10/03
ፈታኝ ፊርማ ቀን

ሰኔ, 2003 ዓ.ም

# ምስጋና

ይህ ጥናት ከጅምሩ እስከ ፍፃሜው ድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ፣ ጽሁፌን በማረም፣ በማስተካከል በቅንነት የረዱኝ መምህሬና አማካሪዬ ዶ/ር ጌታቸው አዱኛ ልከፍለው የማልችለው ውለታ አለብኝ፣ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። እንዲሁም ለመምህሬና አማካሪዬ አቶ ግርማ ገብሬ ጽሁፌን በማረምና የማቴሪያል ድጋፍ በማድረግ ላደረጉልኝ ትብብር ከፍ ያለ ምስጋናን አቀርባለሁ።

የቤተሰቡን ኃላፊነት ብቻዋን ተሸክማ ለጥናቱ መሳካት ከጎኔ በመሆን ስታበረታታኝ የነበረችው ባለቤቴ ወ/ሮ አልማዝ ዘውዴ ውለታሽ ከሁሉም በላይ ነው፤ ምስጋናዬ ይድረስሽ። በሀሳብ የምትረዱኝ ልጆቼ ለቤዛዊትና አቤል ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ሁልጊዜ የምታበረታታኝ የእናትነት ፍቅሯ ወደር የሌለው እናቴ ወ/ሮ ሙሉነሽ፣ ለእህቶቼና ለወንድሞቼ በገንዘብ፣ በሀሳብ፣ በማቴሪያል ላደረጋችሁልኝ ድጋፍ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ የመሰናዶ ትምህርት ቤት ርእሳን መምህራን፣ ለመምህራና ተማሪዎች ላደረጋችሁልኝ ትብብር ሁሉ ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ላደረገልኝ እገዛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በመጨረሻም ጽሁፉን በማረም በኮምፒውተር በመጻፍ ከፍተኛ እገዛ ላደረገችልኝ እህቴ ወ/ት ዙሪያሽወርቅ ሙሉጌታ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

# ማውጫ

ገጽ

ምስጋና ..... i
ማውጫ ..... ii
የአባሪ ማውጫ ..... iv
የሠንጠረዥ ማውጫ ..... v
አጠቃሉ ..... vi

ምዕራፍ አንድ
መግቢያ
1.1. የጥናቱ ዳራ ..... 1
1.2. የጥናቱ ዓላማ ..... 6
1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ ..... 7
1.4. የጥናቱ ወሰን ..... 7
1.5. ሙዳዩ ቃላት ..... 8

ምዕራፍ ሁለት
2. ክለሳ ድርሳን ..... 10
2.1 የአመለካከት መሰረተ ሀሳብ ..... 10
2.1.1. የአመለካከት ምንነት ..... 10
2.1.2. የአመለካከት ባህርያት ..... 14
2.2. አመለካከትና የውጤት ዝምድና ..... 14
2.3. የአመለካከት ተጽዕኖዎችና መነሻቸው ..... 17
2.3.1. ወላጆች፣ እኩዮችና ሕብረተሰብ ..... 17
2.3.2. የመምህሩና የማስተማር ስነ ዘዴ ..... 18
2.3.3. የመማሪያ መጻህፍት ..... 21
2.4. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ..... 22
ምዕራፍ ሶስት
3. የጥናቱ ዘዴ

3.1. የናሙና አመራረጥ 25
3.1.1. የትምህርት ቤቶች አመራረጥ 26
3.1.2. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ 26
3.1.3. የመምህራን ናሙና አመራረጥ 27
3.2. መረጃ መሰብሰቢ መሳሪያዎች 29
3.2.1. መጠይቆች 29
3.2.1.1. የተማሪዎች መጠይቅ 29
3.2.1.2. የመምህራን ቃለ መጠይቅ 31
3.2.2. የክፍል ምልከታ 32
4. የመረጃ አተናተን ዘዴ 32
ምዕራፍ አራት
የመረጃዎች አቀራረብና ትንተና ውጤት 35
4.1. ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ የአመለካከት ውጤትና ትንተና 35
4.1.1. የመላሾች አጠቃላይ ሁኔታ 36
4.1.2. ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት 37
4.1.3. ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸው አመለካከት 51
4.1.4. ተማሪዎች ለመማሪያ መፅሐፉ ያላቸው አመለካከት 58
4.1.5. ተማሪዎች ወላጆቻቸውና ጓደኞቻቸው ስለ አማርኛ በሚሰጡት አስተያየቶች ላይ 63
5. ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት 65
6. የአመለካከትና የፈተና ውጤት ዝምድና 68
ምዕራፍ አምስት
ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች
5.1. ማጠቃለያ 70
5.2. የጥናቱ ግኝቶች 73
5.3. አስተያየት 74
ዋቢ መፃህፍት 77

## የአባሪ ማውጫ


ገጽ

አባሪ 1 ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ ..... 83

አባሪ 2 ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ ..... 84

አባሪ 3 የመምህራን ቃለ መጠይቆች የተጠቃለሉ መልሶች ..... 92

አባሪ 4ሀ. በየትምህርት ቤቶች የተደረጉ ዝርዝር የክፍል ምልከታ ውጤቶች ማጠቃያ አብይ ነጥቦች ..... 93

አባሪ 4ለ. የመምህራን የማስተማር ሂደት ክምልከታ የተገኘ ምላሽ ..... 94

አባሪ 5ሀ. የተማሪዎች አመለካከትና የፈተና ውጤታቸውን የሚያሳይ ስታስቲካዊ መረጃ ..... 95

አባሪ 5ለ. የተማሪዎች አመለካከትና የፈተና ውጤት ..... 96

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ገጽ


ሠንጠረዥ 1፡ በትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎችና ለናሙና የተመረጡ ተማሪዎች ..... 28

ሠንጠረዥ 2፡ በመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በቃለ-መጠይቅ የተሳተፉ የአስራ ሁለተኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን ..... 32

ሠንጠረዥ 3፡ የተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ ..... 36

ሠንጠረዥ 4ሀ፡ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ..... 37

ሠንጠረዥ 4ለ፡ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ..... 41

ሠንጠረዥ 4ሐ፡ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ..... 45

ሠንጠረዥ 5፡ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸው አመለካከት ..... 51

ሠንጠረዥ 6፡ ተማሪዎች ለመማሪያ መጽሐፉ ያላቸው አመለካከት ..... 58

ሠንጠረዥ 7፡ ተማሪዎቹ ወላጆችና ጓደኞቻቸው ስለ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመላካከት ..... 63

ሠንጠረዥ 8፡ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት ያላቸው አመለካከት ..... 65

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዓላማ በአዲስ አበባ አስተዳደር ስር በሚገኙ የመሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከፈተና ውጤታቸው ጋር ያለውን ዝምድና መመርመር ነው። በጉለሌና በአራዳ ክፍለ ከተማ የሚገኙ ሶስት የመሰናዶ ትምህርት ቤት አፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ የሆነ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች በጥናቱ ተካተዋል። እነዚህ ተማሪዎች የተመረጡት በእጣ ንሞና (Random Sampling) ነው። ጥናቱን ለማካሄድ የተከተልኩት ዘዴ ገላጭ ምርምርን ነው። የጥናቱን ተጨባጭነት የበለጠ ለማጉላት ለ120 ተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ተበትኖ መረጃ ተሰብስቧል። በመሰናዶ ትምርህት ቤት የሚያስተምሩ አስራ አንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር ቃለ መጠይቃዊ ውይይት ተደርጎ ጠቃሚ ሀሳቦች ተገኝተዋል። ከተማሪዎችና ከመምህራን የተገኙትን መረጃዎች የበለጠ ለማጠናከር የክፍል ምልከታ ተካሂዷል። የተማሪዎች አንደኛ ወሰነ ትምህርት ማጠቃለያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት ከየትምህርት ቤቶቹ የውጤት ዝርዝር (Mark-list) እንዲለቀሙ ተደርጎ መረጃዎች ተሰብስበዋል። ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ድርሳናትም ተካተዋል። ተማሪዎች በቀረበላቸው መጠይቅ መሰረት ለቋንቋውና ለትምህርቱ፣ ለመማሪያ መጽሐፉ አሉታዊ አመለካከት እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል። ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ ውጤት ደግሞ ለተማሪዎችና ለሙያቸው አዎንታዊ አመለካከት አሳይተዋል። የተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ውጤትና በአንደኛ ወሰነ ትምህርት ከተሰጡት የፈተና ውጤት አማካይ ጋር በተዛምዶ ስታስቲካዊ ቀመር ሲሰላ በተማሪዎች አመለካከት በፈተና ውጤታቸው መካከል ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ጥምረት ታይቷል። ስለዚህ በተማሪዎች አመለካከት በፈተና ውጤታቸው መካከል ዝምድና መኖሩን መረጃው አመልክቷል። ከዚህ በመነሳት ተማሪዎች በሚማሩት የቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት በፈተና ውጤታቸው ላይ ሊንፀባረቅ መቻሉን እንገነዘባለን። ስለሆነም መምህራንም ሆኑ የቋንቋ ማስተማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር የተስማማ የማስተማሪያ ዘዴ መጠቀም ተገቢ መሆኑን እንዲሁም የማስተማሪያ መጻህፍት ሲዘጋጁ ይዘት አመራረጥ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ እደሚያስፈልግ ለመጠቆም ተሞክሯል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ትምህርት ለአንድ አገር ዕድገት ሥልጣኔ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። የህብረተሰቡ አኗኗር እንዲለወጥ፣ ወጣቱ ትውልድ በስነ-ምግባር ታንጾ በአገር ፍቅር ስሜት ተኮትኩቶ ሥራ ወዳድና ተመራማሪ እንዲሆን ለማስቻል ትምህርት ጉልህ ሚና ይጫወታል። ተማሪዎች በስነ-ምግባር ታንጸው አምራችና ተመራማሪ ዜጋ ሆነው እንዲያድጉ ከተፈለገ በቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች አሉ።

የመማር ማስተማሩ ሂደት በተሳካ መልኩ እንዲካሄድ በቅድሚያ የተማሪዎችን ፍላጐት ማወቅ ያስፈልጋል። ተማሪዎች ምን ይወዳሉ? ለትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? ስነ ልቦናዊ ባህሪያቸውስ? የመሳሰሉትን ሁኔታዎች ሁሉ መዳሰስ ተገቢ ይሆናል።

አመለካከትና የቋንቋ ትምህርት የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸው ይታመናል። ተማሪዎች ለአንድ ትምህርት ጥሩ አመለካከት ካላቸው በዚያ ትምህርት ጥሩ ውጤት ያመጣሉ። በአንፃሩ ደግሞ ለአንድ የትምህርት ዐይነት ጥሩ አመላካከት ከሌላቸው በዚያ የትምህርት ዐይነት ዝቅተኛ ውጤት ያገኛሉ። ከዚህም አልፎ ትምህርቱን የሚያስተምረውን መምህር እስከ መጥላት እንደሚደርሱ በርካታ ጥናቶች አረጋግጠዋል። (Aggarwal 1988፤ Skinner 1989)

ይህ አስተያየት በህብረተሰቡም፣ በመምህራንም ዘንድ ተቀባይነት ያለው አመለካከት ነው። ፀጋዬ አረጋይ (1996) ባቀረበው የመመረቂያ ጽሁፍ ውስጥ Spolsky (1989) እና Nunan (1996) ጠቅሶ "አመለካከት በቋንቋ ተስተምህሮ (Learning) ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ቀጥተኛ ሳይሆን ተጽእኖ ሊያመጣ ወደሚችል ማነቃቂያ (motivation) የሚያመራ ነው ብለዋል።" በማለት ገልጿል።

አመለካከት ለአንድ ነገር ያለን ጥሩም ሆነ መጥፎ ዝንባሌ ነው። አመለካከት (attitude) እንዲህ ነው ብሎ ብያኔ ለመስጠት ያስቸግራል። Gagne (1976) ሲገልጽ "የሰው ልጆች በአጠቃላይ ለነገሮች ወይም ክስተቶች የሚኖራቸውን በጎ ወይም መጥፎ አስተያየትን አመለካከት" ይለዋል።

እንግዲህ ከዚህ በላይ የቀረበውን የምሁራን ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጥናቱ ውስጥ አመለካከት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ ለማየት ይሞከራል።

የዚህ ጥናት ትኩረት የመሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል የሚለውን ለመመርመር ነው። ስለሆነም የአማርኛ ቋንቋ አጀማመርና አሁን የደረሰበት ሁኔታ ለመገንዘብ እንዲያስችል ስለ ቋንቋው አጠር ያለ ቅኝት እንደሚከተለው ይቀርባል።

የአማርኛ ቋንቋ የት አካባቢ እንደተጀመረ፣ በየትኛው ዘመን ሊስፋፋ እንደቻለ፣ በማስረጃ አረጋግጦ ለመናገር አይቻልም። ይሁን እንጂ የአማርኛ ቋንቋን አስመልክቶ ጥናት ያደረጉ በርካታ የአገር ውስጥም ሆኑ የውጭ ምሁራን የተለያዩ አስተያየቶችን ሲሰጡ ይስተዋላሉ። ከነዚህም መካከል ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል አለቃ ታዬ (1958)፣ ዮናስና ሌሎች (1966) አምሳሉ (1976)፣ ባየ (2000)፣ Girma (2009) ይጠቀሳሉ። ከውጭ ምሁራን ደግሞ Bender (1976)፣ Cooper (1976)፣ Pankhurst (1972)። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ምሁራን ስለ አማርኛ ቋንቋ አጀማመር በመላምት ደረጃ አስተያየታቸውን አቅርበዋል።

ታየ «የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ» በተሰኘው መጽሐፋቸው ስለ አማርኛ ቋንቋ ሲገልጹ፣ በኢትዮጵያ በደቡብ ክልል ከሚነገሩት ቋንቋዎች አንዱ አማርኛ ነው። አማራ የተባሉትም ህዝቦች የሳንይንት የላም አገር፣ በጌምድር የበግ አገር፣ ደምቢያ የከብት አገር ሲሆኑ ከሶስቱም መደበኛ አማራ ሳይንት ነበር (ታየ 1958፣26)።

ይህ የአለቃ ታየ ገለፃ የሚጠቁመው አማርኛ በመጀመሪያ በጣም ጥቂት አካባቢዎች ይነገር እንደነበር ነው።

አምሳሉ (1976፣145) ሲገልጹ ደግሞ አማርኛ ራሱን የቻለ ቋንቋ ሆኖ ከመቼ ጀምሮ መነገር እንደጀመረ በእርግጥ ለመናገር ያዳግታል። ከሰባተኛው ምዕተ ዓመት ድህረ ልደተ ክርስቶስ ጀምሮ ግን ግዕዝ እንደ ህያው ቋንቋ እየሆነ መሄዱ ይነገራል። አማርኛ ከተባለው ዘመን ጀምሮ እንዲህ የመሰለውን ቦታ ያግኝ እንጂ እስከ 19ኛው መቶ ምዕት ዓመት መጀምሪያ ድረስ ለጽሑፍ አገልግሎት የዋለባቸው ጊዜያት በጣም መጠነኛ ናቸው በማለት ገልጸዋል።

ዮናስና ሌሎች (1968፣118) ሲገልጹ፣ አማርኛ በ14ኛውና በ15ኛው ክፍለ ዘመን ለነገስታቱ የሙገሳ ግጥም ይጻፍበት ነበር። በአፄ አምደጽዮን ዘመን ቋንቋው እያደገ ሄዶ ወደ ጽሑፍ ደረጃ ሊሸጋገር በቅቷል በማለት አስረድተዋል። በመቀጠል አማርኛ ከአክሱም ዘመን መንግስት በኋላ ማለትም ከ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የወቅቱ አስተዳደር፣ የመንግስቱን ዋና ከተማ ለቆ ወደ መሃል አገር ወደ ላስታ በመዛወሩ ምክንያት ቀስ በቀስ እያደገና እየተስፋፋ ሄዶ የህዝብ ቋንቋ እየሆነ መምጣቱን ሰፋ ያለ አስተያየት አቅርበዋል።

Bender, et.al. (1976) በበኩላቸው ስለአማርኛ ቋንቋ እድገት ሲያብራሩ፣ ከ4ኛው ክፍለ ዘመን እስከ 9ኛው ክፍለ ዘመን በአክሱም ዘመነ መንግስትና ክርስትናን በተቀበሉ ሰዎች ግዕዝን መግባቢያ አድርገው ይጠቀሙ ነበር። የአክሱም ዘመነ መንግስት ካከተመ በኋላ ግን ግዕዝ በሰሜን አካባቢ በትግርኛ፣ ወደ ደቡብ ደግሞ በአማርኛ እየተተካ ሄዷል። ከዚያ በኋላ ግዕዝ የቤተ ክርስቲያን ቋንቋ አማርኛ ደግሞ የዕለት ተዕለት መግባቢያ ቋንቋ እየሆነ መጥቷል በማለት ገልፀዋል።

ስለ አማርኛ ቋንቋ አጀማመር ከዚህ በላይ ከቀረበው ለየት የሚለው ደግሞ በባዬ የቀረበው ሀሳብ ነው። እንደ ባዬ (2000፣xv) አገላለጽ ከሰሜን የተነሱት የሴም ወገኖች ግዛታቸውን በማስፋፋት ወደ መሃል አገር ይመጣሉ። ሰራዊታቸው የኩሽ፣ የኦሞና የአባያዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሲሆኑ አዝማቾቹ ደግሞ ከግዕዝ ትንሽ ለየት የሚል የሴም ቋንቋ ተናጋሪ ነበሩ። እነዚህ የሴም ወገኖች ከሰራዊቱ ጋር በአገው መሬት ላይ ከህዝቡ ጋር መኖር ይጀምራሉ። ሰራዊቱም ቀስ በቀስ የአዝማቹን ቋንቋ መልመድ ይጀምራል። የተለያዩ ቋንቋ ይናገር የነበረው ሰራዊት ቀስ በቀስ የአዝማቹን የሴም ቋንቋ ይለምዳል። የአዝማቹ ቋንቋም ሴማዊ ባህሪውን እየተወ የኩሽና የኦሞ ቋንቋዎችን እየመሰለ መጣ። ወደ አራተኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ ከጥንቱ የሴም ቋንቋ የተለየ ይሆንና ከነበረው የአካባቢ ስም በመነሳት "አማርኛ" ተብሎ መጠራት ይጀምራል። "አማርኛ" በአንድ የተለየ ብሔረሰብ ሳይሆን የተለያየ ቋንቋ ይናገር በነበረ ዘማችና አዝማች የተፈጠረ የሰራዊት ቋንቋ ነው፣ ሲሉ አስተያየታቸውን አቅርበዋል።

ከዚህ በላይ የተለያዩ ምሁራንን ዋቢ በማድረግ ለመግለፅ የተሞከረው የአማርኛ ቋንቋ ታሪካዊ አጀማመሩ ምን እንደሚመስል ነው። አማርኛ ከአስራ ሶስተኛው ክፍለ ዘመን በፊት የነበረው ታሪክ ከመላምት ያላለፈ መሆኑን እንገነዘባለን። የአማርኛ ቋንቋ

ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ላይ የደረሰው በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም እስከ ዳግማዊ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት ድረስ አልፎ አልፎ በስነ ጽሁፍ ተግባር ላይ ከመዋሉ በቀር አብዛኛውን አገልግሎት ይሰጥ የነበረው ግዕዝ ነበር። የዳግማዊ ቴዎድሮስ መንግስት ለአማርኛ መስፋፋትና መጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉ ታሪካዊ መረጃዎች አሉ። እንደ አምሳሉ (1976፣ 189) አገላለጽ አፄ ቴድሮስ የራሳቸውን ታሪክ በአማርኛ እንዲፃፍ አለቃ ዘነበን ማዘዛቸው ለአማርኛ መስፋፋት ፍላጎት እንደነበራቸው መገንዘብ ይቻላል። ከቴዎድሮስ በኂላ ደግሞ አፄ ሚኒሊክ የኢትዮጵያን ድንበር ከማስፋፋት ጋር አማርኛን ይበልጥ እንዲስፋፋ አድርገዋል።

በሃያኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ በተለያዩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች የተነሳ ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች ብቅ ብቅ ማለት የጀመሩበት ጊዜ ነው። Pankhurst (1976፣315) ዳግማዊ ምኒሊክ የመጀመሪያውን ትምህርት ቤት በስማቸው በ1908 (እ.ኤ.አ) አቋቋሙ በማለት ገልፀዋል። በዚሁ ትምህርት ቤት ከፈረንሳይኛ፣ እንግሊዝኛና ጣሊያንኛ በመቀጠል አማርኛ እንደ ትምህርት አይነትነት ይሰጥ ነበር። ትምህርት ቤቱ አማርኛ መፃፍና ማንበብ ለሚችል ሁሉ ክፍት ነበር በማለት Pankhurst ይገልፃሉ።

አማርኛ በመግባቢያ ቋንቋነቱ እያደገና የአገልግሎቱም አድማስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ መጥቶ አሁን ያለበት የእድገት ደረጃ ላይ ደርሷል።

በ1983 ዓ.ም አጋማሽ ላይ በኢትዮጵያ የመንግስት ለውጥ ከተደረገ በኂላ አማርኛ የስራ ቋንቋ እንዲሆን በመመረጡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት የስራ ቋንቋ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል።

አማርኛ የስራ ቋንቋ ከመሆን ጎን ለጎን በክልል 3 እና በአዲስ አበባ መስተዳድር ለሚኖር ህዝብ የዕለት ተዕለት ተግባር ማከናወኛ ቋንቋ እንዲሁም የመንግስት የሥራ ቋንቋ ነው። ደቡብ ህዝቦች፣ ጋንቤላና የቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሕዝቦች አማርኛን የክልላቸው መንግስት የሥራ ቋንቋ አድርገው በመጠቀም ላይ ይገኛሉ።

አማርኛ በሁሉም የኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቤቶች ከአራተኛ ክፍል ጀምሮ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ እንደ አንድ የትምህርት አይነት የሚሰጥ ሲሆን በክልል 3 እና ክልል 14 ግን ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ይሰጣል። በተጨማሪም ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ የትምህርት ቋንቋ ሆኖ እዲያገለግል ተወስኗል (የትምህርት ስልጠና ፖሊሲ ረቂቅ 1985)።

በ1986 ዓ.ም የወጣው አዲሱ የትምህርት ስልጠና ፖሊሲ በተለይ የሁለተኛ ደረጃን ትምህርት አስመልክቶ ሲገልጽ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በሁለት ሳይክል የተከፈለ ነው። የመጀመሪያው ሳይክል 9ኛ-10ኛ ክፍል ያሉትን የሚያካትት ሲሆን፣ ሁለተኛው ሳይክል ደግሞ የመሰናዶ ተማሪዎችን (11ኛና-12ኛ ክፍልን) ያጠቃልላል።

በሁለተኛ ሳይክል ውስጥ የሚገኙት የመሰናዶ ተማሪዎች የቅድመ ኮሌጅ ትምህርት ይማራሉ። ለመሰናዶ ተማሪዎች በተዘጋጀው ስርአት ትምህርት ውስጥ አማርኛ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ይሰጣል። ይህ ስርአተ ትምህርት ሲዘጋጅ ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከመግባታቸው በፊት ቅድመ ዝግጅት የሚያደርጉበት መርሃ ግብር ነው።

እነዚህ የመሰናዶ ተማሪዎች የሁለተኛ ዓመት ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመግባት የአገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት የሚያዘጋጀውን የመግቢያ ፈተና ይወስዳሉ። ማለፊያ ነጥብ አግኝተው ያለፉ ተማሪዎች በሚያስመዘግቡት ነጥብ ወደ ልዩ ልዩ ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች ይመደባሉ።

ከዚህ በላይ በቀረበው ዳሰሳ የአማርኛ ቋንቋ ከአጀማመሩ ተነስቶ አሁን እስከ ደረሰበት የእድገት ደረጃ ለማሳየት ተሞክሯል።

በአጠቃላይ ጥናቱ ከላይ ከቀረቡት ጉዳዮች አነሳሽነት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከትና የውጤት ተዛምዶ መመርመርን ዓላማ አድርጎ ተነስቷል። ከዚህም በተጨማሪ፣

1. አማርኛ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ፈተና ላይ እንደ ሌሎቹ የትምርት አይነቶች ሳይካተት መቅረቱ፣

2. ተማሪዎች በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ ይሳተፋሉ ወይ የሚለውን ለመመርመር፤

3. ከአንድ ጥናት በስተቀር በመሰናዶ ትምህርት ቤት ላይ የተጠና ጥናት ያላጋጠመኝ በመሆኑ፤

4. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በአመለካከት ላይ የተጠኑ ጥናቶች ቢኖሩም አብዛኞቹ ረጅም ዓመታትን ያስቆጠሩ በመሆናቸው እና የመሳሰሉት መሪ ጥያቄዎች ለዚህ ጥናት እንደ መነሻ ምክንያት ሆነዋል፡፡

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓላማ በመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሚኖራቸው አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ ግብ ለመድረስ የሚረዱ ዝርዝር ዓላማዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ/ የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? የሚለውን ለማረጋገጥ፤

ለ/ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት በውጤታቸው ላይ ተጽእኖ አሳድሮ እንደሆን መመርመር፤

ሐ/ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ በሚሰጡት ፈተናዎች ላይ አለመካተቱ ቋንቋውን ለመማር ያላቸውን ተነሳሽነት አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሮ እንደሆን ማረጋገጥ፤

መ/ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ ፈተና ላይ አለመካተቱ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ የፈጠረውን ስሜትና በተማሪዎችና በመምህራን መካከል ያለውን ግንኙነት መመርመር፤

ሠ/ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሚኖራቸው አመለካከት ላይ የትምህርት ቤቱ ርዕሳነ መምህራንና የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ተጽእኖ መኖሩን ማረጋገጥ፡፡

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

አመለካከት በቋንቋ ትምህርት ላይ አዎንታዊ ሆነ አሉታዊ አመለካከት ሊኖረው እንደሚችል የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ። (Skinner 1985, Bugleski 1971)

ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሚኖራቸው አመለካከት ምክንያት በውጤታቸው ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ በመፈተሽ ከጥናቱ በተገኘው ውጤት መሠረት አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለማስተካከልና የመፍትሄ ሀሳብ ለማቅረብ ያስችላል። በሌላ በኩል የአማርኛ ቋንቋ ሰፊ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። የፌዴራል መንግስት የሥራ ቋንቋ ነው። በአዲሱ የትምህርት ፓሊሲ በአዲስ አበባ አስተዳደርና በአንዳንድ ክልሎች በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስተማሪያነት፣ በመሰናዶ ትምህርት ቤት እንደ አንድ የትምህርት ዐይነት ይሰጣል። ስለሆነም በቋንቋው ላይ የሚደረጉ ጥናቶች የቋንቋውን ተናጋሪ ባህልና ስልጣኔ ለማሳደግ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕውቀትን ለማስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

ስለሆነም ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል።

- ተማሪዎች ለአማርኛና ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል ለሚለው ፍንጭ ይሰጣል።
- ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለውን ዝምድና በመመርመር ከጥናቱ በሚገኘው ውጤት መሰረት ጠቃሚ የሆነ የመፍትሄ ሀሳብ ለማቀረብ ያስችላል።
- በዚህ ርእስ ዙሪያ ሰፊ ጥናትና ምርምር ማድረግ ለሚሹ ተመራማሪዎች መነሻ ሀሳብ በመሆን ያገለግላል።

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአዲስ አበባ መስተዳድር ውስጥ በሚገኙ የመንግስት መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ያተኩራል። አጥኚው ከጊዜና ከአቅም ውስንነት አንፃር የግል የመሰናዶ ትምህርት ቤቶችን በጥናቱ አላካተተም።

ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በተገኘው መረጃ መሰረት በአዲስ አበባ መስተዳድር አስራ አራት የመንግስት የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች እና ሶስት የግል መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ።

ከነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሶስት የመንግስት መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎችና መምህራን በዕጣ ንሞና (Random sampling) መሠረት ተመርጠዋል። በነዚህ የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአጠቃላይ 1400 ተማሪዎች ይገኛሉ። 11 መምህራን በዕጣ ንሞና በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል።

## 1.5. ሙዳዬ ቃላት

### የቃላት ትርጓሜ

| | |
|---|---|
| Anxiety | ጭንቀት |
| Aptitude Score | የአመለካከት ውጤት |
| Attitude | አመለካከት |
| Changeable | ተለዋዋጭ |
| Confidence | በራስ መተማን |
| Correlation | ተዛምዶ |
| Covert | ድብቅ |
| Feed back | መጋቤ-ምላሽ |
| Innate | አብሮን የሚወለድ |
| Interst | ፍላጎት |
| Learning | ተስተምህሮ |
| Mean | አማካይ |
| Motivation | ንሺ /መነቃቃት/ |
| Negative Attitude | አሉታዊ አመለካከት |
| Peers | እኩዮች |
| Personality | ሰብዕና |
| Positive Attitude | አዎንታዊ አመለካከት |
| Reinforcement | ግፊት |

| | |
|---|---|
| Reliability | አስተማማኝ |
| Response | ምላሽ |
| Second Language | ሁለተኛ ቋንቋ |
| Situational | ሁኔታዊ |
| Skill | ክሒል |
| Standard deviation | መደበኛ ልዩነት |
| Test Score | የፈተና ውጤት |
| T-test | ቲ ቴስት |
| Validity | ተገቢነት |
| Variable | ተላውጦ |

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን

በዚህ ክፍል ውስጥ በጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችን ለመቅረፅና የጥናቱን አቅጣጫ ለማሳየት የሚረዱ አስፈላጊ የሆኑ ንድፈ ሐሳቦች ሰፍረዋል፡፡

በመጀመሪያ የአመለካከት መሰረት ሀሳብ በሚለው ክፍል የአመለካከት ምንነት፣ የአመለካከት ባህሪያት፣ አመለካከትና የውጤት ዝምድና፣ የአመለካከት ተጽዕኖዎችና መነሻቸው ምን እንደሆነ በአጭር በአጭሩ ቀርቧል፡፡ ከዚያ በመቀጠል ደግሞ ጥናቱ ትኩረት የሚያደርግበት የአማርኛ ቋንቋ አጀማመርና ታሪካዊ ዳራ፣ አማርኛ እንደትምህርት አይነትና እድገቱ፣ አማርኛ እንደማስተማሪያ ቋንቋና አሁን የደረሰበት የእድገት ደረጃ አጠር ባለ መልክ ዳሰሳ ተደርጓል፡፡

### 2.1 የአመለካከት መሰረተ ሀሳብ

ከ1950 እ.ኤ.አ ጀምሮ የሰውን አእምሮ፣ አስተሳሰብና አመለካከት ለማጥናት በርካታ የስነ ልቦና ምሁራን ጥናትና ምርምር ሲያካሂዱ ቆይተዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ እነ Gardner (1958), Skinner (1985) Morgan (1986) Cronbach (1954) ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ምሁራን የአመለካከት ምንነት? አመለካከት እንዴት ይመሰረታል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ጥናቶችን አካሂደዋል፡፡

#### 2.1.1. የአመለካከት ምንነት

አመለካከት ለአንድ ነገር ያለን ጥሩም ሆነ መጥፎ ዝንባሌ ነው፡፡ አመለካከት እንዲህ ነው ብሎ ቁርጥ ያለ ብያኔ ለመስጠት ያስቸግራል፡፡ Gagne (1976) ሲገልè "የሰው ልጆች በአጠቃለይ ለነገሮች ወይም ለክስተቶች የሚኖራቸው በጎ ወይም መጥፎ አስተያየትን አመለካከት" ይሉታል፡፡ ይህም ማለት አመለካከት ለተለያዩ ሰዎች ወይም ሁኔታዎች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የአስተሳሰብ ሁኔታ ነው፡፡ ይህን ሃሳብ ለማጠናከር Morgan (1986፣ 382-384) ሲገልጹ፡-

> አመለካከት በግለሰቦች ገለፃ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ለአንድ ነገር የሚሰጡትን ግምገማ የሚወክል ነው፡፡ በመቀጠል ማንኛውም ግምገማ ስሜት የሚቀስቅስ ነገር ለአንድ ሁኔታ ወይም ነገር

አመለካከት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ከዚሁ ጋር አያይዘው ለአንድ ነገር የሚኖረን ግምት የመውደድ፣ የመጥላት፣ የመደገፍ፣ የመንቀፍ፣ የመስማማት፣ ያለመስማማት፣ አዎንታዊና አሉታዊ በሆኑ ምላሾች ይገለፃሉ፡፡

እንግዲህ ከዚህ በላይ በጥቅስ ውስጥ የቀረበውን ሃሳብ ስንመረምር አመለካከት የሰዎችን ውስጣዊ ፍላጎትና ጥልቅ ስሜቶች ሁሉ የሚገለፅበት መሆኑን እንረዳለን፡፡

የስነ-ልቦና ምሁራን አመለካከትን ሲገልጹ፣ "አመለካከት አንድን ነገር መፈለግ ወይም መጥላት፣ አንድን ነገር መውደድና መጥላት፣ አንድን ነገር መቀበል ወይም አለመቀበል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን አመለካከት ከዚህ ሰፋ ያለ ትርጉም እንዳለው Cronbach ይገልፃሉ፡፡ እንደሳቸው አገላለፅ ‹‹አመለካከት ማለት ራስን ከአንድ ነገር ወይም ሀሳብ ጋር አዛምዶ መመልከትና ነገሩን ወይም ሀሳቡን መቀበል ነው፣ እነዚህ ነገሮች የተወሰኑ ወይም ተጨባጭ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በማንኛውም አመለካከት ውስጥ መቀበል ወይም አለመቀበል ይኖራል፡፡" በማለት ሃሳቡን ያብራራሉ (Cronbach 1954፣ 325-326)፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሀሳብ የምንገነዘበው አመለካከት ከሰው ልጆች ፍላጎትና አስተሳሰብ ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው፡፡ አንድን ነገር ስንወድ ወይም ስንጠላ ለዚያ ለምንወደውና ለምንጠላው ነገር አመለካከታችን የራሱ የሆነ ተጽዕኖ እንዳለው እንረዳለን፡፡ አመለካከት እንዲህ በቀላሉ ፍቺው ይህ ነው ብሎ ለመናገር በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም በሰው አእምሮ ውስጥ ያለውን ስሜት መግለጫም ነውና፣ አመለካከት ከስነ-ልቦና ባህሪ አንፃርም ሊታይ ይችላል፡፡

Collier Encyclopedia (1975፣203) አመለካከትን እንደሚከተለው ሲያብራራ

> አመለካከት ከስነ ልቦና ጉዳይ ጋር የተያያዘ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት ያለው ነገር ነው፡፡ አንድ ሰው ለአንድ ነገር የሚሰጠው ምላሽ ከስነ-ልቦናዊ ሁኔታ ጋር ይያያዛል፡፡ ግንኙነቱ ከስነ-ልቦናዊ ጉዳዮችም ጋር ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ለነገሮች፣ ለሃሪጎች ለአባባሎች የሚኖረውን ግንዛቤ ...ወዘተ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ለአንድ የተለየ ሥራ ወይም ስለ አንድ

የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ስለ ተባበሩት መንግስታት የራሳችን የሆነ አመለካከት ይኖረናል፡፡ አንድን ነገር መውደድ ወይም መጥላት፣ መቀበል ወይም አለመቀበላችንን ለመግለፅ ስንፈልግ ለዚያ ጉዳይ ያለን አመለካከት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል በማለት ገልጿል፡፡

ከጥቅሱ እንደምንረዳው አመለካከት ሰፊ ሀሳብን የሚገልጽ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ምን አይነት አመለካከት አላቸው የሚለውን ለማወቅ ከአንድ አቅጣጫ ብቻ መመልከት የለብንም፡፡ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ ከስነ-ልቦና ሁኔታ፣ ከወቅቱ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች አንፃር መመልከት እንዳለብን ነው፡፡

አመለካከት ከሰዎች ውስጣዊ ስሜት፣ ፍላጎትና ምኞት፣ ግምት ጋር የተያያዘ ስለሆነ በባህሪው ውስብስብ፣ ረቂቅና በአይን የማይታይ በእጅ የማይዳሰስ ነገር ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ድብቅና በቀላሉ የማይታይ ሊሆን ይችላል (Oppenheim, 1984፣106፣ Gardner, 1958፣8)፡፡ ይህንን ሀሳብ፣ ያለው (2001፣62) ሲያጠናክሩት፣

> አመለካከት ረቂቅ የሆነ በገሀድ በአይናችን ልናየው፣ በጆሯችን ልንሰማውና በእጃችን ልንዳስሰው የማንችል ነገር ግን መኖሩን የምናውቅና በተለያዩ መንገዶች እንደሚከሰት የምንረዳው ስውር ወይም ድብቅ (Covert) ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ መነሳሳት (Motivation) ፈጠራ (Creativity) እውቀት (Intelligence) ፍላጎት (Interst) ጭንቀት (Anxiety) የመሳሰሉት ወዘተ. እንዳሉ እናውቃለን፡፡ እነዚህም ነገሮች በባህሪያችን ተጽእኖ ያደርጋሉ፡፡ እንዲሁም በእለት ተዕለት ክንዋኔዎችም ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ስለዚህ አመለካከት በአስተሳሰባችን፣ በማህበራዊ ኑሯችን፣ በዕለት ተዕለት ተግባራችን እንዲሁም ከሰዎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት የሚያሳድረው ተፅዕና ከፍተኛ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

Smith (1971:82) አመለካከትን ሲገልè ይማሩታል፤ ከተማሩት ደግሞ ያስተምሩታልም፡፡ እንደ ቋንቋ ሁሉ አመለካከትን የሚማሩትና በልምድ የሚያዳብሩት እምነት፣ አተያይም ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመለካከት አብሮን የተፈጠረ (Innate) ሳይሆን በትምህርትና በልምድ የሚገኝ ነው፡፡ በቋንቋ ትምህርት ሂደትም ምንም እንኳን ተማሪው በመጀመሪያ ጥሩ አመለካከት ወይም ገለልተኛ የሆነ ግምት ይዞ ቢገባም በትምህርቱም ሆነ ከክፍል ውጭ በሚገጥሙት ነገሮች ምክንያት ለቋንቋው ያለው አመለካከት ይለወጣል፡፡ ስለዚህ አመለካከት በሚያጋጥመን ነገሮች ሁሉ የመለወጥ ባህሪ ሊያሳይ፣ ሊበላሽም ሆነ ሊስተካከል የሚችል ይሆናል፡፡ ስለሆነም አመለካከት ሁኔታዊና ተለዋዋጭ ነው ማለት ይቻላል በማለት አስተያየቱን አቅርቧል፡፡

ይህም የሚያመለክተው አመለካከት ተማሪዎች ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት እንዲነሳሳ (Motivated) ወይም እንዲቀንስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ነው፡፡

ከዚህ በላይ የቀረበውን ሀሳብ በማጠናከር Cronbach (1954፡310 ሲገልጹ፣

> አመለካከት ለእያንዳንዱ የትምህርት ዓላማ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የባዮሎጂ ትምህርት ስለ ዱር እንስሳት፣ የህብረተሰቡ ጤና የሚጠበቅበትና ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት ያለንን አመለካከት ለመለወጥ ይረዳናል፡፡ የቋንቋ ትምህርት ከሰዎች ጋር ለመግባባት፣ ማህበራዊ ግንኙነትን ለማጠናከር የሚኖረንን አመለካከት ለመለወጥ ይረዳል፡፡ አመለካከት በተለይ በማህበራዊ ሳይንስ ላይ ያተኩራል፡፡ አመለካከት በትምህርት ሊሻሻልና ሊስተካከል ይችላል፡፡

በዚህ አባባል አመለካከት ሊለወጥ፣ ሊያሻሽል እንደሚችልና በተለይ ለማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት እጅግ ጠቃሚ መሆኑን እንረዳለን፡፡

ተማሪዎች አንድን ቋንቋ የመውደድ ወይም የመጥላት ሁኔታ ዝም ብለው ከመሬት ተነስተው የሚፈጥሩት ጉዳይ አይደለም፡፡ ለዚህ እንደምክንያትነት የሚጠቀሱ በርካታ ተላውጦዎች አሉ (Rosenberg & Houland 1980፡6)፡፡ እነዚህ ተላውጦዎች በመባል የሚታወቁት ቋንቋውን እንደሚማረው ተማሪ፣ እንደየቋንቋው ትምህርት ውስብስብነት፣ ቤተሰባዊ ዳራ፣ የተማሪው ስነ-ልቦናዊ አስተሳሰብ፣ ከፖለቲካዊ፣ ማህበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ የሚመነጩ ሊሆኑ ይችላሉ በማለት ገልፀዋል፡፡

ስለዚህ ተማሪዎች አንድን ቋንቋ ለመውደድ ወይም ለመጥላት የተለያዩ ምክንያቶች እንዳሉ ከፍ ሲል ምሁራኑ ከጠቀሱት ሀሳብ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህ በላይ የቀረበውን ሀሳብ በመደገፍ Spolsky (1989፤15) ቋንቋን ስለመማር አስመልክተው ሲገልፁ፤ "የቋንቋ መማር ማስተማር ተግባር ከማህበራዊ ዐውድ ውጭ ተነጥሎ ሊታይ አይችልም፡፡ በማህበራዊ ዐውድ ውስጥ ከሚጠቀሱት ተላውጦዎች (Variables) መካከል ቤተሰብ፤ አካባቢ፤ ትምህርት ቤቶች መንግስት ይገኙባቸዋል" ብሏል፡፡ ለምሳሌ፤ ወላጆች ልጆቻቸው ታላሚውን ቋንቋ እንዲማሩ የማበረታታትና ያለማበረታታት ደረጃ፤ የተማሪ ሁኔታ፤ የመማር ማስተማሩ ዘዴ ወዘተ. ዋና ተጠቃሾች መሆናቸውን አስረድቷል፡፡

## 2.1.2. የአመለካከት ባህርያት

አመለካከት ሁኔታዊ (Situational) እና ተለዋዋጭ (Changeable) እንደሆነ የስነ-ልቦና ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ አመለካከት ስነ-ልቦናዊ ይዘት ያለው፤ ከሰዎች ውስጣዊ ስሜት፤ ፍላጎት፤ እምነት ...ወዘተ. ጋር የተያያዘ ስለሆነ በባህሪው ውስብስብ፤ ረቂቅና ድብቅም ነው፡፡ Cronbach (1954፤ 325) ይህንኑ ሲገልጹ፤ "አንዳንድ አመለካከቶች በጣም ስር የሰደዱ በመሆናቸው ለማወቅ በጣም ያስቸግራሉ፡፡ አንዳንድ አመለካከቶች ደግሞ በጣም ድብቅ በመሆናቸው በየጊዜው ከምናያቸው ባህሪያት ለማወቅ ያስቸግራል፡፡"

ስለሆነም የአመለካከት ባህሪያትን ለማወቅ የሰውን ልጅ አእምሮ ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ የሰው ልጅ ምን እንደሚፈልግ፤ ምን እንደሚጠላ፤ ውስጣዊ ስሜቱን፤ እምነቱን ሁሉ መረዳት ይጠይቃል፡፡ ይህ ደግሞ በጣም ረቂቅ፤ ውስብስብና በጣም አስቸጋሪ መሆኑን ከዚህ በላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.2. አመለካከትና የውጤት ዝምድና

አመለካከት በተማሪዎች ውጤት ላይ የራሱ የሆነ ተጽእኖ እንዳለው የስ-ልቦና ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ በትምህርት ቤቶች ውስጥ በመምህራንም ሆነ በህብረተሰቡ ዘንድ የተለመደ አስተያየት ሲሰነዘር ይደመጣል፡፡ አንድ ተማሪ በታላሚው ቋንቋ ላይ ጥሩ አመለካከት ካለው በትምህርቱም ጥሩ ውጤት ያስመዘግባል፤ መጥፎ አመለካከት ካለው ደግሞ ውጤቱ ደካማ ይሆናል የሚል አስተያየት ይሰማል Spolsky (1989)

Skinner (1985) እና Buglisky (1971)፡፡ ከዚህ በላይ የቀረበውን ሀሳብ በመደገፍ ሲገልጹ፣ ተማሪዎች ለአንድ ትምህርት ጥሩ አመለካከት ካላቸው ትምህርቱን ለመማር ከፍ ያለ መነቃቃት (Motivation) ያሳያሉ፤ ፍላጎታቸውም ከፍ ይላል፡፡ ለትምህርቱም ጥሩ አመለካከት ይኖራቸዋል ይህንን ሃሳብ Taddele ያጠናክረዋል፡፡

> አመለካከት አንድ ሰው ከሚገጥመው ወይም በውስጡ ከሚያልፍበት ነገር ጋር በሚያደርገው ተራክቦ ስለ ጉዳዩ የሚኖረው ግምት ቅርበትና ርቀት፣ ውዴታና ጥላቻ ነው፡፡ በቋንቋ ትምህርት ሂደትም ተማሪ የሚገጥመውና በውስጡ የሚያልፍበት ማለትም የቋንቋው መምህር፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ አጠቃላይ የትምህርቱ ስርዓትና ሌሎች ማህበራዊ የሆኑ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪ ከነዚህ ጉዳዮች ጋር በሚያደርገው መስተጋብርና የመማር እንቅስቃሴ የሚመነጭ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከትን ያዳብራል፡፡ ያዳበረው አመለካከት ደግሞ ተማሪው በትምህርቱ ሂደት ከሚያደርገው የመማር ጥረትና ከሚደርስበት ውጤት ጋር ይገናኛል በማለት ገልጿል፡፡ Taddele (1990፣14)

ከዚህ የምንረዳው አመለካከት ሰው በኑሮው ሂደት ከሚገጥመው ሁኔታ ወይም ነገር ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የጥላቻም ሆነ የመውደድ ስሜት ይኖረዋል፡፡ እንደዚሁም ተማሪው የቋንቋን ትምህርት ሲማር ከሚኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ፣ ከትምህርቱ ስርአትና ከሌሎችም መሰል ጉዳዮች ጋር በሚደረገው ግንኙነት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከትን ያዳብራል፡፡ ይህም በተዘዋዋሪ መንገድ በቋንቋ ትምህርቱ ላይ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

የአመለካከትንና የውጤትን ዝምድና አስመልክተው ሌሎች የመስኩ ምሁራን ጥናት አቅርበዋል፤ ከነዚህም መካከል አንዱ Muller (1971፣290) ናቸው፡፡ እንደ Muller አገላለፅ፡-

> ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ፣ ትምህርቱ የሚሰጥበት ሁኔታ፣ ለትምህርት ለቀረበው ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰቦችና ለባህላቸው፣ ለቋንቋው መምህርና ለመማሪያ መፃህፍት ያላቸው አመለካከት፣

> ከውጤታቸው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው። በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ድርሳናትም የሚያመላክቱት ይህንኑ ነው። አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ከአማካይ የተማሪዎች ውጤት (GPA) ከዝቅተኛው ጋር ጥምረት ሲያሳይ፣ አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ደግሞ ከከፍተኛው ውጤት ጋር ዝምድና አሳይቷል።

ስለዚህ መምህራን፣ አመለካከት በቋንቋ ትምህርት እና በውጤታቸው ላይ ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለው ተገንዝበው ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት እንዲያዳብሩ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት በጎ አመለካከት ካላቸው ደግሞ የፈተና ውጤታቸውም ጥሩ ይሆናል።

ስለ አመለካከትና መነቃቃት (Motivation) ምንነትና ከቋንቋ ትምህርት ጋር ስላላቸው ተዛምዶ በርካታና ተደጋጋሚ ጥናቶች ካደረጉ ምሁራን ውስጥ Gardner እና ተባባሪዎቹ ተጠቃሾች ናቸው (Gardner 1985፣ እነ Dubin 1986፤14፣ Onoda 1976፤152)። የMullerን ሃሳብ በመደገፍ ሲገልጹ፣ ለቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ከከፍተኛ ውጤት አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ደግሞ ከዝቅተኛ ውጤት ጋር ዝምድና እንዳለው በጥናታቸው አረጋግጠዋል።

Yule, እና ሌሎች (1985፤473) የተማሪዎችን አመለካከት ከራስ መተማመን (Confidence) ጋር አጣምረው ባጠኑት ጥናት ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ መልካም አመለካከት ካላቸው በትምህርቱም ንቁ ተሳታፊ ከመሆናቸውም በላይ በራሳቸው ላይ የመተማመን ስሜት ሊያሳድሩ ይችላሉ። በራሳቸው የሚተማመኑ ተማሪዎች ደግሞ ለቋንቋው ትምህርት ጥሩ አመለካከት ስለሚኖራቸው ውጤታቸው ከሌሎች ተማሪዎች የተሻለ መሆኑን በጥናታቸው ደርሰውበታል።

ስለዚህ አመለካከት ከተማሪዎች የትምህርት እንቅስቃሴና ውጤት ጋር የጠበቀ ግንኙነትና ተዛምዶ እንዳለው በርካታ የመስኩ ምሁራን በጥናታቸው አረጋግጠዋል። በትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራንም ሆኑ የትምህርት ባለሙያዎች፣ አመለካከት ከቋንቋ ትምህርት ጋር የጠበቀ ዝምድና እንዳለው ተገንዝበው ትኩረት ሊሰጡት ይገባል።

## 2.3. የአመለካከት ተጽዕኖዎችና መነሻቸው

### 2.3.1. ወላጆች፣ እኩዮችና ሕብረተሰብ

የአንድን ልጅ የህይወት መሠረት ለመጣል የእድገት አቅጣጫውን ለመወሰን ድርሻ ያላቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ። ከነዚህም ጥቂቶቹ ትምህርት ቤት፣ ቤተሰብ፣ ጓደኞች፣ የአካባቢ ነዋሪዎችና የእምነት ሁኔታዎች (ቤተክርስቲያን፣መስጊድ) የመሳሰሉት ናቸው። ከዚህ በላይ የቀረበውን ሃሳብ Harmer (1991፣4) ሲገልጹ ወላጆች፣ እኩዮችና ህብረተሰብ በልጁ አመለካከት ላይ የሚኖራቸውን ድርሻ እንደሚከተለው ያብራራሉ።

> ብዙ ሁኔታዎች በተማሪው የቋንቋ አመለካከት ላይ ተጽዕኖ ያደርጋሉ። ለምሳሌ የተማሪው ወላጆች የታላሚውን ቋንቋ የሚቃወሙና ባህሉን የሚጠሉ ከሆነ በልጁ አመለካከት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል። ይህም የልጁን አመለካከት ወደ አሉታዊነት ሊቀይረው ይችላል። በአንፃሩ ደግሞ ወላጆች በቋንቋው ላይ ያላቸው አመለካከት ጥሩ ከሆነ በልጁ አመለካከት ላይ አዎንታዊ ሁኔታን ይፈጥራል። ከዚህ በተጨማሪ የተማሪው እኩዮች አመለካከት አዎንታዊ ከሆነ የእሱም እንደዚያው ይሆናል። እንዲሁም የአካባቢው ህብረተሰብ ለታላሚው ቋንቋ ያላቸው አመለካከት በተማሪው አመለካከት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል።

እንግዲህ ከዚህ በላይ Harmer እንደተገለፁት ወላጆች፣ እኩዮችና ህብረተሰቡ የአንድን ልጅ የህይወት አቅጣጫ በመቅረጽ በኩል ከፍተኛ ሃላፊነት እንዳለባቸው ያስገነዝበናል።

Pikunas (1976) ከዚህ በላይ የቀረበውን ሃሳብ በመደገፍ ሲገልጹ፣

> ወላጆች ለልጆቻቸው ስለ አካባቢያቸው ሁኔታ እንዲያውቁ ማድረግ አለባቸው። ወላጆች ለልጆቻቸው እንክብካቤን ከማድረግ በተጨማሪም ባህላቸውን፣ እምነታቸውን፣ ሃይማኖታቸውን ማስተማር ይጠበቅባቸዋል። በስነ-ምግባር የታነፀ ስብዕና እንዲኖራቸው ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። ወላጆች በልጆቻቸው የወደፊት ባህርይና ስብዕና

ምስረታ ላይ የሚፈጥሩት ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው። የህፃናት አመለካከት በዘመዶቻቸው አምሳያ ይቀረፃል። ቤተሰብ ትልቅ ሀይል ያለው የትምህርት ተቋም ነው። ከዚሁ ጋር በተመሳሳይ መልኩ ተማሪው ያደገበት አካባቢ፣ እኩዮች አጠቃላይ ህብረተሰቡ በህፃናት ሰብዕና፣ የባህል፣ የአመለካከትና የአስተሳሰብ ቀረፃ ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው (Pikunas, 1976፣ 83)።

ስለዚህ ወላጆች የልጆቻቸውን ሰብእና በመቅረጽ በኩል ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ያስገነዝበናል። በተጨማሪም ወላጆች የልጆቻቸው የወደፊት ህይወት በስነ-ምግባር የታነፀ ሰብእና ይዘው እንዲያድጉ አስፈላጊውን እገዛና ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። ወላጆች ለልጆቻቸው መልካም አርአያ ሊሆኑ ይገባል። በዚህ መልክ ተኮትኩተው የሚያድጉ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት አቀባበላቸውም ጥሩ ተማሪዎች እንደሚሆኑ ከጽሁፉ እንገነዘባለን።

## 2.3.2. መምህሩና የማስተማር ሥነ-ዘዴ

ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ላይ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸውና ትምህርቱን በፍላጎትና በንቃት መማር እንዲችሉ የመምህሩ ሚና ከፍተኛ ነው። ከተማሪው ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው መምህሩ ነው። ስለሆነም የመማር ማስተማሩን ድባብ በማመቻቸትና በማገዝ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለበት (Harmer 1990፣6, Spolsky 1969፣65)።

የመምህሩ አመለካከት ለተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት አቀባበል ሁኔታ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። በእውቀቱና በችሎታው ላቅ ያለ መምህር በተማሪዎቹ አመለካከት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ለማደሳደር ይችላል። የመምህሩ የማስተማር ስነ-ዘዴ ተማሪዎቹን የሚስብና የሚማርክ፣ የተማሪዎችን መብት የሚያከብር ከሆነ ተማሪዎቹ በእሱ ላይ ጥሩ አመለካከት ይኖራቸዋል። በዚህም ምክንያት ደግሞ ለትምህርቱ ቀና አመለካከት ይኖራቸዋል። በተቃራኒው ደግሞ መምህሩ ሲያስተምር የማይስብ፣ የማይማርክና ተሳዳቢ ከሆነ ተማሪዎች ለእሱ መጥፎ አመለካከትና ጥላቻ ያድርባቸዋል። ስለዚህ መምህሩ ለሙያው ከፍተኛ ፍቅር ያለው፣ በስነ-ምግባሩ ተወዳጅ የሆነ፣ የሚያስተምረውን ትምህርት ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ ተማሪዎችን የሚወድና ታታሪ

ሊሆን ይገባዋል። እንዲህ አይነቱ መምህር በተማሪዎቹ ላይ አዎንታዊ አመለካከትን ሊያሳድር ይችላል።

Harmer ከዚህ በላይ የቀረበውን ሀሳብ በማጠናከር በተማሪዎች ላይ አዎንታዊ አመለካከትን ለማሳደር፣ አንድ የቋንቋ መምህር መፈፀም ያለበትን ተግባር እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡-

1. ትምህርቱን ማራኪ አድርጎ ማቅረብ፣
2. ጥሩ በሆነ የቋንቋ አነጋገር መጠቀም፣
3. ትምህርቱን ግልጽ በሆነ ሁኔታ ማቅረብ፣
4. በትምህርቱ ወቅት ሁሉንም ተማሪ እንዲሳተፉ ማበረታታት፣
5. ሁሉንም ተማሪ በእኩል አይን ማየት፣
6. በተቻለ መጠን ትዕግስተኛ መሆን፣
7. ሰብዕናውን /Personality/ መጠበቅ፣
8. በሚያስምረው የቋንቋ ትምህርት በቂ ችሎታ ያለው መሆን፣
9. የተማሪዎችን ችግር የሚረዳና ለችግሩ የመፍትሄ ሀሳብ የሚያቀርብ፣
10. ተስማሚ የማስተማሪያ ዘዴዎችን የሚጠቀም መሆን አለበት (Harmer, 1990፣18)።

ስለዚህ የቋንቋ መምህራን ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ጥሩ አመለካከት እንዲኖራቸው የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም የሚያስተምሩትን ትምህርት ሳቢና ማራኪ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ተማሪዎች በመምህሩ ላይ የሚኖራቸውን አመለካከት Krashen (1988፣ 23-24) እንደሚከተለው ይገልፃሉ።

> በክፍል ውስጥ ምንም አይነት ችግር የማይገጥማቸውና መምህሩን የሚወዱ ተማሪዎች፣ መምህሩ የሚያስተምረውን ትምህርት በሙሉ ፍላጎት ስለሚቀበሉ መምህሩን እንደ ዕውቀት ምንጭ አድርገው ይቀበሉታል። ይህ ለመምህሩ የሚኖራቸው አዎንታዊ አመለካከት የተማሪዎቹን በራስ የመተማመን ስሜት ያመለክታል። በተጨማሪም እኛ አዎንታዊ አመለካከት ይኖራቸዋል ብለን

> የምንጠብቃቸው ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ወቅት ጥሩ ሁኔታን ያሳያሉ።

ከዚህ በላይ የቀረበው ሀሳብ፣ በመምህሩ ላይ አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ለመማር ያላቸውን ፍላጎትና ለትምህርቱም ቀና አመለካከት ይራቸዋል ማለት ነው።

የመማር ማስተማሩ ሂደት በተጠናከረ መልኩ እንዲከናወን የመምህሩ ሚና ከፍተኛ መሆኑ አይካድም። ከዚሁ ጋር ጎን ለጎን ደግሞ ለትምህርቱ ጥራት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። Muller ይህንን ሀሳብ በመደገፍ ሲገልጹ ‹‹ተማሪዎች በጥሩ ስሜት እንዲማሩና ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ የትምህርትን አቅርቦት ጥራት መጠበቅ ይገባል ይላሉ። የትምህርት ክንውኑ ከተማሪዎች ችሎታ፣ ዕውቀትና ዝንባሌ ጋር የተስማማ መሆን አለበት። ተማሪዎች ለትምህርቱ የተዘጋጁትን ዓላማዎች ተገንዝበው ወደ ግብ እንዲጓዙ ማስቻል ይጠበቅበታል። አንዱ የማስተማር ዘዴዎችን እየለዋወጡ መጠቀም ተገቢ ነው (Muller, 1971፣ 296)።

ስለዚህ የትምህርትን ጥራት ለመጠበቅ ለመምህራን ብቻ የሚተው ጉዳይ አይደለም ተማሪዎችም የትምርቱን ዓላማ ተገንዝበው ለመማር ፍላጎቱና ተነሳሽነቱ ሊኖራቸው ይገባል። መምህራንም እንከን የለሽ የማስተማሪያ ዘዴ እንደሌለ ተገንዝበው በየጊዜው የማስተማር ዘዴያቸውን እያለዋወጡ ቢጠቀሙ የተሻለ ውጤት ይመዘገባል።

Skinner (1959:20) ከዚህ በለይ የቀረበው ሀሳብ በማጠናር ሲገልጹ፤

> ትምህርትን ለማስተማር ጥሩ የሆነ ዘዴ የለም። መምህሩ አንድ የተወሰነ ሁኔታን ለመግለፅ የሚጠቀምበት ሳይንሳዊ ፎርሙላ የለውም። ነገር ግን የማስተማሩን ሥራ መምህሩ አስቦት፣ ተጨንቆበት የሚሰራው ሥራ ውጤት ነው። ተማሪዎቹ ከሚያውቁት ነገር ተነስቶ፣ የራሱን ልምድ ተጠቅሞ፣ በተለያየ መንገድ እውቀቱን አዳብሮ ተማሪዎቹን በጥሩ ሁኔታ ለማስተማር ጥረት ያደርጋል።

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሃሳብ የምንገነዘበው የሰው ልጅ አንድን ትምህርት ለመማር ውስጣዊ ተነሳሽነት ሊኖረው ይገባል። ውስጣዊ ንሺ (Motivation) ካለው ደግሞ ለመማር ዝግጁ ይሆናል። ይህ ንሺ ደግሞ ትምህርታዊ ሂደቱንና ተማሪውን ውጤታማ እንዲሆን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። በትምህርት ሂደት ጊዜ ተገቢውን የማስተማሪያ ዘዴን በመጠቀም ማስተማር ተማሪዎችን የሚያነቃቃ ከመሆኑም በላይ

የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ይጨምራል። ስለዚህ መምህሩ የማስተማር ዘዴውን እያለዋወጠ በመጠቀም ማስተማር ይጠበቅበታል።

### 2.3.3. የመማሪያ መጻህፍት

ለተማሪዎች የሚዘጋጀው የመማሪያ መጽሐፍ የቋንቋን ፖሊሲና የስርአተ ትምህርቱን ዓላማ መሰረት አድርጎ ይዘጋጃል። የመማሪያ መጽሐፉ ለየክፍል ደረጃው የሚመጥን ሲለበስ ውስጥ የሚቀርብ የትምህርት ዓላማ፣ ይዘት ላይ ያተኮረ ሲሆን ከተማሪ ፍላጎት ጋር ቀጥተኛ ዝምድና ያለው ወደ ግብ የሚያደርስ መሳሪያ ነው።

ስርዓተ ትምህርቱን ለማዘጋጀት ሲታሰብ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ የትምህርት ባለሞያዎች፣ የሃይማኖት አባቶች የህብረተሰቡ አባላት ተሳታፊ መሆን አለባቸው።

ይህንን አስመልክተው Harmer (1990፣2) እና Richards (1987፣13) ሲገልጹ መርሃ ትምህርት ሲቀርጽ የመረጃ ምንጭ ለማግኘት በቅድሚያ የተማሪውን ፍላጎት መረዳት ያስፈልጋል። ተማሪው ቋንቋውን ለምን ዓላማ ብሎ ይማረዋል? ለትምህርቱ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል? ተማሪው የመጣበት ቤተሰብ፣ ህብረተሰብ፣ የትምህርት ተቋም፣ መንግስት፣ ከትምህርቱ መጨረሻ ምን እንዲሆንለት ይጠብቃል? ተማሪው ምን አይነት የባህርይና የቋንቋ ክሂል እድገት እንዲያመጣ ይፈለጋል? ወዘተ. የሚሉ ጥያቄዎች በትምህርቱ ሂደት ተጽዕኖ ሲያመጡ የሚችሉ ጉዳዮች በመሆናቸው በመጀመሪያ አስሳ ሊደረግባቸው ይገባል ይላሉ።

የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የተማሪውን አመለካከት በመቀየር በኩል ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። በመሆኑም አንድ የመማሪያ መጽሐፍ ከመዘጋጀቱ በፊት የተማሪዎቹ አመለካከት ስሜትና ፍላጎት መጠናት አለበት። የተማሪዎቹ አመለካከትና ፍላጎት ከተጠና በኋላ ተማሪዎቹ በሚፈልጉት መልኩ የመማሪያ መጽሐፉ መዘጋጀት ይኖርበታል። ብዙ ጊዜ ግን ይህ ሁኔታ ይዘነጋል። በተማሪዎች ፍላጎትና አመለካከት ተመስርቶ የተዘጋጀ የመማሪያ መጽሐፍ ተማሪዎችን ይስባል፣ ትምህርቱንም እንዲወዱት ያደርጋል፣ በሚማሩት ቋንቋ ላይ አዎንታዊ አመለካከትን ያዳብራል። በሌላ በኩል ደግሞ የተማሪዎችን ፍላጎትና አመለካከት መሰረት ያላደረገ የመማሪያ መጽሐፍ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል፣ ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲጠሉ ያደርጋል። ይህንን በተመለከተ Murcia "የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ ከውጭ ሽፋኑ ጀምሮ እስከ ይዘቱ ድረስ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። በተጨማሪም ስእሎች፣ ማብራሪያዎች

ቢ.ታከሉበት የተማሪዎችን ፍላጎትና ስሜት ለመቀስቀስ ያግዛል" Murcia (1991፣68) በማለት ገልፀዋል፡፡

ስለዚህ አንድ የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ የቃላት መግለጫዎች፣ ስእሎች፣ አባሪዎችን አሟልቶ የያዘ መሆን አለበት፡፡ መማሪያ መጻህፍቱ ከውጫዊ ቅርፃቸው ጀምሮ እስከ ውስጣዊ የአፃፃፍ ስልት፣ የስእል ቅንብሮችና ቅቦች ድረስ ጥሩ ቅርጽ የያዙና የሚማርኩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ መልክ የተዘጋጁ መፃህፍት ተማሪዎች ደስ ብሏቸው እንዲያነቧቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡

## 2.4. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ከጥናታዊ ጽሁፌ ጋር በመጠኑ ተቀራራቢነት ያላቸው አምስት የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፎችን ተመልክቻለሁ፡፡ እነዚህ ጽሁፎች ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ የተደረጉ ጥናቶች ሲሆኑ፣ ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

1. ታሪኩ ፋንታዬ (1988 ዓ.ም) "የአዲስ አበባ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ትምህርት ቋንቋ ላይ ያላቸው አመለካከት" (Attitude)
2. ፀጋዬ አረጋይ (1996 ዓ.ም) "መንግስታዊ ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሚኖራቸው አመለካከት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩትን ተውሳጦች መመርመር፡፡"
3. ድንቄሳ ዶሬሳ (1996 ዓ.ም) "በአዲስ አበባ መስተዳድር የአማርኛ ቋንቋ አፈ ፈትና በኦሮምያ ብሔራዊ ክልል ኢ-አፈ ፈት የሆኑ የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን አመለካከት ንፅፅርና ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተውሳጦች፡፡"

ከዚህ በላይ የቀረቡት ሶስቱ ጥናታዊ ጽሁፎች ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን አመለካከት ብቻ ለማወቅ የቀረቡ በመሆናቸው ይመሳሰላሉ፡፡ ነገር ግን የድንቄሳ ጥናት በተማሪዎች አመለካከት ላይ የሚያተኩር ሆኖ በአፈ ፈትና በኢ-አፈ ፈት ተማሪዎች መካከል ንጽጽርና ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተውሳጦችን ይመለከታል፡፡

ስለዚህ የእኔ ጥናት ከመጀመሪያ ሁለቱ በመጠኑ ይለያል፡፡ እነዚህ ሶስት ጥናቶች ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን አመለካከት ብቻ ለማወቅ የተደረጉ ጥናቶች በመሆናቸው ከእኔ ጥናት ጋር በመጠኑ ይቀራረባሉ፡፡ ነገር ግን የእኔ ጥናት ደግሞ ከሶስቱ የሚለይበት ባህሪ አለው፡፡ የእኔ ጥናት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለው ዝምድ ምን ይመስላል የሚለውን ይመለከታል፡፡

4ኛ እሸቱ ወንድሙ (1997 ዓ.ም) ያቀረበው ጥናት ከዚህ በላይ ከቀረቡት ከሶስቱ ጥናታዊ ጽሁፎች ይለያል፡፡ የእሱ ጥናት በኦሮምያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ባላቸው ፍለላጎትና በውጤታቸው መካከል ያለ ግንኙነት የሚል ጥናት ነው፡፡ የእሱ ጥናት በተማሪዎች ውጤት ላይ ማተኮሩ በመጠኑ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ይሁን እንጂ በእኔና በእሱ ጥናት መካከል ሰፊ ልዩነት አለ፡፡

አንደኛ የእሱ ጥናት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ምን ይመስላል የሚል ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል የሚለውን የሚመረምር ነው፡፡ ሁለተኛ የእሱ ጥናት በኦሮምያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን በሚገኙ የ10ኛ ክፍል ኢ-አፊፊት ተማሪዎች ላይ ሲሆን፣ የእኔ ጥናት ደግሞ የሚያተኩረተው በአዲስ አበባ መስተዳድር በሚገኙ የመሰናዶ ትምህርት ቤት (ቅድመ ኮሌጅ) ተማሪዎች ላይ ነው፤ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውም አማርኛ ነው፡፡ ስለዚህ በመካከላችን ሰፊ ልዩነት አለ፡፡

5ኛ ወንድወሰን በየነ (1989 ዓ.ም) «የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀዲይኛ የሆነ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከትና የፈተና ውጤት ዝምድና ምን ይመስላል» የሚል ነው፡፡

ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ተቀራራቢ ቢሆንም በመካከላችን ልዩነት አለ፡፡ አንደኛ የእሱ ጥናት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ኦሮምኛ ነው፡፡ ሁለተኛ የእሱ ጥናት ያተኮረው በቀድሞ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን የእኔ በመሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ሶስተኛ የእሱ ጥናት ከ14 ዓመት በፊት የተደረገ ጥናት ሲሆን የእኔ ግን የቅርብ ጊዜ ጥናት በመሆኑ በመካከላችን ሰፊ ልዩነት አለ፡፡

እነዚህ አጥኚዎች የተለያዩ ዓላማዎችን ይዘው የተነሱ በመሆናቸው የተለያዩ ውጤቶችን አስመዝግበዋል፡፡ ይህንንም ከጥናታዊ ጽሁፎቸው ላይ መመልከት ይቻላል፡፡፡

ከዚህ በመቀጠል አጥኚው መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተጠቀመበትን የጥናት ዘዴ እንመለከታለን፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ጥናታዊ ስራ ውስጥ መረጃዎችን ለመተንተን የተመረጠው አይነታዊ የምርምር ዘዴ ነው። ይህንን የመረጥኩበት ምክንያት አይነታዊ የምርምር ዘዴ አንድን የተከሰተ ችግር ለመፍታትና የውሳኔ ሀሳብ ላይ ለመድረስ ስለሚያስችል ነው። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የተከተልኩት ስልት ገላጭ የምርምር ዘዴን (Descriptive Research Method) ነው።

"ገላጭ ምርምር ስሙ እንደሚያመላክተው ተመራማሪው አንድን ጉዳይ አንስቶ ችግሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት አድርጎ በገለፃ መንገድ የሚያቀርብበት ነው" ያለው (2001 ፡21) በማለት ገልጿል።

ገላጭ ምርምር በጣም ጠቃሚ የሆነ መረጃ ሊገኝበት የሚችል ጥሩ የምርምር አይነት ነው። ከገላጭ ምርም ስር ከሚመደቡት መካከል ለጥናቴ ተስማሚ ሆኖ ያገኘሁት አላሽ (ቃኝ) ጥናትን ነው። አላሽ ጥናትን የመረጥኩበት ምክንያት ይህ የምርምር ዘዴ ችግሮችን ወይም ሁኔታዎችን ጠቅለል ባለ መልኩ የሚዳስስና አጠቃላይ ግንዛቤን የሚሰጥ ስለሆነ ነው። ይህንኑ ሀሳብ በመደገፍ ያለው (2001፡24) "አሰሳዊ ምርምር ያነሳውን ጉዳይ በጥልቀት ሊመረምረውና ሊያጠናው ይችላል። የችግሩን ስፋትና አስቸጋሪነት በሚገባ ሊያብራራና ሊገልጽ ይችላል። የተለዋዋጮችን ዝምድና ይተነትናል። ተመራማሪው ሳይንሳዊ ዘዴን በተመለከተ መንገድ ናሙናዎችን መርጦ የተፈለገውን መረጃ ይሰበስባል" በማለት ገልጿል።

ይህ የምርምር ዘዴ የተማሪዎችን አመለካከት ለመለካት፣ በተማሪዎች ውጤት ላይ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለመመርመር ያስችላል። ስለሆነም ለጥናቴ ተስማሚ ሆኖ ስላገኘሁት ይህንኑ የጥናት ስልት ተጠቅሚያለሁ። ይህንን ዘዴ በመከተል የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለውን ዝምድና ምን እንደሚመስል ትንታኔ ይሰጣል።

## 3.1 የናሙና አመራረጥ

### 3.1.1. የትምህርት ቤቶች አመራረጥ

በአዲስ አበባ መስተዳድር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ሁለት የመንግስት መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። በአራዳ ክፍለ ከተማ ደግሞ ሁለት የመንግስት መሰናዶ ትምህርት ቤቶች አሉ። በሁለቱ ክፍለ ከተሞች በጠቅላላው አራት የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። ከእነዚህ ውስጥ ለጥናቴ የመረጥኳቸው ሶስት የመደናዶ ትምህርት ቤቶችን ነው። አራተኛውን በጥናቱ ውስጥ አላካተትኩትም ለዚህም ምክንያቱም የአቅም ማነስና የጊዜም እጥረት የተነሳ መሆኑን መግለጽ እወዳለሁ።

ለጥናቴ የመረጥኳቸው ሶስት የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ እነሱም፡-
የካቲት አስራ ሁለትመሰናዶ ትምህርት ቤት፣ የመድሐኔዓለም መሰናዶ ትምህርት ቤት እና የዳግማዊ ምኒሊክ መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ ሁለቱ ማለትም የካቲት አስራ ሁለት መሰናዶ ትምህርት ቤትና የመድሐኔዓለም መሰናዶ ትምህርት ቤት በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሚገኙ ሲሆን የዳግማዊ ምኒሊክ መሰናዶ ትምህርት ቤት ደግሞ ባአራዳ ክፍለ ከተማ ውስጥ ይገኛል። እነዚህን ትምህርት ቤቶች የመረጥኩበት ምክንያት መረጃዎችን በቅርብ ለማግኘት ያስችለኛል ብዬ ስላመንኩ ነው። በተጨማሪም እነዚህ የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች በሁለቱ ክፍለ ከተሞች ከሚገኙት አራት የመሰናዶ ትምህር ቤቶች ሶስቱ 75% የሚሆነውን ስለሚይዙ ለጥናቱ በቂ የሆነ መረጃ ይገኛል።

### 3.1.2. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የተመሰረተባቸው የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች በአዲስ አበባ ከሚገኙት ትምህርት ቤቶች ሁሉ በእድሜ አንጋፋ ናቸው። እነዚህ ትምህርት ቤቶች በስፋትም ሆነ በሚቀበሏቸው ተማሪዎች ቁጥር የተለያዩ ናቸው።

የአጥኚው የመጀመሪያ ተግባር ተጠኚ ተማሪዎችን መለየት ነው። በመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የአስራአንደኛ እና የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ይገኛሉ። ከእነዚህ ውስጥ ለጥናቴ የመረጥኳቸው የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎችን ነው።

ለዚህም ምክንያቱ በእድሜያቸው በሰል ያሉ በእውቀት ደረጃም ቢሆን አንድ ዓመት የመሰናዶ መርሃ ግብር ትምህርት ያጠናቀቁ በመሆናችው ከአስራ አንደኛ ክፍል

ተማሪዎች የተሻሉ ናቸው። በሌላ መልኩ የአንደኛ ዓመት የኮሌጅ ትምህርት አጠናቀዋል ተብሉ ይታመናል። በሶስቱም የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች አብዛኞቹ አማርኛ ተናጋሪዎች ሲሆኑ ጥቂት ተማሪዎች አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋቸው ይጠቀማሉ።

በሶስቱም የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ብዙ በመሆኑ ከያንዳንዱ መሰናዶ ትምህርት ቤት በእጣ ንሞና አወሳሰድ (Simple random sampling) ተመርጥዋል። በዚህም የንሞና ዘዴ እያንዳንዱ ተጠኚ ሆኖ ለመመረጥ እኩል እድል አለው። በዚህ እጣ የማውጣት ዘዴ ከየካቲት አስራ ሁለት መሰናዶ ትምህርት ቤት 50፣ ከዳግማዊ ምኒሊክ መሰናዶ ትምህርት ቤት 30፣ ከመድሐኔዓለም መሰናዶ ትምህርት ቤት 40፣ በድምሩ 120 (አንድ መቶ ሃያ) ተማሪዎች በጥናቱ ተካተዋል። ከእያንዳንዱ መሰናዶ ትምህርት ቤት የተመረጡት ተማሪዎች አጠቃላይ ብዛት ከጠቅላላው የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት አንፃር አማካይ ውክልና ይኖራቸዋል ተብሉ ይገመታል። ለዝርዝሩ ሠንጠረዥ አንድን ይመልከቱ።

### 3.1.3. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በየመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የአስራ ሁለተኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን ቁጥር አነስተኛ ነው። በጥናቱ እንዲሳተፉ የተመረጡ መምህራን በየመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአስራ ሁለተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው። እነዚህ መምህራን በናሙናነት የተመረጡበት ምክንያት ከላይ እንደተገለፀው ለናሙናነት የተመረጡት የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ስልሆኑ መልሶቻቸውን ከመምህራኑ አስተያየት ጋር ማነፃፀር አስፈላጊ በመሆኑ ነው። ከየመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የተመረጡት የአማርኛ መምህራን ብዛት እንደሚከተለው ቀርቧል። በዚሁም መሰረት በየካቲት አስራ ሁለት መሰናዶ ትምህርት ቤት በአስራ ሁለተኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን ቁጥር 4፣ በደግማዊ ምኒሊክ መሰናዶ አስራ ሁለተኛ ክፍል አማርኛ የሚያስተምሩ 3፣ በመድሐኔአለም መሰናዶ በአስራ ሁለተኛ ክፍል አማርኛ የሚያስተምሩ 4 በድምር 11 መምህራን በጥናቱ ተካተዋል።

ሠንጠረዥ 1፡ በትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎችና ለናሙና የተመረጡ ተማሪዎች

| ተ.ቁ | | በትምህርት ቤት የሚኙ ተማሪዎች | | | ለናሙና የተመረጡ ተማሪዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድምር | ወ | ሴ | ድምር |
| 1 | የካቲት 12 መሰናዶ ትምህርት ቤት | 215 | 285 | 500 | 20 | 30 | 50 |
| 2 | ዳግማዊ ምኒልክ መሰናዶ ትምህርት ቤት | 220 | 180 | 400 | 20 | 10 | 30 |
| 3 | መድሐኔዓለም መሰናዶ ትምህርት ቤት | 225 | 275 | 500 | 18 | 22 | 40 |
| | ድምር | 660 | 740 | 1400 | 58 | 62 | 120 |

ለተማሪዎች ለቀረቡት ዝግ ጥያቄዎች ለያንዳንዱ ጥያቄ በመልስነት የታጩ አምስት አማራጭ መልሶች ተሰጥተዋል፡፡ ሁለቱ አዎንታዊ፣ ሁለት ደግሞ አሉታዊ ምላሽ የሚሹ ሲሆን አንዱ ከሁለቱም ወገን ያልሆነ ገለልተኛ ምላሽ የሚፈልግ ነው፡፡ ለያንዳንዱ ጥያቄ ለተሰጠው ምላሽ የሚመዘገበው ውጤት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

በአዎንታዊ የሚመለስ ከሆነ በጣም እስማማለሁ 5፣እስማማለሁ 4፣ መወሰን እቸገራለሁ 3፣ አልስማማም 2፣ ፍጹም አልስማማም 1 የሚል ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ ጥያቄው አሉታዊ ምላሽ የሚሻ ከሆነ በጣም እስማማለሁ ~~በጣም እስማማለሁ~~ 1፣እስማማለሁ 2፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 3፣ አልስማማም 4፣ ፍጹም አልስማማም 5 የሚል ነጥብ ተሰጥቶታል፡፡

የማጠቃለያ ውጤቱ አንድ ተማሪ ወይም መምህር ለሁሉም ዝግ ጥቂዎች የሰጠው/ችው/ ምላሽ አማካይ ከሶስት በላይ ከሆነ አዎንታዊ ከሶስት በታች እየቀነሰ ከሄደ አሉታዊ እንደሚሆን ይሰላል፡፡ ከሁለቱ መካከል ላይ ሶስት ከሆነ ግን ተማሪው ያለው አመለካከት ገለልተኛ ይሆናል፡፡ በመጨረሻም በአስራ ሁለተኛ ክፍል የአንደኛ ወሰነ ትምህርት ፈተና ያገኘው/ችው/ ውጤት ተቀምሮና ተሰልቶ በሁለቱ መካከል ያለው ትስስር ይቀርባል፡፡ በዚህ መሰረት በጥናቱ የተካተቱት በ2003 ዓ.ም አስራ ሁለተኛ ክፍል የሚማሩ የመሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ውጤታቸው ከማርክ ሊስት በጥንቃቄ ተለቅሞ ከተወሰደ በኋላ ከተማሪው አመለካከት ውጤት ጋር ተጣምሮ ይቀርባል፡፡

## 3.2. መረጃ መሰብሰቢ መሳሪያዎች

### 3.2.1. መጠይቆች

ይህ ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ከሚጠቀምባቸው መሳሪያዎች አንዱ መጠይቅ ነው። መጠይቆቹ ሲዘጋጁ ቀደምት ጥናቶችን ተመልክቻለሁ። በነዚህ ጥናቶች የቀረቡትን የተወሰኑ ጥያቄዎችን በማሻሻል፣ የራሴን ጥያቄዎች በመጨመር ለጥናቱ በሚስማማ መልኩ እንዲዘጋጁ ተደርጓል። ለተማሪዎቹ በሊክርት አፃፃፍ ስልት የተዘጋጁ መጠይቆች ቀርበዋል። መጠይቆቹ ለተማሪዎቹ ከመበተናቸው በፊት ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን አመለካከት ሊለኩ ይችላሉ ወይ የሚለውን ለማረጋገጥ የጥናቱ አማካሪና ሁለት ባለሙያዎች ተመልክተውት የማሻሻያ ሀሳብ አክለውበታል። የመጠይቆቹ አዘገጃጀት ቀደም ሲል ለተማሪዎች በቀረበው ክፍት መጠይቅ ምላሽ ላይ የተመሰረተ ነው። ጥያቄዎቹ አመለካከትን መለካት እንዲችሉ በጥንቃቄ ታስቦባቸው የተዘጋጁ ናቸው።

#### 3.2.1.1. የተማሪዎች መጠይቅ

ለተማሪዎቹ የቀረበው መጠይቅ 39 ጥያቄዎችን የያዘ ነው። የመጠይቆቹ የትኩረት አቅጣጫ ለመምህሩ፣ ለተማሪውና ለመማሪያ መጽሐፉ፣ ለማስተማሪያው ዘዴ፣ ለቋንቋውና ለትምህርቱ ያለው አመለካከት እና የፈተና ውጤትን የሚጠይቁ ናቸው። በሌላ መልኩ ደግሞ የተማሪ ወላጆች፣ እኩዮችና ህብረተሰቡ በተማሪው አመለካከት ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ ለመለካት የሚያስችሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል። በተቻለ መጠን ጥያቄዎቹ ሚዛናዊ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል። ይህም የሆነበት ምክንያት የአንዱ ተላውጦ ጥያቄ በጣም በዝቶ የሌላው ካነሰ የሚሰጠው ምላሽ ላይ ተጽዕኖ እንዳያደርስ በማሰብ ነው።

በመጠይቁ ውስጥ አምስት የሚሆኑ ተላውጦች ሲገኙ ለእያንዳንዱ ተላውጦ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለሶስቱ መሰናዶ ትምህርት ቤቶች፣ ተማሪዎቹ እንዲሞሉ የተበተነው 140 የጽሁፍ መጠይቅ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 20 መጠይቆች በአሞላል ስህተት የተበላሹ ሆነው ተገኝተዋል። ስለዚህ በትክክል የተሞሉት 120 መጠይቆች ናቸው። ጥያቄዎቹ አዎንታዊና አሉታዊ ሀሳቦችን የያዙ ሲሆኑ በሙሉ ዝግ

ጥያቄዎች ናቸው። ጥያቄዎቹ የተማሪዎቹን አመለካከት ወደ አንድ አቅጣጫ እንዳይመሯቸው ሆን ተብሎ ተዘበራርቀው ቀርበዋል።

ለተማሪዎች ለቀረቡት ዘገ ጥያቄዎች ለያንዳንዱ ጥያቄ በመልስነት የታጩ አምስት አማራጭ መልሶች ተሰጥተዋል። ሁለቱ አዎንታዊ፣ ሁለት ደግሞ አሉታዊ ምላሽ የሚሹ ሲሆን አንዱ ከሁለቱም ወገን ያልሆነ ገለልተኛ ምላሽ የሚፈልግ ነው። ለያንዳንዱ ጥያቄ ለተሰጠው ምላሽ የሚመዘገበው ውጤት እንደሚከተለው ይሆናል።

የቀረበው ጥያቄ በአዎንታዊ መልክ የሚመለስ ከሆነ ውጤቱ፣ በጣም እስማማለሁ 5፣ እስማማለሁ 4፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 3፣ አልስማማም 2፣ ፍጹም አልስማማም 1 የሚል ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ ጥያቄው አሉታዊ ምላሽ የሚሻ ከሆነ ውጤቱ የሚከተለው ይሆናል። በጣም እስማማለሁ 1፣ እስማማለሁ 2፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 3፣ አልስማማም 4፣ ፍጹም አልስማማም 5 የሚል ነጥብ ተሰጥቶታል።

የማጠቃለያ ውጤቱ አንድ ተማሪ ለሁሉም ዘገ ጥቂዎች የሰጠው/ችው/ ምላሽ አማካይ ከሶስት በላይ ከሆነ አዎንታዊ ከሶስት በታች እየቀነሰ ከሄደ አሉታዊ እንደሚሆን ይሰላል። ከሁለቱ መካከል ላይ ሶስት ከሆነ ግን ተማሪው ያለው አመለካከት ገለልተኛ ይሆናል። በመጨረሻም የአንደኛ ወሰነ ትምህርት ፈተና ውጤት ተሰልቶ በሁለቱ መካከል ያለው ትስስር ይቀርባል። ስለዚህ የ2003 ዓ.ም የአስራ ሁለተኛ ክፍል የአንደኛ ወሰነ ትምህርት ፈተና ውጤት ከትምህርት ቤቱ ሪከርድ ክፍል ከማርክ ሊስቱ በመልቀም በጥናቱ የተካተቱ ተማሪዎችን ውጤት ተመዝግቧል፤ ማርክሊስቱ ትክክለኛ ለመሆኑ በትምህርት ቤቱ ማህተም ተረጋግጧል። በዚህ መሰረት በጥናቱ የተካተቱት በ2003 ዓ.ም አስራ ሁለተኛ ክፍል የሚማሩ የመሰናዶ ትምህርት ቤት የተማሪዎች ውጤት ከማርኩሊስቱ በጥንቃቄ ተለቅሞ ከተወሰደ በኋላ ከተማሪው አመለካከት ውጤት ጋር ተጣምሮ ይቀርባል።

### 3.2.1.2. የመምህራን ቃለ መጠይቅ

በዚህ ጥናት በመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአስራ ሁለተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቁጥር በጣም አነስተኛ በመሆኑ ከመምህራኑ የተማሪዎችን አመለካከት በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ ቃለ-መጠይቅን (interview) ተጠቅሚያለሁ። ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን ስም በኮድ ተቀምጧል።

በዚህ ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች ብዛት አስራ ሁለት ሲሆን መረጃዎቹን በመቅረጸ ድምፅ በመቅዳት አያይዞም ወደ ጽሑፍ በመቀየር በመረጃነት ተተንትነዋል። ጥያቄዎቹም በአባሪነት ተያይዘዋል። በቃለ-መጠይቁ የተሳተፉት በሶስቱም መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአስራ ሁለተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው። በተጠኚ ትህርት ቤቶች ውስጥ ሁለት ሁለት መምህራን ሲሆኑ አምስት ወንድ መምህራንና አንድ ሴት መምህርት በድሩ ከስድስት መምህራን ጋር የቃል መጠይቅ ተካሂዷል። ከአንድ ተጠኚ መምህር የተደረገው ቃለ-መጠይቅ 25 ደቂቃ ያህል ወስዷል። ለጠቅላላው ተጠኚዎች የወሰደው ጊዜ ሲሰላ 150 ደቂቃ ወይም 2 ሠዓት ተኩል ነው። ሰንጠረዥ 2 ይመልከቱ።

ሠንጠረዥ 2፡ በመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በቃለ-መጠይቅ የተሳተፉ የአስራ ሁለተኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን

| ተ.ቁ | የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች | በመሰናዶ ትምህርት የአማርኛ መምህራን | | | የትምህርት ደረጃ | | | የአገልግሎት ዘመን | | | በቃለ-መጠይቅ የተሳተፉ የአማርኛ መምህራን | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድ | መጀመሪያ ዲግሪ | ሁለተኛ ዲግሪ | ድ | 10-15 | 16-20 | ከ20 በላይ | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | የካቲት አሥራ ሁለት መሰናዶ ትምህርት ቤት | 4 | - | 4 | 1 | 1 | 2 | - | 2 | 2 | 2 | - | 2 |
| 2 | ዳግማዊ ምኒልክ መሰናዶ ትምህርት ቤት | 3 | - | 3 | 2 | - | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | - | 2 |
| 3 | መድኃኔዓለም መሰናዶ ትምህርት ቤት | 3 | 1 | 4 | 2 | - | 2 | - | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 |
| | ድምር | 10 | 1 | 11 | 5 | 1 | 6 | 1 | 5 | 6 | 5 | 1 | 6 |

### 3.2.2. የክፍል ምልከታ

በመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚካሄደውን የክፍል ውስጥ የትምህርት እንቅስቃሴ ለመመልከት ስለ መምህሩ የማስታማር ዘዴ ስለ ተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበል ለመታዘብ ምልከታ፣ አንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ በምልከታውም ወቅት መረጃዎች የሚሰበሰቡት አስቀድሞ በተዘጋጀ ዝርዝር የመከታተያ ነጥቦች (CheckList) አማካኝነት ለማካሄድ ተሞክሯል፡፡

በእያንዳዱ መሰናዶ ትምህርት ቤት ሁለንብ ሁለት ሁለት ጊዜ በድምሩ ስድስት ጊዜ የክፍል ምልከታ ተደርጓል፡፡ ከተገኘው መረጃ በመነሳት በተለይ በመምህራን የክፍል ቁጥጥርና የትህርት አሰጣጥ እንዲሁም በተማሪዎች የክፍል ተሳትፎ ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡

## 4. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናታዊ ሥራ ውስጥ መረጃዎችን ለመተንተን የተመረጠው አይነታዊ ምርመር ዘዴ ነው፡፡ ይህንን የመረጥኩበት ምክንያት አይነታዊ የምርምር ዘዴ አንድን የተከሰተ ችግር ለመፍታትና የውሳኔ ሃሳብ ላይ ለመድረስ ስለሚያስችል ነው፡፡ ይንን ተግባራዊ ለማድረግ የተከተልኩት ስልት ገላጭ የምርመር ዘዴን (Descriptive Research Method) ነው፡፡ ገላጭ ምርምር ስሙ እንደሚያመለክተው

አንድ አጥኚ አንድን ጉዳይ አንስቶ ችግሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ አስገብቶ በገለፃ መልክ የሚያቀርብበት ዘዴ ነው። ገላጭ ምርምር "ችግሩ ምን ያህል ሰፊ ነው? መጠኑ ምን ያህል ነው?" የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ያስችላል። ያለው (2001፣ 21) ሲገልፅ "የተማሪዎችን ውጤት፣ አመለካከት፣ ባህሪ ወይም ሌሎች ተለዋዋጮችን በተናጠል አልያም በቡድን በመውሰድ ምን እንደሚመስሉ ስዕላዊ በሆነ መንገድ ያብራራል" በማለት አስረድቷል።

የገላጭ ምርምርን ባህሪ ዳንኤልና ሌሎች (1994፣ 17) እንደሚከተለው ያብራራሉ፡-

- ገላጭ ምርምር የአንድን ጉዳይ ወይም ክስተት ወቅታዊ ሁኔታን በግልፅ በማሳየት ላይ ያተኩራል፤
- በተጨባጭ መረጃዎች ላይ በመመስረት ትክክለኛ መደምደሚያዎችን ይሰጣል፤
- እውነታን በመፈለግ ላይ ብቻ ሳይሆን ጠቃሚ የሆኑ የዕውቀት መርሆችንና ለችግሮችም መፍትሄ በመፈለግ ላይ ያተኩራል፤
- መረጃ መሰብሰብ ብቻ ሳይሆን መለካት፣ መመደብ፣ መተንተን፣ ማነፃፀርና መተርጎምን ያካትታል።

ከዚህ በላይ የቀረበው የገላጭ ምርምር ባህሪያት እኔ ለመረጥኩት የጥናት ርዕስ ተስማሚ ሆኖ ስላገኘሁት ይህንን የምርምር ዘዴ ተጠቅሜያለሁ። በገላጭ ምርምር ስር የሚመደቡ ብዙ አይነት ምርምሮች አሉ። ለምሳሌ አሰሳ (ቃኚ) ጥናት፣ ውስን ጥናትና ተንታኝ ወይም አዛማጅ ጥናት ወዘተ... የመሳሰሉት ናቸው። ከነዚህ ከተጠቀሱት የምርምር ስልቶች ውስጥ ለጥናቴ ተስማሚ ሆኖ ያገኘሁት አሳሽ ጥናት ስለሆነ ይህንኑ ስልት ተከትያለሁ። አሳሽ ጥናትን የመረጥኩበት ምክንያት ይህ የምርምር ዘዴ ችግሮችን ወይም ሁኔታዎችን ጠቅለል ባለ መልኩ የሚዳስስና አጠቃላይ ግንዛቤን የሚሰጥ ስለሆነ ነው። ይህ የምርምር ዘዴ የተማሪዎችን አመለካከት ለመለካት፣ በተማሪዎች ውጤት ላይ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመመርመር ያስችላል። ስለሆነም ለጥናቴ ተስማሚ ሆኖ ስላገኘሁት ይህንን የጥናት ስልት ተጠቅሜአለሁ። ይህ ዘዴ የመሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለውን ዝምድና ምን

እንደሚመስል ትንታኔ ይሰጣል። ቃለ መጠይቅ፣ የጽሁፍ ምልከታ እና የተማሪዎች ውጤት፤ በመቀጠልም ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች ለስራው አጋዥ በሆነ መንገድ ከተተነተነ በኋላ በውጤታቸው መካከል ያለው ዝምድ ምን እንደሚመስል ለማረጋገጥ በT-ቴስት ቀመር ይጠቀማል። ከዚያም በመቀጠል የተማሪዎችን አመለካከት ለማወቅ በጽሁፍ መጠይቅ፣ በቃለ-መጠይቅ፣ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ከተተነተኑ በኋላ የተማዎችን ውጤት በጥንቃቄ ከማርክ-ሊስት በመልቀም በT-ቴስት ስሌት ይተነተናል። ከጥናቱ የተገኘውን ውጤትም ያመላክታል። በተጨማሪም የመፍትሄ ሃሳብ ይጠቁማል።

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃዎች ትንተና ውጤት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ ተካትቷል። ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት፣ ለመምህራን ያላቸው አመለካከት፣ ለመማሪያ መጽሐፉ ያላቸው አመለካከት፣ ለወላጆቻቸውና ለጓደኞቻቸው ያላቸው አመለካከት እንዲሁም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የፈተና ውጤታቸው ምን እንደሚመስል በዝርዝር ይቀርባል።

### 4.1. ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ የአመለካከት ውጤትና ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የተማሪዎች አመለካከት ከፈተና ውጤታቸው ጋር ያለውን ዝምድና ማረጋገጥ ነው። ከታለመው ውጤት ላይ ለመድረስ አጥኚው የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ተጠቅሟል። ከነዚህ መሳሪያዎች ዋነኛው የጽሁፍ መጠይቅ ሲሆን አጋዥ መሳሪያ የሆኑት ደግሞ የቃል መጠይቅና የክፍል ምልከታ ናቸው።

በዚሁ መሰረት በምዕራፍ ሶስት እደተገለፀው ሰላሳ ዘጠኝ ጥያቄዎችን ያዘለ መጠይቅ 120 የመሰናዶ ተማሪዎች እንዲሞሉ ተደርጓል። ከጽሁፍ መጠይቁ በተገኘው መረጃ መሰረት የአንደኛ ወሰነ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት ከየትምህርት ቤቶቹ ተሰብስቦ ውጤቱ ቀርቧል። ከዚሁ ጋር እያንዳንዱ ተማሪ ያስመዘገበው የአመለካከት ውጤት ተቆጥሮ ተመዝግቧል። የተገኘው ውጤትም በአማካይና በመቶኛ ተሰልቷል። ለስድስት የመሰናዶ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቃለ መጠይቅ ተደርጎ የተገኘው መረጃ ተካትቷል። የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውኑን ለማየት ምልከታ በማካሄድ መረጃዎች ተሰብስበዋል። ከዚህ በማስከተል መረጃዎቹ በክፍል በክፍላቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 4.1.1. የመላሾች አጠቃላይ ሁኔታ

ሠንጠረዥ 3፡ የተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ

| ትምህርት ቤት | ዕድሜ | | | ድምር | ፆታ | | ድምር | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 16-17 | 18-19 | ከ19 በላይ | | ወ | ሴ | | አማርኛ | ኦሮምኛ | ትግርኛ | |
| የካቲት 12 | 12 | 35 | 3 | 50 | 20 | 30 | 50 | 48 | 2 | 0 | 50 |
| ዳግማዊ ሚኒሊክ | 4 | 23 | 3 | 30 | 20 | 10 | 30 | 24 | 5 | 1 | 30 |
| መድኃኔ ዓለም | 6 | 30 | 4 | 40 | 18 | 22 | 40 | 37 | 3 | 0 | 40 |
| ድምር | 22 | 88 | 10 | 120 | 58 | 62 | 120 | 109 | 10 | 1 | 120 |

ከሠንጠረዥ 2 መረዳት እንደሚቻለው መጠይቁን የሞሉት ሃምሳ ስምንት (58) ወንዶች እና ስልሳ ሁለት (62) ሴቶች ናቸው፡፡ ሁለቱን ፆታዎች ከእድሜ አንፃር ስንመለከት ደግሞ ከ16-17 (18.3%) ከ18-19 (73.3%) ከ19 በላይ (8.3%) የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ናቸው፡፡ ከዚህ የምንረዳው በጥናቱ የተካተቱት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ (73.3%) ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ተማሪዎች በእድሜያቸው በሰል ያሉ በመሆናቸው ለጥናቱ ጠቃሚ መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ ከፆታ አንፃር ስንመለከታቸው የወንዶች እና የሴቶች ተማሪዎች ቁጥር ተቀራራቢ መሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡ ስለዚህ የጾታ ተዋጽኦ ተመጣጣኝ በመሆኑ የጥናቱ ውጤት ወደ አንድ ወገን እንዳያዘነብል የራሱ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ የጾታ ልዩነት በአመለካከት ላይ ምንም ልዩነት አላሳየም፡፡

በጥናቱ ከተሳተፉት 120 ተማሪዎች በአማርኛ አፋቸውን የፈቱት 109 (90.8%) ተማሪዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አፋቸውን የፈቱት በአማርኛ ቋንቋ መሆኑን መረጃዎቹ ያመላክታሉ፡፡

ተማሪዎቹ ለቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት "አዎንታዊ ወይም አሉታዊ" መሆኑንና ይህም አመለካከት በተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ላይ ተፅዕኖ እንደሚኖረው በምዕራፍ ሁለት ላይ ተገልጿል፡፡ (Cronbach, 1954) የዚህ ጥናት ዓላማ በጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎች ለታላሚው ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል ለማወቅ ከተማሪዎች በተገኘው መረጃ ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው መሰረት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

በጥናቱ ውስጥ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት ዋንኛው ተላውጦ ነው። ይህንን ተላውጦ ለመለካት አስር በአዎንታዊ ምላሽ፣ ስምንት ደግሞ በአሉታዊ ምላሽ የተዘጋጁ ጥያቄዎች ቀርበዋል። በዚህም መሰረት በሰንጠረዥ 2 ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት እንመለከታለን።

### 4.1.2. ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል በዝርዝር ይቀርባል። ይህ ሰንጠረዥ በ3 ተከፍሎ ሰንጠረዥ 4ሀ፣ ሰንጠረዥ 4ለ፣ ሰንጠረዥ 4ሐ፣ ተብሎ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 4ሀ፡ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | % | 4 | % | 3 | % | 2 | % | 1 | % | |
| 1 | ተማሪዎችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | |
| 1.1 | የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት በጣም ስለምወደው ክፍለ ጊዜውን በጉጉት እጠብቃለሁ። | 34 | 28.3 | 60 | 50 | 19 | 15.8 | 5 | 4.2 | 2 | 1.7 | 3.99 |
| 1.2 | ግድ ሆኖብኝ ነው እንጂ የአማርኛን ቋንቋ መማር አልፈልግም። | 2 | 1.7 | 10 | 8.3 | - | - | 38 | 31.7 | 70 | 58.3 | 4.01 |
| 1.3 | አማርኛ በሁለተኛ ደረጃ የሁሉም ትምህርቶች ማስተማሪያ ቢሆን እመርጣለሁ። | 22 | 18.3 | 16 | 13.3 | 22 | 18.3 | 38 | 31.7 | 22 | 18.4 | 3.18 |
| 1.4 | የአማርኛ ቋንቋ ወደ ከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና ባለመካተቱ በጣም ያናድደኛል። | 67 | 55.8 | 10 | 8.3 | 12 | 10.0 | 14 | 11.7 | 17 | 14.2 | 3.50 |
| 1.5 | የአማርኛ ቋንቋን እንደሌሎች የትምህርት አይነቶች በእኩል አይን እመለከተዋለሁ። | 50 | 41.7 | 36 | 30.0 | - | - | 22 | 18.3 | 12 | 10 | 3.75 |
| 1.6 | የአማርኛ ትምህርቱን በመቀጠል ደራሲና ጋዜጠኛ መሆን እፈልጋለሁ። | 31 | 25.8 | 24 | 20.0 | 8 | 6.7 | 36 | 30.0 | 21 | 17.5 | 3.07 |
| 1.7 | በአማርኛ ክፍለ ጊዜ በትምህርቱ መሳተፍ አልፈልግም። | 17 | 14.2 | 7 | 5.8 | 2 | 1.7 | 24 | 20.0 | 70 | 58.3 | 4.03 |

- መግለጫ

አዎንታዊ ለሆነ የአመለካከት ውጤት፡-
በጣም እስማማለሁ - 5 ነጥብ
እስማማለሁ - 4 ነጥብ
ለመወሰን እቸገራለሁ - 3 ነጥብ
አልስማማም - 2 ነጥብ
ፍጹም አልስማማም - 1 ነጥብ

አሉታዊ ለሆነ የአመለካከት ውጤት፡-
በጣም እስማማለሁ - 1 ነጥብ
እስማማለሁ - 2 ነጥብ
ለመወሰን እቸገራለሁ - 3 ነጥብ
እስማማለሁ - 4 ነጥብ
ፍጹም አልስማማም - 5 ነጥብ

ከሰንጠረዥ 4 እንደምንረዳው ተማሪዎች በተራ ቁጥር 1.1 ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ 34 (28.3%) በጣም እስማማለሁ፣ 60 (50%) እስማማለሁ፣ 19 (15.8%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 5 (4.2%) አልስማማም፣ 2 (1.7%) በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ ባጠቃላይ 94 (78.5%) ተማሪዎች አዎንታዊ፣ 7 (5.9%) የሚሆኑት ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥቡ 3.99 ነው፡፡ ስለዚህ አብዛኛዎቹ የመሰናዶ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት እንደሚወዱ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘውም ምላሽ ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ጥሩ አመለካከት እንዳላቸው መምህራንም ገልፀዋል፡፡

ለምሳሌ መምህር 1፡ ተማሪዎች የአማርኛን ቋንቋ ትምህርተ በሚገባ ይከታተላሉ መምህሩ ትምህርቱን ሳቢና ማራኪ አድርጎ ካቀረበው ተማሪዎች ትምርቱን በጥሩ ሁኔታ ይከታተላሉ፡፡
ምልከታ በተካሄደበትም ወቅት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ መምህሩ ጥያቄ ሲጠይቅ አብዛኙዎቹ ተማሪዎች እጃቸውን በማውጣት ጥያቄ ለመመለስ ሲሞክሩ፣ ትምህርቱንም በንቃት ሲከታተሉ ለማየት ተችሏል፡፡

በተራ ቁጥር 1.2 በሰንጠረዥ 4 ለቀረበው ጥያቄ 2 (1.7%) በጣም እስማማለሁ፣ 10 (8.3%) እስማማለሁ፣ 38 (31.7%) አልስማማም፣ 70 (58.3%) በጣም አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥቡ 4.01 ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን ጥያቄ አብዛኞዎቹ የመሰናዶ ተማሪዎች 108 (90%) ተቃውመውታል፡፡ ተማሪዎች ግድ ሆኖባቸው ሳይሆን በፍላጎታቸው ትምህርቱን እንደሚከታተሉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለመምህራን በቀረበው ቃለ መጠይቅም ይህንኑ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ አብዛኞቹ መምህራን በሰጡት ቃለ መጠይቅ ተማሪዎች በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የንቃ ተሳትፎ እደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

ለምሳሌ መምህር 4፡ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች በፀጥታ ትምህርቱን ይከታተላሉ፡፡ የክፍል ስራ ሲሰጣቸው በደስታ ይሰራሉ በማለት አስተያየቱን ሰጥቷል፡፡

መምህር 5፡ ምንም እንኳ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮሌጅ መግቢያ ፈተና ላይ ባይካተትም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ጥሩ ተሳትፎ

ያደርጋሉ። ይሁን እንጂ ጥቂት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መማር የማይፈልጉ ተማሪዎች አሉ በማለት ገልፀዋል።

በሶስቱም መሰናዶ ትምህርት ቤት በተካሄደው ምልከታ ተማሪዎች መምህራን ለሚያቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ ያልገባቸውን፣ ሲጠይቁ ለማየት ተችሏል። የተሰጣቸውን የክፍል ስራ ሰርተዋል። በእርግጥ ጥቂት ተማሪዎች ወሬ ሲያወሩ ተስተውለዋል፤ አብዛኞቹ ተማሪዎች ግን ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ከፍተኛ ነው። ስለዚህ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በግዴታ ሳይሆን በራሳቸው ፍላጎት የሚማሩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

በተራ ቁጥር 1.3 ሰንጠረዥ 4 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 22 (18.3%) በጣም እስማማለሁ፤ 16 (13.3%) እስማማለሁ፤ 22 (18.3%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 38 (31.7%) በጣም አልስማማም፤ 22 (18.4%) አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 3.18 ነው። ይህን ጥያቄ ከግማሽ በላይ 60 (50.1%) የሚሆኑ ተማሪዎች ተቃውመውታል። ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሁሉም ትምህርቶች ማስተማሪያ እንዲሆን አለመፈለጋቸው መረጃው አመልክቷል። ከዚህ የምንረዳው ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ አመለካከት ቢኖራቸውም የአማርኛ ቋንቋ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሁሉም የትምህርት አይነቶች ማስተማሪያ እንዲሆን አለመፈለጋቸው ታውቋል።

በተራ ቁጥር 1.4 በሰንጠረዥ 4 ለቀረበው ጥያቄ 67 (55.8%) በጣም እስማማለሁ፣ 10 (8.3%) እስማማለሁ፤ 12 (10.0%) ለመወሰን እቸገራለሁ፤ 14 (11.7%) አልስማማም፤ 17 (14.2%) በጣም አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 3.80 ነው። ስለዚህ 64.1% አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 25.9% ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህ የምንረዳው ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ወደ ከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና ላይ መካተት አለበት የሚል ፍላጎት እንዳላቸው ጥናቱ አረጋግጧል። በተራ ቁጥር 1.4 ላይ ለቀረበው ጥያቄ ተማሪዎቹም ሆኑ መምህራን የሰጡት መልስ ተደጋጋፊ ሆኖ ተገኝቷል። በጥናቱ የተካተቱት ሁሉም መምህራን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮሌጅ ፈተና ላይ ባለመካተቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የነበራቸው ፍላጎት እየቀነሰ መጥቷል በማለት አስተያየታቸውን አቅርበዋል።

ለምሳሌ መምህር 2፡ "የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮሌጅ መግቢያ ፈተና ላይ ባለመካተቱ ተማሪዎች የአማርኛን ቋንቋ ትምህርት ለመማር የነበራቸው ፍላጎት እየቀነሰ ሄዷል። ይህ በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ነው። የአማርኛ ቋንቋ አብዛኛውን የሀገራችን ህዝብ በጋራ የሚያግባባ ቋንቋ ነው። ስለዚህ በኮሌጅ መግቢያ ፈተና ላይ መካተት አለበት። ትምህርት ሚኒስቴርም ሆነ መንግስት ትኩረት ሊሰጡት ይገባል፣ በማለት አስተያየቱን አቅርቧል።" ስዚህም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮሌጅ መግቢያ ፈተና ላይ መካተት ይገባዋል።

በተራ ቁጥር 1.5 በሰንጠረዥ 4 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 50 (41.7%) በጣም እስማማለሁ፣ 36 (30.0%) እስማማለሁ፣ 22 (18.3%) አልስማማም፣ 12 (10.0%) በጣም አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 3.75 ነው። በዚህ ሃሳብ ላይ 71.7% አዎንታዊ 28.3% አሉታዊ ምላሽ ተሰጥቷል። ስለዚህ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 71.7% የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን እንደ ሌሎች ትምህርት አይነቶች በእኩል አይን እንደሚመለከቱት ጥናቱ አመልክቷል። ለመምህራን በቀረበው ቃለ መጠይቅም ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በንቃት መሳተፋቸው ተገልጿል።

ለምሳሌ መምህር 5፡ "በኔ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ ይከታተላሉ። ጥያቄ ስጠይቃቸው ይመልሳሉ። የአማርኛን ትምህርት እንደሌሎቹ የትህርት አይነቶች በእኩል አይን ይመለከቱታል በማለት አስተያየቱን ሰጥቷል።" ይህም የሚያሳየን ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ጥሩ አመለካከት ስላላቸው እንደሌሎቹ የትምህርት አይነቶች እኩል ትኩረት ይሰጡታል ማለት ነው።

በተራ ቁጥር 1.6 በሰንጠረዥ 4 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 31 (25.8%) በጣም እስማማለሁ፣ 24 (20.0%) እስማማለሁ፣ 8 (6.7%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 36 (30.0%) አልስማማም፣ 21 (17.5%) በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል። አማካይ ነጥቡ 3.07 ነው። ስለዚህ 45.8% አዎንታዊ፣ 47.5% አሉታዊ ምላሽ ተሰጥቷል። ስለዚህ የምንረዳው ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ደራሲና ጋዜጠኛ መሆን እንደማይፈልጉ መረጃው አረጋግጧል።

በተራ ቁጥር 1.7 በሰንጠረዥ 4 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 17 (14.2%) በጣም እስማማለሁ፣ 7 (5.8%) እስማማለሁ፣ 2 (1.7%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 24

(20.0%) አልስማማም፣ 70 (58.3%) በጣም አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 4.03 ነው። ስለዚህ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 78.3% ጥያቄውን በመቃወም ምላሽ ሰጥተዋል።

ከዚህ የምንገነዘበው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ መሳተፍ እንደሚፈልጉ ጥናቱ አረጋግጧል። ለመምህራን በቀረበው ቃለ መጠይቅም አብዛኛዎቹ መምህራን ተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ከፍተኛ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል።

ለምሳሌ መምህር 2፡ "እኔ በማስተምረው ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በፈተና ጥሩ ውጤት ያስመዘግባሉ በማለት ገልፀዋል።"

መምህር 4፡ "የአብዛኛዎቹ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት ጥሩ ነው። አማርኛ በኮሌጅ መግቢያ ፈተና ላይ እንደማይካተት ያውቃሉ፤ ነገር ግን በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ማለፊያ ማርክ ያመጣሉ።"

አብዛኛዎቹ የአማርኛ መምህራን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ገልፀዋል። ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮሌጅ መግቢያ ፈተና ላይ ቢካተት የመሰናዶ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውጤት ያስመዘግባሉ። በአጠቃላይ ለቀረበው ጥያቄ ከተማሪዎቹ የቀረበው ምላሽ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው ምላሽና ከምልከታ የተገኘው ውጤት ተስማሚ ሆኖ ተገኝቷል።

ሠንጠረዥ 4 ለ፡

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | % | 4 | % | 3 | % | 2 | % | 1 | % | |
| 1.8 | የአማርኛ ቋንቋ ለኮሌጅ መግቢያ ፈተና ቢካተት ከፍተኛ ውጤት አመጣለሁ፡ | 67 | 55.8 | 30 | 25.0 | 10 | 8.3 | 5 | 4.2 | 8 | 6.7 | 4.19 |
| 1.9 | በሳምንት ለአማርኛ የተመደበው ክፍለ ጊዜ በጣም ስለሚያንስ ክፍለ ጊዜ ቢጨመርለት ይሻላል። | 24 | 20.0 | 26 | 21.7 | 16 | 13.3 | 29 | 24.2 | 25 | 20.8 | 3.04 |
| 1.10 | የአማርኛ ቋንቋ ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና ከሚሰጡት ትምህርቶች እንደ አንዱ ሆኖ መሰጠት አለበት። | 69 | 57.5 | 33 | 27.5 | - | - | 12 | 10.0 | 6 | 5.0 | 4.23 |
| 1.11 | የአማርኛ ቋንቋ ከእንግሊዘኛ ባልተናነሰ የማስተማሪያ ቋንቋ ሊሆን ይችላል። | 62 | 51.7 | 31 | 25.8 | 10 | 8.3 | 11 | 9.2 | 6 | 5.0 | 4.10 |

በተራ ቁጥር 1.8፡ በሠንጠረዥ 4 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 67 (55.8%) በጣም እስማማለሁ፣ 30 (25.0%) እስማማለሁ፣ 10 (8.3%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 5 (4.2%) አልስማማም፣ 8 (6.7%) በጣም አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 4.19 ነው። ስለዚህ 80.8% አዎንታዊ፣ 10.9% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህ የምንገነዘበው አብዛኞዎቹ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለኮሌጅ መግቢያ ፈተና ላይ ቢካተት ከፍተኛ ውጤት እንደሚያመጡ ገልፀዋል። ከመምህራን ጋር የተደረገው ቃለ መጠይቅ ይህንኑ አረጋግጧል።

ለምሳሌ መምህር 2፡ "እኔ በማስተምረው ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በፈተና ጥሩ ውጤት ያስመዘግባሉ።"

መምህር 4፡ የአብዛኛዎቹ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት ጥሩ ነው። አማርኛ በኮሌጅ መግቢያ ፈተና ላይ እንደማይካተት ያውቃሉ፤ ነገር ግን በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከፍተኛ ውጤት ያመጣሉ በማለት አስተያየቱን አቅርቧል።

መምህር 3፡ "አብዛኞቹ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የፈተና ውጤታቸው ጥሩ አይደለም። ዝቅተኛ ማርክ ያመጣሉ ምክንያቱም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮሌጅ መግቢያ ፈተና ላይ እንደማይካተት ስለሚያውቁ ትምህርቱን አያጠኑትም"። ከዚህ መምህር በስተቀር ሌሎቹ ተጠኚ መምህራን በሙሉ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ገልፀዋል። ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮሌጅ መግቢያ ፈተና ላይ ቢካተት የመሰናዶ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውጤት ያስመዘግባሉ።

በተራ ቁጥር 1.9 በሠንጠረዥ 4 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 24 (20.0%) በጣም እስማማለሁ፣ 26 (21.1%) እስማማለሁ፣ 16 (13.3%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 29 (24.2%) ደግሞ አልስማማም፣ 25 (20.8%) በጣም አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 3.04 ነው። ለቀረበው ጥያቄ 41.7% አዎንታዊ፣ 45.0% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህ የምንረዳው ለቀረበው ጥያቄ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ የተሰጠው ምላሽ ተቀራራቢ ሆኖ ተገኝቷል። ከተማሪዎቹ መካከል ግማሽ ያህሉ ለአማርኛ ትምህርት የተመደበው ክፍለ ጊዜ በቂ ነው ሲሉ ግማሽ ያህሉ ደግሞ ለአማርኛ ትምህርት የተመደበው ክፍለ ጊዜ ስለሚያንስ ቢጨመር ይሻላል የሚል

መልስ ሰጥተዋል። ከመምህራንም ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ በሳምንት ለአማርኛ ቋንቋ የተመደበው ክፍለ ጊዜ በቂ አይደለም በማለት አብዛኛዎቹ መምህራን መልስ ሰጥተዋል።

መምህር 2፡ "ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሳምንት የተመደበው ክፍል ጊዜ በቂ አይደለም።"

መምህር 4፡ "ለአማርኛ ቋንቋ የተመደበው ክፍል ጊዜ በቂ አይደለም። በመጽሐፉ ውስጥ በርካታ ይዘቶች አሉ። ይህ ለመጨረስ ክፍለ ጊዜው አይበቃም።"

ለክፍለ ጊዜው መጨመር ያቀረቡት ምክንያት የመማሪያ መጽሐፉን ለመጨረስ የተመደበው ክፍለ ጊዜ በቂ አይደለም የሚል ነው። እዚህ ላይ መምህራን ካላቸው ልምድና ከሙያቸው አንፃር የሰጡት አስተያየት መሆኑ ይገመታል።
ምልከታው በተካሄደበትም ጊዜ አንዳንድ መምህራን የዕለቱን ትምህርት በተመደበው ክፍለ ጊዜ ለመጨረስ ሲቸገሩ ለማየት ተችሏል። በአጠቃላይ ሲታይ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበው ክፍለ ጊዜ አነስተኛ እንደሆነ ከመረጃዎቹ መገንዘብ ተችሏል። ስለዚህ ተማሪዎቹ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ የሰጡት ምላሽ ተቀራራቢ በመሆኑ ትምህርት ሚኒስቴር ለአማርኛ ቋንቋ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ በቂ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ሊመረምረው ይገባል። ከመምህራንም ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ በሳምንት ለአማርኛ ቋንቋ የተመደበው ክፍለ ጊዜ በቂ አለመሆኑን ገልፀዋል።

በተራ ቁጥር 1.10 በሠንጠረዥ 4 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 69 (57.5%) በጣም እስማማለሁ፣ 33 (27.5%) እስማማለሁ፣ 12 (10.0%) አልስማማም፣ 6 (5.0%) በጣም አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 4.23 ነው። ለቀረበው ጥያቄ 85% አአዎንታዊ፣ 15% አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። ስለዚህ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 85.0% የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና ከሚሰጡት ትምህርቶች እንደ አንዱ ሆኖ መሰጠት አለበት በማለት ድጋፋቸውን ሰጥተዋል። ከመምህራን ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅም አብዛኛዎቹ መምህራን የአማርኛ ቋንቋ ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና ከሚሰጡት ትምህርቶች እንደ አንዱ ሆኖ ቢሰጥ ለቋንቋው እድገት አስተዋፅኦ ይኖረዋል በማለት መልሰዋል።

ለምሳሌ መምህር 1፡ "የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና ላይ ከሚሰጡት ትምህርቶች እንደ አንዱ ሆኖ መሰጠት አለበት። ምክንያቱም

የአማርኛ ቋንቋ በስነ ፅሁፍ የዳበረ ነው። የራሱ የሆነ ፊደል አለው፣ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል እንደ የጋራ መግባቢያ ይገለገልበታል። ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንደሌሎቹ የትምህርት አይነቶች ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና ከሚሰጡት ትምህርቶች እንደ አንዱ ሆኖ መሰጠት አለበት።" ሁሉም ተጠኚ መምህራን ይህን የመምህሩን ሀሳብ ይጋራሉ። ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና ከሚሰጡት ትምህርቶች እንደ አንዱ ሆኖ መሰጠት አለበት።

በተራ ቁጥር 1.11 በሠንጠረዥ 4 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 62 (51.7%) በጣም እስማማለሁ፣ 31 (25.8%) እስማማለሁ፣ 10 (8.3%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 11(9.2%) አልስማማም፣ 6 (5.0%) በጣም አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 4.10 ነው። በዚህ ሀሳብ ላይ 77.5% አዎንታዊ፣ 14.2% አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። ለዚህ ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ባልተናነሰ የማስተማሪያ ቋንቋ ሊሆን ይችላል በማለት ድጋፋቸውን ሰጥተዋል። ከመምህራንም ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ መምህራን ተመሳሳይ ሀሳብ አቅርበዋል።

ለምሳሌ መምህር 5፡ "የአማርኛ ቋንቋ ታላቅ ቋንቋ ነው። ከማንኛውም ቋንቋ ባልተናነሰ መልዕክት ለማስተላለፍ ብቁ ነው። የአማርኛ ቋንቋ በኮሌጅ ደረጃ ማስተማሪያ ቋንቋ ሊሆን ይችላል በማለት አስተያየቱን አቅርቧል።"

መምህር 2፡ "የአማርኛ ቋንቋ ብዙ ታሪክ ያለው ቋንቋ ነው። የራሱ ፊደል አለው። በስነ ፅሁፍ የዳበረ ነው። ስለዚህ ድጋፍ ከተደረገለት ከማንኛውም ቋንቋ ባልተናነሰ መልኩ የማስተማሪያ ቋንቋ ለመሆን ብቃት አለው።" ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ባልተናነሰ መልኩ የማስተማሪያ ቋንቋ በመሆን ሊያገለግል ይችላል። የዚህ ጥናት አቅራቢም የአማርኛ ቋንቋ የማስተማሪያ ቋንቋ ለመሆን ብቃት ያለው መሆኑን ያሳያል።

ሠንጠረዥ 4ሐ፡

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | % | 4 | % | 3 | % | 2 | % | 1 | % | |
| 1.12 | የአማርኛ ቋንቋ ለከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና ላይ ባይካተትም ቋንቋውን መማር ያስደስተኛል። | 67 | 55.8 | 38 | 31.7 | 5 | 4.2 | 6 | 5.0 | 4 | 3.3 | 4.38 |
| 1.13 | የአማርኛ ቋንቋ ከኢትዮጵያ አልፎ የአፍሪካ ቋንቋ ቢሆን በጣም እደሰታለሁ። | 72 | 60.0 | 31 | 25.8 | 8 | 6.7 | 9 | 7.5 | - | - | 3.33 |
| 1.14 | የአማርኛ መምህራን የሙያ ማሻሻያ ኮርስ መከታተል አለባቸው። | 43 | 35.8 | 36 | 30.0 | 20 | 16.7 | 14 | 11.7 | 7 | 5.8 | 3.78 |
| 1.15 | አማርኛ ቋንቋ ከባድ ትምህርት ስለሆነ ለእኔ አይመችኝም። | 2 | 1.7 | 14 | 11.7 | 18 | 15.0 | 55 | 45.8 | 31 | 25.8 | 3.83 |
| 1.16 | አማርኛ ለእኔ አሰልቺና አድካሚ ትምህርት ነው። | 12 | 10.0 | 7 | 5.8 | - | - | 37 | 30.8 | 64 | 53.4 | 4.12 |
| 1.17 | አማርኛ በሥራ ገበያም ሆነ በሌላው የኑሮ መስክ ጠቃሚ ነው የሚል እምነት አለኝ። | 53 | 44.2 | 53 | 44.2 | 5 | 4.2 | 4 | 3.2 | 5 | 4.2 | 4.21 |
| 1.18 | የአማርኛ ትምህርት ብዙም ስለማይጠና ሌላ ጊዜ ሰጥቼ ለፈተና የምዘጋጀው ለሌሎች ከባድ ለሆኑ ትምህርቶች ነው። | 60 | 50.0 | 36 | 30.0 | 9 | 7.5 | 10 | 8.3 | 5 | 4.2 | 4.13 |

በተራ ቁጥር 1.12 በሠንጠረዥ 4 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 67 (55.8%) በጣም እስማማለሁ፣ 38 (31.7%) እስማማለሁ፣ 5 (4.2%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 6 (5.0%) አልስማማም፣ 4 (3.3%) በጣም አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 4.38 ነው። ይህንን ሀሳብ በመደገፍ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 87.5% አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ 8.3% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ስለዚህ የመሰናዶ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን መማር እንደሚያስደስታቸው ጥናቱ አረጋግጧል። ምንም እንኳን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና ላይ ባይካተትም የመሰናዶ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው። ትምህርቱን በመማራቸው ደስተኞች ናቸው። ከመምህራንም ጋር

በተደረገው ቃለ መጠይቅም ተማሪዎች በአማርኛ ክፍል ጊዜ ንቁ ተሳትፎ እደሚያደርጉ ገልፀዋል።

ለምሳሌ መምህር 3፡ "በኔ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች ከፍተኛ ተሳትፎ ያደርጋሉ። ጥያቄ ስጠይቃቸው ብዙዎቹ እጃቸውን በማውጣት ለመመለስ ይጥራሉ በማለት አስተያየቱን ሰጥቷል።"

መምህርት 6፡ "ምንም እንኳ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና ላይ ባይካተትም በክፍል ውስጥ ጥሩ ተሳትፎ ያደርጋሉ። የክፍል ስራ ሰርተው ይመጣሉ፤ ጥያቄ ሲጠየቁ አብዛኛዎቹ ይመልሳሉ። ጥቂት ተማሪዎች ደግሞ ትምህርቱን የመማር ፍላጎ የላቸውም። ባጠቃላይ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ጥሩ ተሳትፎ ያደርጋሉ።"

በዳግማዊ ምኒሊክ መሰናዶ ትምህርት ቤት የጠዋት ፈረቃ በተካሄደው ምልከታ የአማርኛ መምህሩ ሲያስተምር ተማሪዎች በጥሞና ያዳምጣሉ። መምህሩ ጥያቄ ሲጠይቅ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች መልስ ይሰጣሉ። አንዳዶቹ ደግሞ ያልገባቸውን ይጠይቃሉ። ባጠቃላይ ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ ትምህርቱን ሲከታተሉ ለማየት ተችሏል።

ስለዚህ ከተማሪዎች ምላሽ፣ ከመምህራን ቃለ መጠይቅና ከምልከታው በተገኘው ውጤት መሰረት የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ አመለካከት እንዳላቸውና ትምህርቱንም እንደሚወዱት በጥናቱ ተረጋግጧል። ስለሆነም ተማሪዎች የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አስፈላጊው ድጋፍ ሁሉ ሊደረግለት ይገባል።

በክፍል ውስጥ በተካሄደው ምልከታ አብዛኛዎቹ መምህራን አሳታፊ የማስተማር ዘዴ በመጠቀማቸውና ትምህርቱን ሳቢና ማራኪ አድርገው በማቅረባቸው ተማሪዎች በከፍተኛ ሁኔታ ሲሳተፉ ለመመልከት ተችሏል። በአጠቃላይ ሲታይ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ጥሩ አመለካከት እንዳላቸውና ትምህርቱንም እንደሚወዱት ጥናቱ አረጋግጧል።

በተራ ቁጥር 1.13 በሠንጠረዥ 4 ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ 72 (60.0%) በጣም እስማማለሁ፣ 31 (25.8%) እስማማለሁ፣ 8 (6.7%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 9 (7.5%) አልስማማም፣ በማለት መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 3.33 ነው። ለዚህ

ጥያቄ አብዛኞዎቹ ተማሪዎች 85.8% አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ 7.5% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ አብዛኞዎቹ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ተስፋፍቶና ዳብሮ የአፍሪካ ቋንቋ ቢሆን ደስተኛ እንደሚሆኑ መረጃው ያመለክታል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ከመምህራን ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅም ሁሉም ተጠኚ መምህራን የተማሪዎችን ስሜት ይጋራሉ፡፡

ለምሳሌ መምህር 1፡ "የአማርኛ ቋንቋ ለብዙ ዘመናት ያገለገለ ቋንቋ ነው፡፡ በአፍሪካ ውስጥ የራሱ ፊደል ያለው ቋንቋ ነው፡፡ በቋንቋው ብዙ መፃህፍት ተፅፎበታል፡፡ ለአፍሪካውያንም ከስዋህሊ በተሻለ ሁኔታ ሊያገለግል ይችላል ስለዚህ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል"፡፡

መምህር 4፡ "ባገራችን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በጋራ የሚግባባው በአማርኛ ቋንቋ ነው፡፡ በፌዴራል መንግስት ደረጃም ቢሆን አማርኛ የስራ ቋንቋ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ ቋንቋው በስነ ጽሁፍ ደረጃ የዳበረ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ታላቅ ቋንቋ ከኢትዮጵያ አልፎ የአፍሪካ ቋንቋ ሊሆን ይችላል፡፡ መንግስትም ትኩረት ሊጠው ይገባል፡፡" ስለዚህ ከተማሪዎቹ የቀረበው ምላሽና ከመምህራን የተገኘው መልስ ተደጋጋፊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የአማርኛ ቋንቋ የአፍሪካ ቋንቋ ሆኖ ለማገልገል ብቃት አለው፡፡

በተራ ቁጥር 1.14 ሠንጠረዥ 4 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 43 (35.8%) በጣም እስማማለሁ፣ 36 (30.0%) እስማማለሁ፣ 20 (16.7%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 14 (11.7%) አልስማማም፣ 7 (5.8%) በጣም አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥቡ 3.78 ነው፡፡ በዚህ ሀሳብ ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ተማሪዎች 65.8% አዎንታዊ፣ 17.5% አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሙያ ማሻሻያ ኮርስ መከታተል አለባቸው በማለት አስተያየታቸውን አቅርበዋል፡፡ በቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ሶስት መምህራን ልዩ ልዩ ስልጠና ወስደናል፣ ነገር ግን ስልጠናው የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የሚያግዝ አይደለም ሲሉ ሁለት መምህራን ደግሞ ምንም አይነት የሙያ ማሻሻያ ስልጠና አልወሰድንም በማለት ገልፀዋል፡፡ ከውይይቱ አብዛኞቹ መምህራን የሙያ ማሻሻያ ስልጠና አለመውሰዳቸውን እንገነዘባለን፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ ለመምህራን የሙያ ማሻሻያ ስልጠና ሊሰጣቸው

ይገባል ያሉት ሀሳብ በመምህራንም ዘንድ ድጋፍ አግኝቷል። መምህራንም የሙያ ማሻሻያ ስልጠና እንደሚያስፈልጋቸው መረጃው አመላክቷል።

በተራ ቁጥር 1.15 ሠንጠረዥ 4 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 2 (1.7%) በጣም እስማማለሁ፣ 14 (11.7%) እስማማለሁ፣ 18 (15.0%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 55 (45.8%) አልስማማም፣ 31 (25.8%) በጣም አልስማማም፣ በማለት መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 3.83 ነው። በዚህ ሀሳብ ላይ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 13.4% አዎንታዊ፣ 71.6% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ስለዚህ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሲማሩ ምንም ችግር እንደማይገጥማቸው ለማወቅ ተችሏል።

ለምሳሌ መምህር 4፡ "ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ጥሩ ተሳትፎ ያደርጋሉ። በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ይፅፋሉ፣ ይናገራሉ፣ ሀሳባቸውን በቀላሉ መግለፅ ይችላሉ። በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ምንም አይቸገሩም"። ስለዚህ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት በቀላሉ ይረዱታል፤ ቋንቋውን ለመማር አይከብዳቸውም። ከመምህራም ጋር በተካሄደው ቃለ መጠይቅ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውጤት ያስመዘግባሉ በማለት መምህራን ገልፀዋል። ስለዚህ ተማሪዎች ጥሩ ውጤት ካመጡ ቋንቋውን በቀላሉ ይረዱታል ማለት ነው።

በተራ ቁጥር 1.16 ሠንጠረዥ 4 ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ 12 (10.0%) በጣም እስማማለሁ፣ 7 (5.8%) እስማማለሁ፣ 37 (30.8%) አልስማም፣ 64 (53.4%) በጣም አልስማማም፣ የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 4.12 ነው። በዚህ ሀሳብ ላይ 13.4% አዎንታዊ፣ 71.6% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህን ሀሳብ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 85.8% የሚሆኑት ተቃውመውታል። ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰልቺና አድካሚ አለመሆኑን አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ገልፀዋል። ከመምህራን ጋር በተካሄደው ቃለ መጠይቅም አብዛኛዎቹ መምህራን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ በማለት አስተያየታቸውን አቅርበዋል። የአማርኛ ትምህርት አሰልቺና አድካሚ ቢሆን ኖሮ ተማሪዎች በንቃት ትምህርቱን አይከታተሉም ነበር። ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰልቺና አድካሚ አለመሆኑ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽና ከመምህራን ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማረጋገጥ ተችሏል።

ለምሳሌ መምህር 5፡ "በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ። የምሰጣቸውን የክፍል ስራ ይሰራሉ። ትምህርቱን ደስ ብሏቸው ይማራሉ።"

መምህር 3፡ "በኔ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ ይከታተላሉ። ነገር ግን እንደ መምህሩ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል። መምህሩ ትምህርቱን ሲያቀርብ ሁልጊዜ አንድ አይነት መንገድ የሚከተል ከሆነ ተማሪዎች ትምህርቱን ሊጠሉት ይችላሉ። ስለዚህ መምህሩ በየጊዜው የተለያየ ርዕስ ይዞ ገብቶ የሚያስተምር ከሆነ ተማሪዎች ትምህርቱን ይወዱታል።"

በክፍል ምልከታውም ወቅት ተማሪዎች ጥያቄዎችን ሲጠይቁ፣ መምህሩ መልስ ሲሰጥ፣ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ሲሳተፉ ለማየት ተችሏል። ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለተማሪዎቹ አሰልቺና አድካሚ አለመሆኑን መረጃዎቹ አመልክተዋል። በተጨማሪም በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ባልተናነሰ ሁኔታ ተማሪዎች ሲሳተፉ፣ ሲጠይቁ መምህሩ ለሚጠይቀው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ ተመልክተናል። ይህም የሚያሳየን በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ትምህርቱ በጥሩ ሁኔታ መካሄዱን ነው።

በተራ ቁጥር 1.17 በሠንጠረዥ 4 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 53 (44.2%) በጣም እስማማለሁ፣ 53 (44.2%) እስማማለሁ፣ 5 (4.2%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 4 (3.2%) አልስማማም፣ 5 (4.2%) በጣም አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 4.21 ነው። ከዚህ በላይ ለቀረበው ጥያቄ 88.4% አዎንታዊ፣ 7.4% አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። ስለዚህ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 88.4% አማርኛ በማንኛውም የስራ መስክ ይጠቅማል በማለት ሀሳቡን ደግፈውታል። ከመምህራም ጋር የተደረገው ቃለ መጠይቅም የአማርኛ ቋንቋ ሰፊ አገልግሎት እንዳለው ገልፀዋል።

ለምሳሌ መምህር 2፡ "አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል ለጋራ መግቢያያነት ቋንቋውን ይጠቀምበታል። ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ ሰፊ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል በማለት አስተያየቱን አቅርቧል።" ከተማሪዎቹ የተገኘው ምላሽና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው ውጤት፣ የአማርኛ ቋንቋ በየትኛውም የኑሮ መስክ ጠቃሚ

መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ስሆነም ቋንቋው እያደገና እየደረጀ እንዲሄድ ድጋፍ ቢደረግለት ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል።

በተራ ቁጥር 1.18 በሠንጠረዥ 4 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 60 (50.0%) በጣም እስማማለሁ፣ 36 (30.0%) እስማማለሁ፣ 9 (7.5%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 10 (8.3%) አልስማማም፣ 5 (4.2%) በጣም አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 4.13 ነው። ለዚህ ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 80% አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት ሰፊ ጊዜ ሰጥተው እንደማያጠኑት መረጃው አመልክቷል። ከመምህራን ጋር በተካሄደው ቃለ መጠይቅ አብዛኛዎቹ መምህራን ተማሪዎች የአማርኛን ትምህርት ትኩረት ሰጥተው እንደማያጠኑት ገልፀዋል።

ለምሳሌ መምህር 5፤ "አብዛኞቹ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ስለሆነ አውቀዋለሁ በማለት እንደሌሎቹ የትምህርት አይነቶች ትኩረት ሰጥተው አያጠኑትም በማለት አስተያየቱን አቅርቧል።"

መምህር 4፤ "የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮሌጅ መግቢያ ፈተና ላይ ስማይካተት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን አያጠኑትም።" ከዚህ በላይ ከተማሪዎች የተሰጠው መልስና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው ውጤት የሚያሳየው ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ትኩረት ሰጥተው እደማያጠኑት ነው። ስለዚህ የመምህራንና የወላጆች ምክርና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል።

ባጠቃላይ ሲታይ ለተላውጦ አንድ የቀረቡትን ምላሾች ስንመለከት አብዛኞቹ አዎንታዊ ናቸው። የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ አመለካከት እንዳላቸውና ቋንቋውን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ከፍተኛ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል። ለተላውጦ አንድ የተጠቃለለ መረጃ ለማግኘት ሠንጠረዥ 4ን ይመልከቱ።

### 4.1.3. ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸው አመለካከት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ተማሪዎች ለአማርኛ መምህራን ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል በዝርዝር ይቀርባል።

ሠንጠረዥ 5፡ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸው አመለካከት

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | % | 4 | % | 3 | % | 2 | % | 1 | % | |
| 2 | መምህራንን የሚመለከቱ ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | |
| 2.1 | የአማርኛን ትምህርት የምወደው መምህሩን ስለምወደው ነው። | 36 | 30.0 | 42 | 35.0 | 12 | 10.0 | 24 | 20.0 | 6 | 5.0 | 3.65 |
| 2.2 | የአማርኛ መምህር ሊያስተምር ክፍሉ ሆኜ እጠባበቀዋለሁ። | 60 | 50.0 | 42 | 20.0 | 7 | 5.8 | 5 | 4.2 | 6 | 5.0 | 4.21 |
| 2.3 | የአማርኛ መምህሩን ስለማልወደው ትምህርቱንም አልወደውም | 6 | 5.0 | 24 | 20.0 | 6 | 5.0 | 78 | 65.0 | 6 | 5.0 | 3.45 |
| 2.4 | የአማርኛ መምህራችን ጥያቄ ስንጠይቀው ስለሚናደድ ይሰድበናል። | 5 | 4.2 | 13 | 10.8 | 6 | 5.0 | 30 | 25.0 | 66 | 55.0 | 4.12 |
| 2.5 | የአማርኛ መምህራችን የሚያስተምረውን ትምህርት ጠንቅቆ ያውቀዋል። | 78 | 65.0 | 24 | 20.0 | 12 | 10.0 | 6 | 5.0 | - | - | 4.45 |
| 2.6 | በአማርኛ ክፍለ ጊዜ መምህሩ ስለሚያበረታታን ትምህርቱን በፍቅር እማራለሁ። | 48 | 40.0 | 41 | 34.2 | 9 | 7.5 | 18 | 15.0 | 4 | 3.3 | 3.93 |
| 2.7 | የአማርኛ መምህሩ የሚሰጠን የቤት ሥራ አሰልቺ አይመስለኝም። | 12 | 10.0 | 24 | 20.0 | - | - | 54 | 45.0 | 30 | 25.0 | 3.55 |
| 2.8 | የአማርኛ መምህሩ የማስተማር ስልቱና አቀራረቡ ማራኪና ሳቢነት አለው። | 60 | 50.0 | 36 | 30.0 | 18 | 15.0 | 6 | 5.0 | - | - | 4.25 |
| 2.9 | የአማርኛ መምህር የሚሰጠን የቤት ስራ ሁልጊዜ ያርማል፣ | 12 | 10.0 | 18 | 15.0 | 18 | 15.0 | 66 | 55.0 | 6 | 5.0 | 3.30 |
| 2.10 | መምህሩ የሚሰጠን የቤት ስራ ሁልጊዜ ስለማያርምልኝ ክህሎቴ ለመማር ይሰለቸኛል። | 24 | 20.0 | 12 | 10.0 | 6 | 5.0 | 60 | 50.0 | 18 | 15.0 | 3.30 |

በተራ ቁጥር 2.1 ሠንጠረዥ 5 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 36 (30.0%) በጣም እስማማለሁ፣ 42 (35.0%) እስማማለሁ፣ 12 (10.0%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 24 (20.0%) አልስማማም፣ 6 (5.0%) በጣም አልስማማም፣ በማለት መልሰዋል። አማካይ ነጥቡ 3.65 ነው። ለዚህ ጥያቄ 65% የሚሆኑ ተማሪዎች አዎንታዊ፣ 25%

የሚሆኑት አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ 65% የሚሆኑት ሀሳቡን ስደገፉት የአማርኛ መምህሩ በተማሪዎቹ ዘንድ ተወዳጅ መሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡ ከመምህራን ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ አብዛኞዎቹ መምህራን ለመምህርነት ሙያ ከፍተኛ ፍቅር ያላቸውና ለተማሪዎቻቸው አክብሮት የሚሰጡ በመሆናቸው በተማሪዎቻቸው ዘንድ ይወደዳሉ፡፡

ለምሳሌ መምህር 3፡ ዘወትር ወደ ክፍል ስገባ የማስተምረውን ትምህርት ተዘጋቼ እገባለሁ፡፡ ትምህርቱ እንዳይሰለቻቸው ጥረት አደርጋለሁ፡፡ ተማሪዎቼን አከብራለሁ ስለዚህ ለኔ ጥሩ አመለካከት አላቸው በማለት ገልጿል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጥሩ አመለካከት አላቸው፡፡ አብዛኞዎቹ መምህራን ለመምህርነት ሙያ ከፍተኛ ፍቅር እንዳላቸው መረጃው ይጠቁማል፡፡

በተራ ቁጥር 2.2 ሠንጠረዥ 5 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 60 (50.0%) በጣም እስማማለሁ፣ 42 (35.0%) እስማማለሁ፣ 7 (5.8%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 5 (4.2%) አልስማማም፣ 6 (5.0%) በጣም አልስማማም፣ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥቡ 4.21 ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ አብዛኞዎቹ ተማሪዎች 85% አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ የአማርኛ መምህራን በጥሩ ሁኔታ እንደሚያስተምሩ መረጃው አመልክቷል፡፡ ከተጠኚ መምህራን ጋር በተደረገው ውይይትም ይህንኑ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ መምህራን፤ ተማሪዎች የአማርኛን ትምህርት ይከታተላሉ ወይ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ አብዛኞዎቹ መምህራን ተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ በንቃት እንደሚሳተፉ ገልፀዋል፡፡

ለምሳሌ መምህር 5፡ "ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ከፍተኛ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡ ትምህርቱን እንዲከታተሉ የተለያየ ዘዴዎችን እጠቀማለሁ፡፡ የልቦለድ ስራዎችን አነብላቸዋለሁ፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት ይወዱታል፡፡"

መምህርት 6፡ "በእኔ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ ትምህርቱን ይከታተላሉት በማለት አስተያየቷን አቅርባለች፡፡"

በመድሀኒዓለም መሰናዶ ትምህርት ቤት በክስዓት በኋላ ፈረቃ በተካሄደው ምልከታ መምህሩ ሲያስተምር ተማሪዎች ከልብ ሆነው ይከታተሉት ነበር፡፡ መምህሩ ጥያቄ ሲጠይቅ እጃቸውን በማውጣት ይመልሳሉ፡፡ በርግጥ የከሰዓት በኋላ ክፍለ ጊዜ

ስለነበር ጥቂት ተማሪዎች የድካም ስሜት ይታይባቸው ነበር። በተረፈ አብኛዎቹ ተማሪዎች ከፍተኛ ተሳትፎ ሲያደርጉ ለማየት ተችሏል። ስለዚህ የመሰናዶ ተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ትምህርቱን በጥሩ ሁኔታ ይከታተላሉ።

በተራ ቁጥር 2.3 ሠንጠረዥ 5 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 6 (5%) በጣም እስማማለሁ፣ 24 (20.0%) እስማማለሁ፣ 6 (5%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 78 (65.0%) አልስማማም፣ 6 (5.0%) በጣም አልስማማም፣ በማለት መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 3.45 ነው። ለዚህ ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 70% በመቃወም መልስ ሰጥተዋል። ስለዚህ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ለትምህርቱም ሆነ ለአማርኛ መምህራቸው ጥላቻ እንደሌላቸው ጥናቱ አረጋግጧል። ከመምህራንም ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ በጎ አመለካከት እንዳላቸው ተገንዝበናል።

ለምሳሌ መምህር 2፡ "ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በስነ ስርአት ይማራሉ፣ ትምህርቱንም ይወዱታል፤ ትምህርቱን ከወደዱት ደግሞ በመምህሩ ላይ ጥላቻ አይኖራቸውም። አልፎ አልፎ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ማስተማር ደስ የማይላቸው መምህራን አሉ። እንደነዚህ አይነቶቹን መምህራን ተማሪዎች ሊጠሏቸው ይችላሉ። ነገር ግን አብዛኛዎቹ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሙያ ግዴታቸውን ስለሚወጡ በማስተማሩ ስራ የተመሰገኑ ናቸው።"

በክፍል ምልከታውም ወቅት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ትምህርቱን በንቃት ሲከታተሉ ለማየት ተችሏል። ስለዚህ የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርትም ሆነ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጥላቻ የላቸውም።

በተራ ቁጥር 2.4 ሠንጠረዥ 5 ላይ ለቀረበው ጥያቄ የአማርኛ መምህራንን ስነ ምግባር የሚመለከት ሲሆን 5 (4.2%) በጣም እስማማለሁ፣ 13 (10.8%) እስማማለሁ፣ 6 (5.0%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 30 (25.0%) አልስማማም፣ 66 (55.0%) በጣም አልስማማም፣ በማለት መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡም 4.12 ነው። ለዚህ ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 80% በመቃወም መልስ ሰጥተዋል። 15% የሚሆኑት ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡ ስለዚህ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ መምህራቸውን ጥያቄ በመጠየቃቸው ስድብ የማይደርስባቸው መሆኑን ገልፀዋል። በክፍል ምልከታው የተገኘውም መረጃ ይህንኑ

የሚደግፍ ነው። አብዛኞዎቹ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመምህርነት ሙያ ለብዙ አመታት ያገለገሉ ናቸው። በውይይቱ ወቅት መምህራን ለተማሪዎቻቸው ፍቅርና አክብሮ እንዳላቸው ለመገንዘብ ተችሏል።

ለምሳሌ መምህር 2፡ "ከተማሪዎቼ ጋር መልካም ግንኙነት አለኝ ሲያጠፉ እመክራቸዋለሁ፤ ሲሳሳቱ ስህተቱን ለማረም ጥረት አደርጋሁ። ግንኙነታችን የአባትና የልጅ አይነት ግንኙነት ነው፤ ተማሪዎቼን በፍቅር እይዛቸዋለሁ።" በክፍል ምልከታውም ወቅት በሶስቱ የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ሳይጨነቁ ተዝናንተው ሲማሩ ለመመልከት ተችሏል። ይህም የሚያሳየን በመምህራንና በተማሪዎች መካከል መልካም ግንኙነት መኖሩን ነው። ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጥሩ ስነ ምግባር የተላበሱ በመሆናቸው ጥያቄ ተጠየቅን ብለው አይሳደቡም፤ እንዲያውም ለተማሪዎቻቸው አክብሮትና ፍቅር አላቸው።

በተራ ቁጥር 2.5 ሠንጠረዥ 5 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 78 (65.0%) በጣም እስማማለሁ፤ 24 (20.0%) እስማማለሁ፤ 12 (10.0%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 6 (5.0%) አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 4.45 ነው። ለዚህ ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 85% አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 5% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ስለዚህ 85% የሚሆኑ ተማሪዎች ሀሳቡን ስለደገፉት የአማርኛ መምህራን የሚስተምሩትን ጠንቅቀው የሚያውቁ መሆናቸው መረጃው አመለክቷል። በክፍል ምልከታ የመምህራን የማስተማር ሂደት አባሪ 4 ላይ ለጥያቄ 5 ከምልከታ የተገኘውን ውጤት ስንመለከት ሁሉም ተጠኚ መምህራን በቋንቋው ትምህርት ላይ ያላቸው እውቀትና የማስተማር ብቃት ከፍተኛ መሆኑ በምልከታው ወቅት ተረጋግጧል።

ስለዚህ የአማርኛ መምህራን የሚያስተምሩን ትምህርት ጠንቅቀው የሚያውቁ መሆኑን ከተማሪዎቹ የተሰጠው ምላሽና ከምልከታው የተገኘው ውጤት አረጋግጧል። ከዚሁም ጋር በተዛማጅ ጽሁፍ ክለሳ ክፍል እንደተገለፀው መምህሩ ለሙያው ከፍተኛ ፍቅር ያለው፤ የሚያስተምረውን ትምህርት ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ ተማሪዎቹን የሚወድና ታታሪ ሊሆን ይገባል። እንዲህ አይነቱ መምህር በተማሪዎቹ ላይ አዎንታዊ አመለካከትን ሊፈጥር ይችላል።

በተራ ቁጥር 2.6 ሠንጠረዥ 5 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 48 (40.0%) በጣም እስማማለሁ፣ 41 (34.2%) እስማማለሁ፣ 9 (7.5%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 18 (15.0%) አልስማማም፣ 4 (3.3%) በጣም አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 3.93 ነው። ከዚህ የምንረዳው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 74.2% አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ስለዚህ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ መምህራን ተማሪዎቹን እንደሚያበረታቱ ለማወቅ ተችሏል። በክፍል ምልከታው ተራ ቁጥር 3 ሠንጠረዥ 8 ላይ ለቀረበው የተገኘውን ውጤት ስንመለከት አራቱ መምህራን ሁሉንም ተማሪዎች በማሳተፍ የዕለቱን ትምህርት አከናውነዋል።

ከምልከታው አብዛኛዎቹ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ስለሚያበረታቷቸው ተማሪዎቹ ትምህርቱን በጥሩ ሁኔታ ይከታተላሉ።

በተራ ቁጥር 2.7 ሠንጠረዥ 5 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 12 (10%) በጣም እስማማለሁ፣ 24 (20%) እስማማለሁ፣ 54 (45%) አልስማማም፣ 30 (25%) በጣም አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 3.55 ነው። ለዚህ ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 70% አሉታዊ ምለሽ ሰጥተዋል። ስለዚህ ተማሪዎች መምህራን የሚሰጧቸውን የቤት ስራ ሰርተው እንደሚመጡ ለመገንዘብ ተችሏል።

ለምሳሌ መምህር 5፡ "ተማሪዎች ልዩ ልዩ መልመጃዎችን የቤት ስራዎችን ሰርተው ይመጣሉ ነገር ግን ደብተራቸውን ለማረም በጣም አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም በአንድ ክፍል ውስጥ የተማሪዎቹ ቁጥር በጣም ብዙ በመሆኑ ነው።" ተማሪዎች መምህራን የሚሰጧቸውን የቤት ስራዎች ሰርተው ቢመጡም በአንፃሩ ደግሞ መምህራን የተማሪዎችን ደብተር እንደማያርሙ በቃለ መጠይቅ ወቅት ገልፀዋል። ለዚህም የሰጡት ምክንያት በአንድ ክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር መብዛት ነው። ይሁን እንጂ መምህራን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የተማሪዎችን ደብተር ለማረም ጥረት ቢያደረጉ ተማሪዎች ከስህተታቸው ለመማር እድል ያገኛሉ። በተራ ቁጥር 2.8 ሠንጠረዥ 5 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 60 (50.0%) በጣም እስማማለሁ፣ 36 (30.0%) እስማማለሁ፣ 18 (15.0%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 6 (5.0%) አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡም 4.25 ነው። ለዚህ ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 80% አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። ስለዚህ አብዛኛዎቹ

ተማሪዎች ሀሳቡን ስለደገፉት የአማርኛ መምህራን የማስተማር ስልትና አቀራረብ ለተማሪዎቹ ተስማሚ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል።
በክፍል ምልከታው ጊዜ በተራ ቁጥር 8 አባሪ 4 ላይ ለቀረበው ጥያቄ የተገኘው ውጤት ከስድስቱ ተጠኚ መምህራን አራቱ አሳታፊ የማስተማር ስልት የሚከተሉ መሆኑን በምልከታው ወቅት ማረጋገጥ ተችሏል። ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አሳታፊ የማስተማር ስልት በመጠቀም ትምህርቱን ሳቢና ማራኪ አደርገው አቅርበዋል። ይህ አሳታፊ የማስተማር ስልት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በራሳቸው እንዲሰሩ ከጓደኞቻቸውም ጋር እየተጋገዙ የመስራት ልምድ እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል።

በተራ ቁጥር 2.9 ሠንጠረዥ 5 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 12 (10.0%) በጣም እስማማለሁ፣ 18 (15.0%) እስማማለሁ፣ 18 (15.0%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 66 (55.0%) አልስማማም፣ 6 (5.0%) በጣም አልስማማም በማለት መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 3.30 ነው። ለዚህ ጥያቄ 60% የሚሆኑ ተማሪዎች ሀሳቡን ተቃውመው አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። 25% የሚሆኑት ሀሳቡን ደግፈው አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ስለዚህ 60% የሚሆኑት ተማሪዎች ሀሳቡን ስለተቃወሙት የአማርኛ መምህራን የቤት ሥራ ሰጥተው የተማሪዎቹን ደብተር እንደማያርሙ ለመገንዘብ ተችሏል። ከመምህራን ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅም ሶስት መምህራን የተማሪዎችን መልመጃና የቤት ሥራዎችን እንደማያርሙ ለማረጋገጥ ተችሏል። ሁለት መምህራን ደግሞ አልፎ አልፎ አርመው እንደሚመልሱ ገልጸዋል።

ለምሳሌ መምህር 4፡ "በአንድ ክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር በመብዛቱ የተማሪዎችን የቤት ሥራ ለማረም በጣም ያስቸግረኛል።"

መምህር 2፡ "በአንድ ክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር በመብዛቱ የተማሪዎችን ደብተር አላርምም።" ስለዚህ አብዛኞቹ መምህራን የተማሪዎችን የቤት ስራ እንደማያርሙ ከተማሪዎቹ በተገኘው ምላሽና ከመምህራን ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማረጋገጥ ተችሏል። መምህራን የተማሪዎችን የቤት ስራዎችና ልዩ ልዩ መልመጃዎች ማረም ይጠበቅባቸዋል። ይህንን ተግባራዊ ካላደረጉ በመማር ማስተማሩ ላይ ችግር መኖሩን ያሳያል። ስለዚህ መምህራን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የተማሪዎችን የቤት ስራ ለማረም ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በተራ ቁጥር 2.10 ሠንጠረዥ 5 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 24 (20%) በጣም እስማማለሁ፣ 12 (10.0%) እስማማለሁ 6 (5.0%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 60 (50.0%) አልስማማም፣ 18 (15.0%) በጣም አልስማማም በማለት መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 3.30 ነው። ለዚህ ጥያቄ 65% ተማሪዎች አሉታዊ፣ 30% የሚሆኑት ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ስለዚህ 65% ተማሪዎች ሀሳቡን ተቃውመውታል። የአማርኛ መምህራንም የሚሰጡትን የቤት ሥራ ስለማያርሙ ተማሪዎች ከስህተታቸው ለመማር አለመቻላቸውን ለመገንዘብ ተችሏል። ከመምህራን ጋር በተደርገው ቃለ መጠይቅም አብዛኞቹ መምህራን የተማሪዎችን የቤት ስራዎች ባለማረማቸው ተማሪዎች ከስህተታቸው ለመማር አለመቻላቸው ተገልጿል።

ለምሳሌ መምህር 3፡ "የተማሪዎች ቁጥር በጣም ብዙ ስሆን የተማሪዎችን ደብተር አላርምም በማለት ገልጿል።"

መምህር 4፡ "በአንድ ክፍል ውስጥ ቁጥራቸው ብዙ የሆኑ የተማሪዎች ስላሉ የቤት ስራቸውን ለማረም በጣም አስቸጋሪ ነው በማለት አስተያቱን አቅርቧል።" አብዛኞቹ መምህራን የተማሪዎችን የቤት ስራ እንደማያርሙ መረጃው አመልክቷል። ስለዚህ መምህራን የተማሪዎቹን የቤት ስራዎች ካላረሙ ተማሪዎች ስህተታቸውን ለማረም አይችሉም። የተማሪዎችን የቤት ስራዎች ማረም የትምህርቱ አካል ስለሆነ መምህራን የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅመው ማረም ይጠበቅባቸዋል።

በዚህ ተላውጦ ስር የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን በተመለከተ የቀረቡት ጥያቄዎች ከአንዱ ጥያቄ በስተቀር ሁሉም አዎንታዊ ምላሽ አግኝተዋል። በተላውጦው ለቀረቡት ጥያቄዎች አማካይ ነጥቡ 3.82 ነው። ስለ ተላውጦ ሁለት የተጠቃለለ መረጃ ለማግኘት ሰንጠረዥ 5ን ይመልከቱ።

## 4.1.4. ተማሪዎች ለመማሪያ መፅሐፉ ያላቸው አመለካከት

በዚህ ንኡስ ስር ተማሪዎች ለመማሪያ መጽሐፉ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል በዝርዝር ይቀርባል።

ሠንጠረዥ 6፡ ተማሪዎች ለመማሪያ መጽሐፉ ያላቸው አመለካከት

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | % | 4 | % | 3 | % | 2 | % | 1 | % | |
| 3 | የመማሪያ መጽሐፍን የሚመለከቱ ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | |
| 3.1 | የአማርኛ መማሪያ መጽሐፌን እንደ ሌሎቹ መጻሕፍት ሁሉ እወደዋለሁ። | 24 | 20.0 | 19 | 15.8 | 14 | 11.8 | 19 | 15.8 | 44 | 36.6 | 2.67 |
| 3.2 | የመማሪያ መጽሐፉ በጥሩ ሁኔታ ስለተዘጋጀ በአማርኛ ፈተና ጥሩ ውጤት እንዳመጣ ረድቶኛል። | 12 | 10.8 | 31 | 25.8 | 14 | 11.8 | 43 | 35.8 | 19 | 15.8 | 2.76 |
| 3.3 | በአማርኛ ትምህርት ውስጥ የተካተቱት አወዛጋቢ ይዘቶች የዕውቀት አድማሴን ለማስፋት ረድተውኛል። | 24 | 20.0 | 36 | 30.2 | 26 | 21.6 | 26 | 21.6 | 8 | 6.6 | 3.35 |
| 3.4 | አሁን ያለው የመማሪያ መጽሐፍ በአዲስ ቢለወጥ ደስ ይለኛል። | 62 | 51.6 | 16 | 13.3 | 12 | 10.0 | 16 | 13.3 | 14 | 11.8 | 3.80 |
| 3.5 | የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ በርካታ የሰዋሰው ደንቦችን ቢይዝ ደስ ይለኛል። | 64 | 53.4 | 31 | 25.8 | 9 | 7.5 | 9 | 7.5 | 7 | 5.8 | 4.13 |
| 3.6 | የመማሪያ መጽሐፉ ይዘት ለብሔራዊ መግቢያ ፈተና ለማዘጋጀት አላገዘኝም። | 14 | 11.8 | 24 | 20.0 | 19 | 15.8 | 19 | 15.8 | 44 | 36.6 | 3.46 |

በተራ ቁጥር 3.1 በሠንጠረዥ 6 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 24 (20.0%) በጣም እስማማለሁ፣ 19 (15.8%) እስማማለሁ፣ 14 (11.8%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 19 (15.8%) አልስማማም፣ 44 (36.6%) በጣም አልስማማም በማለት መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡም 2.67 ነው ለዚህ ጥያቄ 35.8% አዎንታዊ፣ 52.4 % አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ስለዚህ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች (52.4%) የአማርኛ መጽሐፋቸውን እንደሌሎቹ መጻህፍት የማያነቡ መሆናቸውን መረጃው አረጋግጧል። ከመምህራን ጋር በተደረገው ውይይትም አብዛኛዎቹ መምህራን

የመማሪያ መጽሐፉ የተማሪዎቹን ፍላጎት የሚያረካ አይደለም በማለት አስተያየታችውን ሰጥተዋል። አብዛኞቹ ተማሪዎች የመማሪያ መጻሐፉን የማንበብ ፍላጎት እንደሌላቸው ከመምህራን ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ማረጋገጥ ተችሏል።

ለምሳሌ መምህር 1፡ "ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፉን ይጠሉታል። ለማንበብ አይፈልጉም። የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ አይደለም።"

መምህር 3፡ የመጽሐፉ ይዘት ጥሩ ነው ነገር ግን የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ አይደለም። ሳቢና ማራኪ አይደለም በማለት አስተያየቱን አቅርቧል። አብዛኞቹ መምህራን የመማሪያ መጽሐፉ በባለሙያ የተዘጋጀ አይደለም በማለት አስተያየታቸውን አቅርበዋል።" ስለዚህ የመማሪያ መጽሐፉ ችግር ስላለበት የሚመለከተው ክፍል ችግሩን ፈትሾ የማሻሻያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል።

በተራ ቁጥር 3.2 በሠንጠረዥ 6 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 12 (10.8%) በጣም እስማማለሁ 31 (25.8%) እስማማለሁ፣ 14 (11.7%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 43 (35.8%) አልስማማም፣ 19 (15.8%) በጣም አልስማማም በማለት መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡም 2.76 ነው። ስለዚህ 51.7% የሚሆኑት ሀሳቡን በመቃወም አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ 36.6% የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህን ጥያቄ 51.7% የሚሆኑት ተማሪዎች ተቃውመወታል። ከዚህ የምንረዳው የመማሪያ መጽሐፉ በጥሩ ሁኔታ አለመዘጋጀቱን ነው።

ለምሳሌ መምህር 4፡ የመማሪያ መጽሐፉ ሳቢነት ስሌለው ተማሪዎች ለማንበብ ፍላጎት የላቸውም።

መምህርት 6፡ "የመጽሐፉ ይዘት ከተማሪዎቹ አቅም በላይ ነው። ስለዚህ ተማሪዎች ለማንበብ ፍላጎት የላቸውም።" ከተማሪዎቹ የተሰጠው ምላሽና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የቀረበው ሀሳብ የሚያመለክተው የመማሪያ መጽሐፉ በጥሩ ሁኔታ አለመዘጋጀቱን ነው። ስለዚህ የመማሪያ መጽሐፉ ተሻሽሎ መዘጋጀት አለበት።

በተራ ቁጥር 3.3 በሠንጠረዥ 5 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 24 (20%) በጣም እስማማለሁ፣ 36 (30.2%) እስማማለሁ፣ 26 (21.6%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 26

(21.6%) አልስማማም፣ 8 (6.6%) በጣም አልስማማም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.35 ነው፡፡ በቀረበው ሀሳብ ላይ 50.2% የሚሆኑት ተማሪዎች አዎንታዊ፣ 28.2% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች ዕወቀታችውን ለማዳበር አስተዋጽኦ እንዳደረጉላቸው ገልፀዋል፡፡

ለምሳሌ መምህር 5፡ "የመማሪያ መጽሐፉ ይዘት አራቱን ክሂሎች ለማስተማር የሚያግዝ ነው፡፡"

መምህር 2፡ "የመማሪያ መጽሐፉ ደረቅ እውነታን ብቻ የያዘ ነው፡፡ የልቦለድ ስራዎች የሉትም፡፡ ስለዚህ ተማሪዎችን አያንቀሳቅሰም፡፡"

መምህር 1፡ "የመማሪያ መጽሐፉ ይዘት ጥሩ ቢሆንም አንዳንዱ ይዘት ግን ከተማሪዎቹ አቅም በላይ ነው፡፡"

በአጠቃላይ ከተማሪዎቹ የተሰጠው ምላሽና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው ውጤት የሚሳየው የመጽሐፉ ይዘት ጥሩ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኘው ይዘት ጥሩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ይዘቶች ከተማሪዎች አቅም በላይ ስለሆኑ ተሻሽለው ሊቀርቡ ይገባል፡፡

በተራ ቁጥር 3.4 በሠንጠረዥ 6 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 62 (51.6%) በጣም እስማማለሁ፣ 16 (13.3%) እስማማለሁ፣ 12 (10.0%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 16 (13.3%) አልስማማም፣14 (11.8%) በጣም አልስማማም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥብ 3.80.ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ 64.9% የሚሆኑት ተማሪዎች አዎንታዊ፣ 25.1% የሚሆኑት ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ አብዘኛዎቹ ተማሪዎች 64.9% የሚሆኑት የመማሪያ መጽሐፉ በአዲስ መልክ ቢለወጥ የሚደግፉ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ከመምህራንም ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ መምህራን የመማሪያ መጽሐፉ በባለሙያ የተዘጋጀ እንዳልሆነና ችግር ያለበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ለምሳሌ መምህር 5፡ "የመማሪያ መጽሐፉ ችግር አለበት፣ መካተት ያለበትን ይዘት አላካተተም፡፡ ለምሳሌ የልቦለድ ጽሁፎች የሉትም፡፡ በግሌ አንዳንድ ጽሑፎችን

እያመጣሁ ለተማሪዎች እነብላቸዋለሁ። በተረፈ መጽሐፉ በባለሙያዎች የተዘጋጀ አይደለም።"

መምህር 2፡ "የመማሪያ መጽሐፉ ተማሪዎች ደስ ብሏቸው የሚያነቡት አይደለም። ብዙ የልቦለድ ስራዎች የሉትም። ከዚህ ይልቅ ደረቅ እውነታን ብቻ የሚያንፀባርቅ ነው። ስለዚህ የመማሪያ መጽሐፉ በአዲስ መልክ መዘጋጀት አለበት።" የመማሪያ መጽሐፉ በርካታ ችግሮች እንዳሉበት ከተማሪዎቹ የተሰጠው ምላሽና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው ውጤት አመልክቷል። ስለዚህ የመማሪያ መጽሐፉ የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ በአዲስ መልክ ተሻሽሎ መዘጋጀትና መለወጥ አለበት።

በተራ ቁጥር 3.5 በሠንጠረዥ 6 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 64 (53.4%) በጣም እስማማለሁ፣ 31 (25.8%) እስማማለሁ፣ 9 (7.5%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 9 (7.5) አልስማማም፣ 7 (5.8%) በጣም አልስማማም በማለት መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡም 4.13 ነው። ለዚህ ጥያቄ አብዛኞዎቹ ተማሪዎች 79.2% በመደገፍ አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ 13.3% የሚሆኑት ደግሞ አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። ስለዚህ አብዛኞዎቹ 79.2% ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በዛ ያሉ የልቦለድ ሥራዎች ቢካተቱ ደስተኛ እንደሚሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

ለምሳሌ መምህርት 6፡ የመማሪያ መጽሐፉ ተማሪዎችን የሚያዝናና የልቦለድ ስራዎች የሉትም። ይህ መጽሐፍ መለወጥ አለበት። ከተማሪዎች የተሰጠው ምላሽና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው ውጤት የመማሪያ መጽሐፉ ችግር እንዳለበት አመልክቷል። ስለዚህ የመማሪያ መጽሐፉ የተማሪዎቹን ፍላጎት መሰረት አድርጎ መዘጋጀት አለበት።

በተራ ቁጥር 3.6 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 14 (11.8%) በጣም እስማማለሁ፣ 24 (20.0%) እስማማለሁ፣ 19 (15.8%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 19 (15.8%) አልስማማም፣ 44 (36.6%) በጣም አልስማማም በማለት መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡም 3.46 ነው። ለዚህ ጥያቄ 31.6% የሚሆኑት ተማሪዎች አዎንታዊ፣ 52.4% አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። ለቀረበው ጥያቄ 52.4% የመሆኑ በተማሪዎች ሀሳቡን

በመቃወም አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ አብቸኛዎቹ ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፉ ይዘት ጠቃሚ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ለምሳሌሌ መምህር 4፡ "የመማሪያ መጽሐፉ ይዘት ጥሩ ነው፡፡ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ለማስተማር ይረዳል፡፡ ነገር ግን መጽሐፉ በየጊዜው ሊሻሻል ይገባል በማለት አስተያየቱን አቅርቧል፡፡"

መምህር 5፡ "በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች ጥሩ ናቸው፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች መጽሐፉን የማንበብ ፍላጎት የላቸውም፡፡" ከተማሪዎች የቀረበው ምላሽና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው ውጤት በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች ለተማሪዎቹ ጠቃሚ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያሉት ይዘቶች አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ መምህራን እነዚህን ይዘቶች በየጊዜው እያሻሻሉ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡ ለዝርዝሩ ሠንጠረዥ 6ን ይመልከቱ፡፡

ከመምህራን ጋር በተካሄደው ቃለ መጠይቅም ወቅት አብዛኛዎቹ መምህራን የመማሪያ መጽሐፉ ይዘት አራቱን ክሂሎች ለማስተማር ያግዛል በማለት አስተያየታቸውን አቅርበዋል፡፡ ስለዚህ ከተማሪዎች የቀረበው ምላሽና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው ውጤት ተደጋጋፊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የመማሪያ መጽሐፉ ይዘት ለተማሪዎቹ የሚጠቅም መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ለዝርዝሩ ሰንጠረዥ 6ን ይመልከቱ፡፡

በአጠቃላይ መማሪያ መጽሐፉን በተመለከተ ተማሪዎች አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፉ በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ስዚህ ተላውጦ ተማሪዎች አዎንታዊ አመለካከት አሳይተዋል፡፡ ለመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት ጥያቄዎች ድምር አማካይ ነጥብ 3.36 ነው፡፡

## 4.1.5. ተማሪዎች ወላጆቻቸውና ጓደኞቻቸው ስለ አማርኛ በሚሰጡት አስተያየቶች ላይ

በዚህ ንኡስ ርእስ ስር ተማሪዎች ወላጆቻቸውና የትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው ስለ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል በዝርዝር ይቀርባል።

ሠንጠረዥ 7፡ ተማሪዎቹ ወላጆችና ጓደኞቻቸው ስለ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመላካከት

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | % | 4 | % | 3 | % | 2 | % | 1 | % | |
| 4 | የተማሪዎቹን ወላጆችና ጓደኞቻቸውን የሚመለከቱ ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | |
| 4.1 | ወላጆቼ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ አመለካከት አላቸው። | 32 | 26.7 | 36 | 30.0 | 32 | 26.7 | 12 | 10.0 | 8 | 6.6 | 3.35 |
| 4.2 | ጓደኞቼ ለሌሎች ትምህርት የሚጨነቁትን ያህል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እምብዛም ትኩረት አይሰጡትም። | 54 | 45.0 | 36 | 30.0 | 8 | 6.6 | 20 | 16.7 | 2 | 1.7 | 4.00 |

በተራ ቁጥር 4.1 ሠንጠረዥ 7 ለቀረበው ጥያቄ 32 (26.7%) በጣም እስማማለሁ፣ 36 (30.0%) እስማማለሁ፣ 32 (26.7%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 12 (10.0%) አልስማማም፣ 8 (6.6%) በጣም አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡም 3.35 ነው። በዚህ በቀረበው ሀሳብ ላይ 68% አዎንታዊ፣ 20% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህ የምንገነዘበው 68%የሚሆኑ ተማሪዎች ወላጆቻችው ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ አመለካከት እንዳላቸው ገልጸዋል። ከመምህራን ጋር በተካሄደው ቃለመጠይቅ ወላጆች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝቅተኛ አመለካከት አላቸው በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ለምሳሌ መምህር 3፡ "ወላጆች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ አመለካከት የላቸውም። ከአማርኛ ቋንቋ ይልቅ ለእንግሊግዘኛ ቋንቋ ትልቅ አክብሮት አላቸው፤ ልጆቻቸው አማርኛ ከሚናገሩ ይልቅ እንግሊዝኛ ቋንቋ ቢናገሩ ይመርጣሉ። በጣም አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለነው በማለት አስተያየቱን ሰንዝሯል።"

መምህር 4 "አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍልና ወላጆች ለእንግሊዝኛ ቋንቋና ለውጭው ባህል ከፍተኛ ፍቅር አላቸው፤ በራሳቸው ቋንቋ ለመናገር ያፍራሉ። ስለዚህ ለአማርኛ ቋንቋም ሆነ ለትምህርቱ ትኩረት አይሰጡትም፤ ልጆቻቸውም ከአማርኛ ቋንቋ ይልቅ እንግሊዝኛ ቋንቋ ቢናገሩ ይመርጣሉ።" አብዛኛዎቹ መምህራን ወላጆች ልጆቻቸውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን እንዲማሩ አያበረታቷቸውም በማለት መልስ ሰጥተዋል።" ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽና ከመምህራን ጋር በተደረገው ውይይት ወላጆች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምንም አይነት ትኩረት እንደማይሰጡት ለማረጋገጥ ተችሏል።

ይህ ጉዳይ በጣም አሳሳቢ ስለሆነ ወላጆች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ትኩረት ሊሰጡት ይገባል። ልጆቻቸውም የአማርኛን ቋንቋ ትምህርት እንዲማሩ ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል።

በተራ ቁጥር 4.2 በሰንጠረዥ 7 ለቀረበው ጥያቄ 54 (45.0%) በጣም እስማማለሁ፣ 36 (30.0%) እስማማለሁ፣ 8 (6.6%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 20 (16.7%) አልስማማም፣ 2 (1.7%) በጣም አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡም 4.00 ነው። በዚህ ሀሳብ ላይ 75% ተማሪዎች አዎንታዊ፣ 18.4% ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። በመረጃው መሰረት 75% ተማሪዎች ሀሳቡን ደግፈውታል። ስለዚህ የተማሪዎቹ ጓደኞች ለአማርኛ ቋንቋ ምንም ትኩረት እንደማይሰጡት ለመገንዘብ ተችሏል።

መምህር 4 "አብዛኛው የህብረተሰብ፣ ክፍልና ወላጆች ለእንግሊዝኛ ቋንቋና ለውጭው ባህል ከፍተኛ ፍቅር አላቸው። በራሳቸው ቋንቋ መናገር አይፈልጉም። ስለዚህ ለአማርኛ ቋንቋ ትኩረት አይሰጡትም፣ ልጆችችውም ከአማርኛ ቋንቋ ይልቅ እንግሊዝኛ ቋንቋ ቢናገሩ ይደሰታሉ።" አብዛኛዎቹ መምህራን ወላጆች ልጆቻቸውን የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት እንዲማሩ አያበረታቷቸውም በማለት መልስ ሰጥተዋል።

ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽና ከመምህራን ጋር በተደረገው ውይይት ወላጆች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምንም አይነት ትኩረት እንደማይሰጡት ለማረጋገጥ ተችሏል። በዚህ ተላውጦ ስር ለቀረቡት ሁለት ጥያቄዎች ወላጆችም ሆኑ የተማሪዎች ጓደኞች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሉታዊ አመለካከት እንዳላቸው ጥናቱ አረጋግጧል። ይህ ሁኔታ በተማሪዎቹ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል። የዚህ ተላውጦ አማካይ ነጥብ 3.68 ነው።

## 5. ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት ያላቸው አመለካከት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ፈተና ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል በዝርዝር ይቀርባል።

ሠንጠረዥ 8፡ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት ያላቸው አመለካከት

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | % | 4 | % | 3 | % | 2 | % | 1 | % | |
| 5 | የፈተና ውጤትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | |
| 5.1 | በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዘወትር ውጤቴ ዝቅተኛ ነው። | 6 | 5.0 | 14 | 11.7 | 2 | 1.6 | 42 | 35.0 | 56 | 46.7 | 4.07 |
| 5.2 | የአማርኛን ትምህርት አጠናሁ፣ አላጠናሁ የፈተና ውጤቴ ጥሩ ነው። | 16 | 13.3 | 24 | 20.0 | 24 | 20.0 | 24 | 20.0 | 32 | 26.7 | 3.27 |
| 5.3 | የአማርኛ ቋንቋ የአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ስለሆነ አውቀዋለሁ በማለት ለፈተና አላጠናውም። | 12 | 10.0 | 16 | 13.3 | 16 | 13.3 | 38 | 31.7 | 38 | 31.7 | 3.62 |

በሠንጠረዥ 8 ተራ ቁጥር 5.1 ለቀረበው ጥያቄ 6 (5.0%) በጣም እስማማለሁ፣ 14 (11.7%) እስማማለሁ፣ 2 (1.6%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 42 (35.0%) አልስማማም፣ 56 (46.7%) በጣም አልስማማም በማለት መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡም 4.07 ነው። በዚህ ሀሳብ ላይ 16.7% ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 81.7% ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።

አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 81.7% የሚሆኑት ይህን ሀሳብ ተቃውመውታል። ስለዚህ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ጥሩ ውጤት እንደሚያመጡ ለመገንዘብ ተችሏል። ከመምህራን ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ወቅት አብዛኛዎቹ መምህራን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የፈና ውጤታቸው በጣም ጥሩ ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል።

ለምሳሌ መምህር 5፡ "የአብዛኛዎቹ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት ጥሩ ነው። ማለፊያ ማርክ ያመጣ።"
መምህር 2፡ "የአብዛኛዎቹ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት ጥሩ ነው። ከጥቂት ተማሪዎች በስተቀር አብዛኛዎቹ በጥሩ ውጤት ፈተናውን ያልፋሉ።" ከተማሪዎቹ የተገኘው ምላሽና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው ውጤት አብዛኞቹ የመሰናዶ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ማለፊያ ማርክ እንደሚያመጡ አመልክቷል። ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳን ውስጥ እንደተገለፀው ተማሪው ለቋንቋው አዎንታዊ አመለካከት ካለው ቋንቋውን የመማር ፍላጎት ይኖረዋል። ፍላጎት ካለው ደግሞ በትምህርቱ ጥሩ ውጤት ያመጣል Spolsky (1990)።

በተራ ቁጥር 5.2 በሰንጠረዥ 8 ለቀረበው ጥያቄ 16 (13.3%) በጣም እስማማለሁ፣ 24 (20.0%) እስማማለሁ፤ 24 (20.0%) ለመወሰን እቸገራለሁ ለ24 (20.0%) አልስማማም 32 (26.7) በጣም አልስማማም ከመላሾቹ በማለት መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡም 3.27 ነው። ለቀረበው ጥያቄ 33.3% የሚሆኑት አዎንተዊ መልስ ሲሰጡ 46.7% የሚሆኑት ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ተሰጥተዋል። ውስጥ 46.7% የሚሆኑ ተማሪዎች ሀሳቡን ተቃውመውታል። ስለዚህ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ጊዜ እንደ ሌሎቹ ትምህርቶች ሁሉ የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት አጥንተውና ተዘጋጅተው እንደሚመጡ ተረጋግጧል። ከመምህራን ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ወቅት ተማሪዎች በፈተና ጊዜ የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት አጥንተው እንደሚመጡ ለማረጋገጥ ተችሏል።

ለምሳሌ መምህር 4፡ "ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት አያጠኑትም በፈተና ውጤታቸው ግን ጥሩ ማርክ ያመጣሉ።"

መምህር 1፡ "የአብዛኛዎቹ ተማሪዎች የፈተና ውጤት ጥሩ ነው።" ስለዚህ ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው ውጤት

ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት አጥንተው፣ ለፈተና ተዘጋጅተው እንደሚመጡ ለማረጋገጥ ተችሏል።

ከዚህ የምንገነዘበው የመሰናዶ ተማሪዎች በፈተና ጊዜ የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት እንደሌሎቹ የትምህርት አይነቶች አጥንተው፣ ተዘጋጅተው ይመጣሉ።

በተራ ቁጥር 5.3 በሰንጠረዥ 8 ለቀረበው ጥያቄ 12 (10.0%) በጣም እስማማለሁ፣ 16 (13.3%) እስማማለሁ፣ 16 (13.3%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 38 (31.7%) አልስማማም፣ 38 (31.7%) በጣም አልስማማም በማለት መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡ 3.62 ነው። ለቀረበው ጥያቄ 28% ተማሪዎች አዎንታዊ፣ 76% ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። በመረጃው መሰረት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 76% ሀሳቡን ተቃውመዋል። ስለዚህ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ነው በማለት ሳይንቁት ለፈተና አጥንተው፣ ተዘጋጅተው እንደሚመጡ ለማረጋገጥ ተችሏል። ከመምህራንም ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ወቅት አብዛኛዎቹ መምህራን፣ ተማሪዎች በፈተና ጊዜ የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት አጥንተው እንደሚመጡ አረጋግጠዋል።

ለምሳሌ መምህር 2፡ "እኔ በማስተምረው ክፍል ከጥቂቶቹ በስተቀር አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለፈተና ተዘጋጅተውና አጥንተው ይመጣሉ።"

መምህር 1፡ "አብዛኞቹ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ጊዜ በደንብ አጥንተውና ተዘጋጅተው ይመጣሉ።"

ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽና ከመምህራን ጋር በተካሄደው ቃለ መጠይቅ ተማሪዎች በፈተና ጊዜ የአማርኛ ቋንቋን አጥንተው እንደሚመጡ በጥናቱ ተረጋግጧል።

ስለዚህ የመሰናዶ ተማሪዎች አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋችን ነው በማለት ሳይንቁት በፈተና ጊዜ የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት አጥንተውና ተዘጋጅተው ይመጣሉ።

አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው በጥናቱ ተረጋግጧል። የዚህ ተላውጦ አማካይ ነጥቡም 3.65 ነው። ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ሰንጠረዥ 8ን ይመልከቱ።

## 6. የአመለካከትና የፈተና ውጤት ዝምድና

የጥናቱ ዋና ዓላማ የተማሪዎች አመለካከትና የፈተና ውጤት ዝምድና አለው ወይስ የለውም የሚለውን ለማረጋገጥ ሲሆን እዚህ ውጤት ላይ ለማድረስ የተለያዩ ዘዴዎችና መሳሪያዎች አገልግሎት ላይ ውለዋል።

በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን ውስጥ ተማሪዎች ለቋንቋውና ለትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት ካላቸው ጥሩ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ አሉታዊ አመለካከት ካላቸው ደግሞ ዝቅተኛ ውጤት እንደሚያመጡ የምሁራን ጥናቶች እንዳረጋገጡ ተገልጿል (Gardner, 1985፡41)።

በዚህ ጥናትም እነዚህ ከዚህ በላይ የቀረቡት ሀሳቦች ትክክለኛ መሆናቸው ተረጋግጧል። ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ የሆነ አመለካከት አላቸው። እንደ መለኪያ በቀረቡት በተላውጦ አንድ ውስጥ በቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች ጥሩ አመለካከት እንዳላቸው የተጠናቀረው መረጃ ያስረዳል ሰንጠረዥ '4'ን ይመልከቱ። ተማሪዎች ለቋንቋው ያላቸው አመለካከት በሶስቱም የመሰናዶ ትህርት ቤቶች የእያንዳንዱን ተማሪ የአመለካከት ውጤት ስንመለከት በሁሉም ትምህርት ቤቶች ላይ አዎንታዊ አመለካከት ታይቷል። ተማሪዎች ለቋንቋው ያላቸውን አመለካከት ከፈተና ውጤታቸው ጋር በንጽጽር ሲታይ የአብዛኛዎቹ ተማሪዎች ተስማሚ ሆኖ ተገኝቷል። አባሪ 5ን ይመልከቱ። በተዛምዶ ስልት ቀመር /Correlation/ ውስጥ በማስገባት የፈተናው ውጤት ከአጠቃላይ የተማሪዎች አመለካከት ጋር በማዛመድ በስሌት የተገኘው ውጤት አመርቂ መሆኑ ተረጋግጧል። አባሪ "5"ን ይመልከቱ። በዚህ ትንታኔ ውስጥ የፈተናው ውጤት የተማሪዎች የአንደኛ ወሰነ ትምህርት የአማርኛ ፈተና ውጤት ሲሆን የአመለካከቱ ደግሞ የ120ዎቹ ተማሪዎች ለ39ኙ ጥያቄዎች በተናጠል ያስመዘገቡት አማካይ ነጥቦች ተወስደዋል።

የተማሪዎች አጠቃላይ አመለካከት አማካይና የአንደኛ ወሰነ ትምህርት በክፍል መምህራን የተሰጡ ፈተናዎች አማካይ ውጤት ተቀናጅተው ሲሰሉ 0.42 የተዛምዶ ውጤት አስገኝተዋል። የዚህ ተዛምዶ ውጤት በአመለካከታቸውና በፈተና ውጤታቸው መካከል ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ጥምረት ያሳየ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል። በ"ቲ" ዋጋ /t-value/ መፈለጊያ ቀመር ሲሰላ ውጤቱ 0.00 ፋይዳ ያለው

ሆኖ ተገኝቷል። ይህም ማለት የተማሪዎቹ አመለካከትና ያስመዘገቡት የፈተና ውጤት መካከል ከፍተኛ ዝምድና አለው ማለት ይቻላል። ለዝርዝሩ አባሪ "5"ን ይመልከቱ።

# ምዕራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች

በዚህ ክፍል የጥናቱ ማጠቃለያ የጥናቱ ግኝትና አስተያየቶች ይቀርባሉ፡፡

### 5.1. ማጠቃለያ

ለዚህ ጥናት መካሄድ እንደ መነሻ ሀሳብ የሆነው ‹‹ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት እየቀነሰ መምጣት በውጤታቸው ላይ ተጽእኖ ይኖረው ይሆን?›› የሚለውን መላምት መሰረት በማድረግ በተማሪዎች አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለውን ዝምድና መመርመር የሚለውን አጠቃላይ አላማ መነሻ አድርጎ ነው፡፡ ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸው የሶስት የመሰናዶ ትምህርት ቤት የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡

ተጠኚ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፣ ለመምህሩና ለመማሪያ መጽሐፉ ያላቸውን አመለካከት ለመለካት እንዲሁም የተማሪዎቹ ወላጆች፣ ጓደኞቹና ህብረተሰቡ፣ ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርት ላይ የሚኖራቸው አመለካከት ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ ለመመርመር የሚያስችሉ የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡

ጥናቱ ከአጠቃላይ አላማው እንዲደርስ በመጠይቆቹ አማካይነት መልስ የሚሹ ዝርዝር ጥያቄዎች ነበሩት፡፡

- የመሰናዶ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ምን ይመስላል?
- ተማሪዎች ለመማሪያ መጽሐፉ ያላቸው አመለካከት ምንድነው?
- የተማሪው ወላጆች፣ ጓደኞቹና ማህበረሰቡ በተማሪው አመለካከት ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ምን ያህል ነው?
- የተማሪዎች አመለካከት በፈተና ውጤታቸው ላይ ምን ያህል ተፅዕኖ ይኖረው ይሆን?
- ተማሪዎች ለመምህራቸውና ለማስተማር ስልቱ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የመነሻ ጥያቄዎችና ዝርዝር አላማዎቹን ለመመርመርና ለመተንተን በቅድሚያ የተማሪዎች አመለካከት መለየት ነበር። በዚህም መሰረት በሊከርት የአፃፃፍ ስልት በቀረቡት መጠይቆች እያንዳንዱ ተማሪ በሰላሳ ዘጠኙ ጥያቄዎች ያስመዘገበው ውጤት እንዲሁም አንድ መቶ ሃያ ተማሪዎች ለያንዳንዱ ጥያቄ ያስመዘገቡት አመለካከት አማካይ ውጤት ተለይቷል። መጠይቁን የሞሉት ተማሪዎች ከቀረበላቸው አምስት ተውላጦች ውስጥ ለቋንቋውና ለትምህርቱ (3.84) አማካይ ነጥብ በማስመዝገብ አዎንታዊ አመለካከት ታይቷል። ሌላው ደግሞ ለመምህሩ (3.82)፣ ለመማሪያ መጽሐፉ (3.36) ለወላጆቻቸውና ለጓደኞቻቸው (3.68) እና ለፈተና ውጤት (3.65) አማካይ ነጥብ ተመዝግቧል። የእነዚህ ተላውጦዎች ድምር ውጤት የተገኘው የተማሪዎች አጠቃላይ የአመለካከት ውጤት አዎንታዊ ሆኖ ተገኝቷል። ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸው የተጠቃለለ አዎንታዊ አመለካከት ሰንጠረዥ "4" ያመለክታል። ይህ ውጤት ከፍ ሲል ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ አስገኝቷል።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ለመምህራን በመቅረፀ-ድምፅ ተቀርፆ በቀረበው ቃለ-መጠይቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት መልስ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ለቃለ-መጠይቅ የቀረቡት ስድስት መምህራን ሲሆኑ ጥያቄዎቹም በአምስት ተውላጦዎች ተከፍለው ቀርበዋል።

- መምህራን ለቋንቋውና ለትምህርቱ ያላቸውን አመለካከት የሚጠይቁ፣
- መምህራን ለመማሪያ መጽሐፉ ያላቸውን አመለካከት የሚጠይቁ፣
- መምህራን ለሙያቸው ያላቸውን አመለካከት የሚጠይቁ፣
- መምህራን ለትምህርት ቤቶች ርእሳነ መምህራን ያላቸውን አመለካከት የሚጠይቁ፣
- መምህራን ለተማሪዎቻቸው የፈተና ውጤት ያላቸውን አመለካከት የሚጠይቁ ናቸው።

ከዚህ በላይ የቀረቡት ጥያቄዎች መምህራን ስለ ተማሪዎቻቸው አመለካከት ምስረታ ደጋፊ ሀሳብ ለማገኘት ነው።

በዚህም መሰረት መምህራን ለቋንቋውና ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ (83.3%) መሆኑ ተመዝግቧል፡፡ ለመማሪያ መጽሐፉ አሉታዊ (66.7%) አመለካከት፣ ለሙያዊ ስልጠና አሉታዊ (66.7%) አመለካከት፣ ለመሰናዶ ትምህርት ቤት ርእሳነ መምህራን ስድስቱም ተጠኚ መምህራን አሉታዊ አመለካከት (100%) አሳይተዋል፡፡ ለተማሪዎች የፈተና ውጤት በከፍተኛ ደረጃ አዎንታዊ አመለካከት (83.3%) ያላቸው መሆኑን በተደረገው ቃለ-መጠይቅ /interview/ ተረጋግጧል፡፡ ከመቅረፀ ድምጽ በጽሁፍ የተገለበጠውን የተጠቃለለ መረጃ አባሪ 3ን ይመልከቱ፡፡

በተማሪዎችና በመምህራን አመለካከት መካከል በተደረገው ንጽጽር በተወሰኑ ጥያቄዎች ላይ በቀረቡት መልሶች ልዩነት ታይቷል፡፡ መምህራን የሙያ ማሻሻያ ስልጠና እና ለመማሪያ መጽሐፉ አሉታዊ አመለካከት እንዳላቸው ታይቷል፡፡ በተለይ ደግሞ የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራን ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ዝቅተኛ አመለካከት እንዳላቸው ሁሉም ተጠኚ መምህራ (100%) በቃለ-መጠይቁ ወቅት አረጋግጠዋል፡፡ መምህራን ለቋንቋውና ለትምህርቱ እንዲሁም ለተማሪዎቹ የፈተና ውጤት አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ተመዝግቧል፡፡ በተካሄደው የክፍል ምልከታ ወቅት የተገኘው ውጤትም ይህንኑ ያጠናክራል፡፡ የጥናቱ ዋና ክፍል የሆነውን የተማሪዎቹ አመለካከትና ውጤት ዝምድና ለመመርማር ከሁሉም ተጠኚ ተማሪዎች በተገኘው የአመለካከትና የፈተና ውጤቶች መካከል ስታስቲካዊ ንጽጽር ተደርጓል፡፡ የፈተናው ውጤት ከሶስቱ መሰናዶ ትምህርት ቤቶች የአንደኛው ወሰነ ትምህርት ፈተና በክፍል መምህር የተሰጠው ነው፡፡ የተማሪዎቹ የአመለካከት አማካይ ውጤትና የፈተናው አማካይ ውጤት በስታስቲክስ ተዛምዶ ቀመር ውስጥ ገብቶ ሲሰላ 0.00 ውጤት አስገኝቷል፡፡ ይህ የ"ቲ" ዋጋ የተገኘው ውጤት በጣም ከፍተኛ አዎንታዊ በመሆኑ በተማሪዎቹ አመለካከትና በፈተና ውጤታቸው መካከል ከፍ ያለ ዝምድና እንዳለ በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከተማሪዎቹ የተገኘው አጠቃላይ የአመለካከት አማካይ ነጥብ (121.88) እንዲሁም የሁሉም ተማሪዎች የፈተናቸው ድምር አማካይ ውጤት (71.68) ሲሆን የ‹‹ቲ›› ፋይዳ 0.00 ነው፡፡ ስለዚህ የጥናቱ ማጠቃለያ ከፍተኛ አዎንታዊ አመለካከት ከከፍተኛ የማለፊያ ውጤት ጋር ዝምድና አሳይቷል ለማለት አስችሏል፡፡ ይህ ውጤት ተማሪዎቹ በሁሉም ተላውጦዎች ያስመዘገቡት አዎንታዊ አመለካከት፣

መምህራኑም በቃለ-መጠይቅ ወቅት በሁለት ተላውጦዎች አዎንታዊ አመለካከት ማስመዝገባቸውን፣ በክፍል ምልከታም የመምህራን የማስተማር ችሎታ ላቅ ያለ መሆኑን፣ እንዲሁም የተማሪዎቹ የክፍል ተሳትፎ ከፍተኛ መሆኑ የሚጠበቅ ውጤት አስገኝቷል፡፡

በዚህ መሰረት በተማሪዎቹ አመለካከትና በፈተና ውጤታቸው መካከል ከፍ ያለ ዝምድና መኖሩን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

የተገኘው ውጤት ‹‹ተጠኚ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት በውጤታቸው ላይ ተጽእኖ ይኖረው ይሆን?›› የሚለው መነሻ መላምት ስህተት መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው ተጠኚ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ቀና አመለካከት ያላቸው መሆኑን እንዲሁም በአማርኛ ቋንቋ የፈተና ውጤታቸው ከፍተኛ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም በክለሳ ድርሳናት ከተጠቀሱት ምሁራን ስራዎች ጋር ተስማሚ ሆኖ ተገኝቷል ማለት ያስችላል፡፡ የቀረቡትም ስታስቲካዊ ስሌቶች ይህንኑ ያረጋግጣሉ፡፡

## 5.2. የጥናቱ ግኝቶች

የጥናቱን ዓላማ መነሻ በማድረግ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ምሁራን በሰጡት አስተያየት በመመስረት በተካሄደው ጥናትና በተሰሩት ስታስቲካዊ ስሌቶች የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

1. ተማሪዎቹ ለቋንቋውና ለትምህርቱ፣ ለመማሪያ መጽሐፉ፣ ለመምህሩ እንዲሁም ለተማሪዎቹ አመለካከት ምስረታ ወላጆችና ማህበረሰብን በሚለኩ የተማሪዎች መጠይቅ ውጤት የሚከተሉት ግኝቶች ላይ ተደርሷል፡፡ ከቀረቡት አምስት ተላውጦዎች ውስጥ ተማሪዎቹ ለመምህሩ፣ ለመማሪያ መጽሐፉና፣ ለፈተና ውጤታቸው አዎንታዊ አመለካከት አስመዝግበዋል፡፡ እንዲሁም የተማሪው ወላጆች አዎንታዊ አመለካከት ሲኖራቸው ለጓደኞቻቸው አሉታዊ መሆኑ ታይቷል፡፡ በነዚህ ተላውጦች መሰረት በጥናቱ የታቀፉት ተማሪዎች አጠቃላይ አመለካከት ድምር አማካይ ውጤት ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት አሳይተዋል፡፡

2. በአመለካከትና በፈተና ውጤታቸው መካከል ስላለው ተዛምዶ በተደገው ስታስቲካዊ ቀመር ፋይዳ ያለው ተዛምዶ መኖሩን ስሌቱ አሳይቷል፡፡
3. የሁሉም ተጠኝዎች የፈተና ውጤትና ለቋንቋውና ለትምህርቱ የተመዘገበው አመለካከት ድምር አማካይ ውጤት አዎንታዊ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ውጤት "በጥናቱ የተሳተፉት ተማሪዎች ለውጤታቸው ከፍተኛ መሆን ምክንያቱ ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው አመለካከት ነው፡፡" የሚለውን መላምት መልሷል፡፡
4. መምህራን በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ /interview/ ተማሪዎቻቸው ለአማርኛ ቋንቋ ጥሩ አመለካከት እንዳላቸው አረጋግጠዋል፡፡ ለመማሪያ መጽሐፉ ሁለት መላሾች አዎንታዊ አመለካከት ሲኖራቸው፣ ሶስቱ መላሾች አሉታዊ አመለካት እንዳላቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ስለዚህ አብዛኛዎቹ መምህራን ለመማሪያ መጽሐፉ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ተረጋግጧል፡፡
5. በሰስቱም መሰናዶ ትምህርት ቤቶች በተደረገው የክፍል ምልከታ አብዛኛዎቹ የአማርኛ መምህራን ተማሪዎችን ለማሳተፍ ያደረጉት ጥረት፣ በዕለቱ ያቀረቡት ትምህርት የቋንቋውን ክሂሎች ለማዳበር አስተዋጽኦ እንዳላቸው፣ የማስተማር ስልታቸው ሳቢና ማራኪ መሆኑ፣ የክፍሉን ስርአት ለመቆጣጠር የተጠቀሙበት ስልት፣ በአጠቃላይ የመማር ማስተማሩ ሂደት በጠንካራ ጎን የሚታይ ሲሆን የተማሪዎችም የክፍል ተሳትፎ ከፍተኛ እንደነበር ታይቷል፡፡ ስለዚህ የክፍል ምልከታው አዎንታዊ ውጤት አመልክቷል፡፡

ከነዚህ ውጤቶች በመነሳት የዚህ ጥናት የመነሻ ጥያቄዎችና አላማዎች ተገቢውን መልስ አግኝተዋል፡፡

## 5.3. አስተያየት

ከጥናቱ መረጃዎችና ከተገኙት ውጤቶች በመነሳት አጥኚው የሚከተሉትን አስተያየቶች ያቀርባል፡፡

1. በጥናቱ ውጤት መሰረት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ ነው፡፡ የማለፊያ ውጤታቸውም በጣም ከፍተኛ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ ቀደም ሲል ለመምህራን በቃለ መጠይቅ ለቀረበው ጥያቄ "የአማርኛ ቋንቋ ለኮሌጅ መግቢያ ፈተና ባለመካተቱ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ

ትምህርት ያላቸው አመለካከት ቀንሷል" ተብሎ በመምህራን የተሰጠው ምላሽ ትክክል እንዳልሆነ በጥናቱ ተረጋግጧል። እንዲያውም የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሌሎች ትምህርቶች ባልተናነሰ መልኩ ከፍተኛ ትኩረት እንደሚሰጡትና በአማርኛ ፈተና ውጤታቸውም በጣም ከፍተኛ ውጤት እንዳስመዘገቡ በአንደኛ ወሰነ-ትምህርት የክፍል ፈተና ውጤታቸው ላይ ታይቷል።

2. የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ርእሳነ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ከተጠኚ መምህራን ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ወቅት ለማወቅ ተችሏል። መምህራን እንደገለጹት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በቋንቋው ትምህርት ላይ አድሎ ሲያደርጉ ይታያሉ። ለምሳሌ በየትምህርት ቤቶቹ የክረምት ትምህርት፣ የማጠናከሪያ ትምህርት ፕሮግራም ሲዘጋጅ ሌሎች ትምህርቶች ሁሉ ሲሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ብቻ እንዳይሰጥ ይደረጋል በማለት መምህራን ቅሬታቸውን ገልፀዋል። በመሰረቱ በትምህርት አይነቶች መካከል ልዩነት ሊደረግ አይገባም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እንዲህ አይነት አድሎ ተደርጎ ከሆነ የሚመለከታቸው የትምህርት ኃላፊዎች የእርምት ርምጃ ሊወስዱ ይገባል። የመሰናዶ ትምህርት ቤት ርእሳነ-መምህራን ለአማርኛ ቋንቋ ዝቅተኛ አመለካከት ካላቸው በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊፈጥር እንደሚችል ይገመታል። ስለዚህ የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ-መምህራን እንደ ሌሎቹ የትምህርት አይነቶች ሁሉ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርትም ትኩረት ሊሰጡትና አስፈላጊውን እገዛ ሊያደርጉለት ይገባል። ይህ ሲሆን ደግሞ የመማር ማስተማሩ ሂደት የተቃና ይሆናል። ተማሪዎችም ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎት ከፍ ይላል፣ ውጤታቸውም ያማረ ይሆናል።

3. ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘው ምላሽ እንደሚያሳየው፣ ተማሪዎች ለመማሪያ መጽሐፉ አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል። አማካይ ነጥቡም 3.36 ነው። አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች ጠቃሚ መሆናቸውንና የልቦለድ ጽሁፎችም ቢጨመሩ የተሻለ እንደሚሆን ገልጸዋል።

4. ከመምህራን ጋር በተደረገው ቃለ-መጠይቅ /interview/ የተገኘው ውጤት መምህራን ለተማሪዎችና ለአማርኛ ቋንቋ አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ያሳያል። ነገር ግን ለመማሪያ መጽሐፉ፣ ለሙያ ማሻሻያ ስልጠና አሉታዊ አመለካከት እንዳላቸው ለመገንዘብ ተችሏል። ከግማሽ በላይ የሚሆኑት መምህራን የመማሪያ መጽሐፉ የተማሪዎችን ደረጃ የሚመጥን አይደለም የሚል መልስ ሰጥተዋል። ስለዚህ የትምህርት መሳሪያዎችን የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች፣ የመማሪያ መፃህፍት አዘጋጆች የመማሪያ መጽሐፉን ይዘት ሊመረምሩት ይገባል።

5. የሙያ ማሻሻያ ስልጠናን በተመለከተ አብዛኞዎቹ የአማርኛ መምህራን የሚሰጠው ስልጠና ሙያችንን ለማሻሻል የሚያግዝ አይደለም ብለዋል። ጥቂት መምህራን ደግሞ በመምህርነት ሙያ ከተመረቁ በኋላ ምንም አይነት ስልጠና አላልወሰዱ ተጠቁሟል። የሙያ ማሻሻያ ስልጠና የመምህራንን ዕውቀት ለማዳበር፣ አዳዲስ የመማር ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግ እጅግ ጠቃሚ መሆኑ አይካድም።

ስለዚህ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎች ሲዘጋጁ ዓላማቸው በውል ታውቆ፣ የመምህሩን ሙያ ለማሻሻል ታስቦባቸው ለአንድ ሳምንት ታይተው የሚጠፉ ሳይሆን ተከታታይነት ያለው ስልጠና ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የትምህርት ኃላፊዎች፣ ባሙያዎች ትኩረት ሊሰጡት ይገባል። ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ አብዛኛዎቹ መምህራን ለተማሪዎች የቤት ስራዎችን፣ መልመጃዎችን ይሰጣሉ። ነገር ግን የተማሪዎቹን የቤት ስራዎች እንደማያርሙ በቃለ-መጠይቅ ጊዜ ለማወቅ ተችሏል። ለዚህ አብይ ችግር መምህራን የተለያዩ ምክንያቶች እንዳሉ በቃ-መጠይቁ ወቅት ገልፀዋል። ይሁን እንጂ በርካታ ችግሮችም ቢኖሩ መምህራን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የተማሪዎችን የቤት ስራዎችን፣ መልመጃዎችን ማረም ይኖርባቸዋል። ይህ ካልሆነ ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ትኩረት አይሰጡትም፣ ለመማር ያላቸው ፍላጎትም ይቀንሳል።

# ዋቢ መጻህፍት


ባየ ይማም፡፡ (2000) **የአማርኛ ሰዋስው** (2ኛ እትም) አዲስ አበባ፤ እሌኒ ማ.ኃ.የ.ተ.ያማ.ማህበር፡፡

ታሪኬ ፋንታዬ፡፡ (1988) ‹‹ በአዲስ አበባ ከ/ሁ/ደ/ት/ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት፡፡ (Attitude) ›› አዲስ አበባ፣ በቋንቋዎች ተቋም ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)

ታየ ገ/ማሪያም፡፡ (1958) **የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ**፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡ (1968) **ትምህርት አቅጣጫና መመሪያ**፡፡ አዲስ አበባ፤ በስርአተ ትምህርት ቡድን፡፡

________፡፡(1985) "በብሔረሰብ ቋንቋዎች መደበኛ ትምህርት ስለመስጠቱ ከሽግግር መንግስቱ የተሰጠ ፖሊሲ፡፡" **ከትምህርት አለም በትምህርት ሚኒስቴር የሕዝ ግንኙነት አገልግሎት የሚዘጋጅ መጽሔት**፡፡ አዲስ አበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

________፡፡ (1986) ‹‹የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት አጠቃላይ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፡፡›› አዲስ አበባ፤ በሽግግር መንግስቱ የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ፡፡

አምሳሉ አክሊሉ፡፡ (1976) **አጭር የኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍ ታሪክ** አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡

እሸቱ ወንድሙ፡፡ (1997) ‹‹በኦሮምያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በውጤታቸው መካከል ያለው ግንኙነት፡፡›› አዲስ አበባ፣ በቋንቋዎች ተቋም ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)

ወንድወሰን በየነ፡፡ (1989) ‹‹የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀዲይኛ የሆነ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና የፈተና ውጤታቸው ዝምድና፡፡›› አዲስ አበባ፣ በቋንቋዎች ተቋም ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2001) **የምርምር መሠረታዊ አተገባበር** (2ኛ እትም) አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ዮናስ አድማሱ እና ሌሎች (1966) ‹‹አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ›› የተዘጋጀ። አርትስ ፋኩሊቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ክፍል፣ ቀ.ኃ.ሥ. ዩኒቨርስቲ።

ድንቄሳ ዱሬሳ። (1996) ‹‹በአዲስ አበባ መስተዳድር የአማርኛ ቋንቋ አፈፊትና በኦሮምኛ ብሔራዊ ክልል ኢ-አፈፊት የሆኑ የመሰናዶ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ንጽጽርና ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች።›› አዲስ አበባ፣ በቋንቋዎች ተቋም ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)

ዳንኤል ዘውዴና ሌሎች (1994) **የትምህርት ጥናትና ምርምር አተገባበር**። አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ።

ዐጋዩ አረጋይ። (1996) ‹‹ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሚኖራቸው አመለካከት ላይ ዝምድና ያላቸው ተላውጦች፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንግስታዊ ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች የተካሄደ ጥናት›› አዲስ አበባ፣ በቋንቋዎች ተቋም ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)

Aggarawal, J.C.(1989). **Essentials of Educational Psychology**. Reprinted, New Delhi: Vikas Publishing House Put Ltd.

Bender, M.L.(1976).«The Amharic Language.» In Bender et.al (ed)**Language in Ethiopia**. London: Ethiopia, Oxford: Oxford University Press.

Bugleski, R.B. (1971). The Psychology of Learning Applied to Teaching. New York: The Bobbs Merrill Company, Inc.

Celece-Murcia. (1991). **Teaching** English: as a second or Foreign Language, 2nd ed. Boston: Heinle and Hinle Publisher.

Cooper, R (1976). "The spread of Amharic" in Bender etal (1976 eds) **Language in Ethiopia.** Oxford University Press.

Cronbach. L.J. (1954). **Educational Psychology**. New York: Mc Graw-Hill Book Company, INC.

Dubin, Fraida and Elite Olshtain. (1986). Course Design: Developing Programs and Materials for Language Learning. Cambridge.

Gagne, R.M. (1976). The Conditions of Learning. New York: Holt, Rinehart and Winston.

Gardner, R.C. (1985). Social Psychology and Second Language Learning: The Role of Attitude and Motivation. London: Edward Arnoled, Ltd.

_____ (1968). "Attitude and Motivation: Their Role in second Language Acquisition." In TESOL Quarterly 2,141.50.

Girma Amare.(1963). "Government Education in Ethiopia." Ethiopian Observer. 6(4) PP. 335-342.

Girma Awgichew.(2009). The Origin of Amharic. Addis Ababa French Center for Ethiopian Studies.

Harmer, Jermy.(1990). The Practice of English Language Teaching. New York: Longman Group Ltd.

_______(1991). The Practice of English Language Teaching. New edition. London: Longman group UK Limited.

Krashen, Stephen D. (1988). Second Language Acquisition and Second Language Learning. New York: Printice Hall international UK) Ltd.

McNab,C. (1989). Language Policy and Language Practice: Implementation Dilemmas in Ethiopian Education. Stockholm: University of Stockholm.

Morgan, C. etal (1986). Introduction to Psychology.7th ed. New York: Mc Graw - Hill Book.

Muller, H.T.(1971). Attitudes in Basic French courses at the University of Kentucky. "The Modern Language Journals." Volss. No.s

Onoda, Lawernce.(1976). "Personality Characteristics and Attitudes Toward. Achievement Among Main High Achieving and Under Achieving Ja[panse-American sansei" Journal of educational Psychology. Vol. 68 No.2.

Oppenheim, A.N. (1984). Questionnaire Design and Attitude Measurement. London: Gower Publishing Company, Ltd.

Pankhurst, Richard H.P (1972). "Education in Ethiopia during the Italian Facist Occupation." The International Journal of Africa Historical Studies, 5(3) PP. 361-396.

Pikunas, Justin (1976). Human Development an Emergent Science. New York: McGraw-Hill Book Company.

Richards, Jack C. (1998). Principles Methods and Techniques of Teaching. New Delhi: Vikas Publishing House.

Rosenberg, M.J and C.Houland. (1980). "Cognitive, Affective, and Behavioral Components of Attitude." In M.J. Rosenberg "etal" (eds) Attitude Organizational and Change. (pp.48-64) west port Connecticut. Green wood. Press, pub.

Skinner, E.C. (1985). Educational Psychology. 4ed, Prentice-Hall, Inc. Englewood Cliffs N.J.

_______ (1989). Educational Psychology. 4ed, New Delhi: Prentice-Hall of India.

Smith, Alfred, N (1971). "The Importance of Attitude in Foreign Language Learning." The Modern Language Journals. Vol. 55,No 2.

Spolsky, B. (1969). "Attitudinal Aspects of Second Language Learning." Journal of Applied Linguistic: Language Learning vol. 19. No.3.

_______ (1998). Condition for Second Language Learning. New York: Oxford University.

Taddele Adamu. (1990). "Individual difference in Second Language Learning in Formal Context." Thesis submitted for the Degree of PhD Department of Linguistic Science: University of Reading.

Yule, Geoge "etal". (1985). "Investigating Aspects of the Language Learner's Confidence: An Application of the theory of signal Dictation." Journal of Applied Linguistic Language Learning. Vol.35. No.4.

# አበሪዎች

አባሪ 1

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## የቋንቋዎች ተቋም
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል
## የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር

## በመሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

### የመጠይቁ ዓላማ

የዚህ መጠይቅ ዓላማ በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሚገኙ የመሰናዶ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸውን አመለካከት ለማወቅና መረጃ ለመሰብሰብ ነው። ጥናቱ ግቡን ይመታ ዘንድ የእንተ/ቺ/ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ስለዚህ ጥያቄዎቹን በትክክል አንብበህ /ሽ/ና ተረድተህ/ሽ/ ትክክለኛ መልስ እንድትሰጠኝ /ጭኝ/ በትህትና እጠይቃሁ። ውድ ጊዜህ/ሽ/ን በመሰዋት ይህን መጠይቅ በመሙላትህ/ሽ/ በቅድሚያ አመሰግናለሁ።

<u>ማሳሰቢያ</u>

በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም።

<u>ክፍል አንድ</u>፦ በክፍት ቦታዎቹ ላይ ትክክለኛ መረጃ ሙላ/ይ/

1. ጾታ ________
2. ዕድሜ ______
3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ________
4. የትምህርት ቤቱ ስም ___________
5. ክፍል __________

<u>ክፍል ሁለት</u>፦ ለያንዳንዱ ጥያቄ በመመዘኛ መስፈርቱ ላይ በተቀመጡት መገለጫዎች አግባኝነት ተገቢ ነው የምትለው/ይ/ን መልስ የ"X" ምልክት በማስቀመጥ አመልክት /ቺ/

አባሪ 2

## ቃለ መጠይቅ (Interview)

## ለመምህራን ከቀረበው ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

አጥኚው በሶስት መሰናዶ ትምህርት ቤት ከሚገኙ የአስራ ሁለተኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን መካከል ከስድስቱ ጋር ቃለ መጠይቃዊ ውይይት አድርጓል። ቃለ መጠይቁ አስር ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን ጥያቄዎቹና መልሶቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? ለዚህ ጥያቄ ሁለት መልሶች ተመዝግበዋል።
   ሀ. የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በጎ አመለካከት አላቸው አራት መላሾች 66.7% ይህንን መልስ ሰጥተዋል።
   ለ. የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ አመለካከት የላቸውም። ምክንያቱም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮሌጅ መግቢያ ፈተና ላይ እንደማይካተት ስለሚያወቁ ለትምህርቱ በጎ አመለካከት የላቸውም። ሁለት መላሾች 33.3% ይህንን መልሰዋል።
   ስለዚህ 66.7% የሚሆኑ መላሾች ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በጎ አመለካከት እንዳላቸው ገልጸዋል። ይህንንም መረጃው ያመለክታል።
2. የመሰናዶ ተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ? ለዚህ ጥያቄ
   ሀ) አብዛኞቹ መምህራን ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ አምስት መላሾች 83.3% በማለት መልሰዋል።
   ለ) አንድ መላሽ እንደመምህሩ ሁኔታ ይወሰናል 16.7% በማለት መልሷል።
   ስለዚህ 83.3% መላሾች ተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ በማለት መልሰዋል።
3. ለተማሪዎች ልዩ ልዩ መልመጃዎች፣ የክፍል ስራዎችና የቤት ስራዎችን ሰጥተው ወዲያው አርመው ይመልሱላቸዋል? ለዚህ ጥያቄ ሶስት መልሶች ተመዝግበዋል።
   ሀ. አንድ መላሽ አዎ ወዲያው አርሜ እመልሳለሁ 16.7%

ለ. ሶስት ተጠኚ መምህራ በክፍል ውስጥ የተማሪዎቹ ቁጥር ብዙ በመሆኑ ወዲያው እርሜ ለመመለስ እቸገራለሁ 50.0% ይህንን መልስ ሰጥተዋል፡፡

ሐ.ሁለት መላሾች አልፎ አልፎ እርሜ እመልሳለሁ 33.3% በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ስለዚህ ከግማሽ በላይ 50% የሚሆኑ መምህራን የተማሪዎችን መልመጃዎችና የቤት ሥራዎችን እንደማያርሙ ከቃለ-መጠይቁ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

4. በሳምንት ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተሰጠው ክፍለ ጊዜ በቂ ነው? ለዚህ ጥያቄ ከአንድ መላሽ በስተቀር ሌሎቹ በሙሉ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተሰጠው ክፍለ ጊዜ በቂ አይደለም፡፡ በማለት መልሰዋል፡፡ ዝርዝር ሁኔታው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሀ. አንድ መላሽ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለኮሌጅ መግቢያ ፈተና ላይ ስለማይካተት የተመደበው ክፍል ጊዜ በቂ ነው፡፡ 16.7% የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

ለ. አምስቱ መላሾች የመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ይዘቶች ስላሉት ያንን ለመጨረስ ክፍለ ጊዜው በቂ አይደለም 83.3% የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

ስለዚህ 83.3% መላሾች ለአማርኛ ትምህርት የተመደበው ክፍለ ጊዜ በቂ አይደለም በማለት ገልጸዋል፡፡

5. የመሰናዶ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮሌጅ መግቢያ ፈተና ላይ ባለመካተቱ የአማርኛን ትምህርት ለመማር የነበራቸው ፍላጎት ቀንሷል?

ለዚህ ጥያቄ ስድስቱም መላሾች የአማርኛ ትምህርት በኮሌጅ መግቢያ ፈተና ላይ ባለመካተቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ለመማር የነበራቸው ፍላጎት ከዕለት ወደ ዕለት እየቀነሰ መምጣቱን ገልጸዋል፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ተጠኚ መምህራን በተማሪዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ 100% የሚል መልስ ሰጥተዋል ይህም በመረጃው ላይ ተረጋግጧል፡፡

6. በመሰናዶ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ መምህራን የአማርኛ ቋንቋን በማስተማራቸው ያጋጠማቸው ችግር አለ? ለዚህ ጥያቄ ሁለት መልሶች ተመዝግበዋል፡፡

ሀ. አዎን አማርኛን በማስተማሬ ችግር ገጥሞኛል፡፡ ሶስት መላሾች 50.0% ይህንን መልስ ሰጥተዋል፡፡ ምክንያቱን ሲገልፁ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ በኮሌጅ መግቢያ ፈተና ላይ እንደማይሰጥ ስለሚያውቁ ትምህርቱን በፍላጎት አይከታተሉም፡፡ በማለት አስተያየታቸውን አቅርበዋል፡፡

ለ. አማርኛን በማስተማሬ በግሌ ችግር አልገጠመኝም፡፡ ነገር ግን የተማሪዎች የመማር ፍላጎት መቀነሱ ያበሳጨኛል፡፡ ሶስት መላሾች 50% የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

ስለዚህ ከግማሽ በላይ 50% የሚሆኑ አማርኛን በማስተማራቸው የሚቸገሩ መሆኑን ሲገልፁ በግሌ ችግር አልገጠመኝም የሚሉትም ቢሆን ተማሪዎች የቤት ስራቸውን ሳይሰሩ እንደሚመጡ ሳይሸሽጉ ገልፀዋል፡፡

7. በመምህርነት ሙያ ስልጥነው ከተሰማሩ በኋላ የሙያ ማሻሻያ ኮርስ ወስደዋል?

ለዚህ ጥያቄ ሶስት መልሶች ተመዝግበዋል፡፡

ሀ. አዎ ስልጠና ወስጃለሁ ነገር ግን የአማርኛ ትምህርትን ለማሻሻል የሚያግዝ ስልጠና አይደለም፡፡ በኤች.አይ.ቪ ዙሪያ እና በመሰል ጉዳዮች ሴሚናሮች ይሰጣሉ፡፡ ሶስት መላሾች 50% ይህን መልሰዋል፡፡

ለ. በመምህርነት ተመርቄ ስራ ላይ ከተሰማራሁ በኋላ ምንም አይነት ሙያ ማሻሻያ ኮርስ አልወሰድኩም ሁለት መላሾች 33.3% ይህንን መልሰዋል፡፡

ሐ. አዎ ከሙያዬ ጋር በተያያዘ ብዙ ስልጠና ወስጃለሁ፡፡ አንድ መላሽ 16.7% ይህንን መልስ መልሷል፡፡

ስለዚህ 50.0% የሚሆኑት የሙያ ማሻሻያ ኮርስ ወስደናል ነገር ግን ስልጠናው የአማርኛ ቋንቋ ለማስተማር የሚያግዝ አይደለም ሲሉ 33.3%ቱ ደግሞ ምንም አይነት የሙያ ማሻሻያ ኮርስ አልወሰድንም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ሀሳብ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናው ላይ አንድ ችግር መኖሩን እንገነዘባለን፡፡

8. የአማርኛ ቋንቋን በተመለከተ ያለዎትን አስተያየት ቢገልፁልኝ?

ለዚህ ጥያቄ ሁሉም መላሾች ተመሳሳይ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ የራሱ ፊደል ያለው መሆኑ፣ ለጋራ መግባቢያነት የሚያገለግል መሆኑ፣ የስነ-ጽሑፍ ቅርስ ያለው መሆኑን በመግጽ ለቋንቋው ጥሩ አመለካከት እንዳላቸው ሰድስቱም መላሾች 100% ገልፀዋል፡፡

ስለዚህ ሁሉም መላሾች 100% ለቋንቋው ጥሩ አመለካከት ካላቸው ተማሪዎቻቸውን በጥሩ ስሜትና ፍላጎት የሚያስተምሩ መሆኑን እንገነዘባለን።

9. አሁን በስራ ላይ ያለው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ከተማሪዎቹ ችሎታ አንፃር ብቁ ነው ይላሉ? ለዚህ ጥያቄ ሶስት መልሶች ተመዝግበዋል።

    ሀ. ሶስት መላሾች አሁን በስራ ላይ ያለው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ በባለሙያ የተዘጋጀ አይደለም፤ መካተት ያበትን ይዘት አላካተተም። ሶስት መላሾች 50.0% ይህንን መልስ ሰጥተዋል።

    ለ. የመማሪያ መጽሐፉ ይዘት ለተማሪዎቹ ደረጃ የሚመጥን ነው፤ አራቱን ክሂሎች ለማስተማር የሚያግዝ ነው። ሁለት መላሾች 33.3% ይህንን መልስ ሰጥተዋል።

    ሐ. የመማሪያ መጽሐፉ ለተማሪዎች የሚመጥን ቢሆንም አንዳንዱ ይዘት ግን ከተማሪዎቹ አቅምና ደረጃ በላይ ነው። አንድ መላሽ 16.7% ይህንን መልስ መልሷል።

ስለዚህ ከግማሽ በላይ መላሾች 50.0% የመማሪያ መጽሐፉ የተማሪዎችን ፍላጎትና ደረጃ የሚመጥን አይደለም በማለት መልስ ሰጥተዋል። እዚህ ላይ ተማሪዎች በተላውጦ ሶስት ስር መማሪያ መጽሐፉን በተመለከተ የሰጡት መልስ መምህራን ለመማሪያ መጽሐፉ ከሰጡት መልስ አንፃር ሲታይ በተቃራኒ ሆኖ ተገኝቷል። የዚህ ምክንያቱ ምናልባት ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፉን የመገምገም ብቃት ማነስ ወይም የቀረበላቸውን መጠይቅ ሲሞሉ ትኩረት ሰጥተው አለመሙላታቸው ሊሆን ይችላል ተብሎ ይገመታል።

10. የመሰናዶ ተማሪዎች በአማርኛ ፈተና ውጤታቸው ምን ይመስላል? ለዚህ ጥያቄ ሁለት መልሶች ተመዝግበዋል።

    ሀ. የመሰናዶ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የፈተና ውጤታቸው በአብዛኛው ጥሩ ነው። በአማርኛ ፈተና ማለፊያ ማርክ ያመጣሉ። አምስት መላሾች 83.3% በማለት መልስ ሰጥተዋል።

    ለ. የአብዛኛው ተማሪ ውጤት ጥሩ አይደለም። ምክንያቱም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮሌጅ መግቢያ ፈተና ውስጥ ስለማይካተት ተማሪዎች

የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት እያጠኑትም፤ ካላጠኑ ደግሞ ጥሩ ውጤት እያመጡም እንድ መላሽ 16.7% በማት መልሷል።

ስለዚህ 83.3% የሚሆኑ መላሾች የመሰናዶ ተማሪዎች በአማርኛ ጥሩ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ አረጋግጠዋል። በቃለ መጠይቅ ጊዜ የቀረበው መረጃም ይህንኑ ያመለክታል።

11. ህብረተሰቡና ወላጆች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

ለዚህ ጥያቄ ሁለት መልሶች ተመዝግበዋል።

ሀ. ህብረተሰቡና ወላጆች ለአማርኛ ቋንቋ ጥሩ አመለካከት አላቸው። ወላጆች ልጆቻቸውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን እንዲማሩ ያበረታታሉ። ሁለት መላሾች 33.3% ይህንን መልስ ሰጥተዋል። ይሁን እንጂ ጥቂት የህብረተሰብ ክፍሎች ለቋንቋው ጥላቻ እንዳላቸው መምህራን ገልፀዋል።

ለ. አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍልና ወላጆች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝቅተኛ አመለካከት አላቸው። ምክንያቱን ሲገልጹ ወላጆች ከአማርኛ ይልቅ ልጆቻቸው በእንግሊዝኛ ቢማሩ ይመርጣሉ፤ ከአማርኛ ይልቅ ለውጭ ቋንቋ ክብርና አድናቆት አላቸው። አራት መላሾች 66.7% በማለት መልሰዋል።

ስለዚህ 66.7% የሚሆኑ መላሾች አብዛኛው የህብረተሰቡ ክፍልና ወላጆች ለአማርኛ ቋንቋ ዝቅተኛ አመለካከት ሲኖራቸው፤ ከአማርኛ ቋንቋ ይልቅ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ትልቅ ክብር እንዳላቸው ገልጸዋል። ወላጆችና ህብረተሰቡ ለአማርኛ ዝቅተኛ አመለካከት ካላቸው ደግሞ ልጆቻችውን አማርኛ ቋንቋን እንዲማሩ እንደማያበረታቷቸው መገመት አያስቸግርም።

12. በመሰናዶ ትምህርት ቤት የሚገኙ ርእሳነ-መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

ለዚህ ጥያቄ ስድስቱም መላሾች ተመሳሳይ መልስ ሰጥተዋል። የመሰናዶ ትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ለአማርኛ ቋንቋ ዝቅተኛ አመለካከት አላቸው። በአማርኛ ቋንቋ ላይም አድሎ ያደርጋሉ የማጠናከሪያ ትምህርት፤ የክረምት ትምህርት የመሳሰሉት ሲሰጥ ከሌሎች ትምህርቶች ተለይቶ አማርኛ እንዳይሰጥ ይደረጋል። ለሌሎች ትምህርቶች ድጋፍ ሲያደርጉ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምንም ድጋፍ አያደርጉለትም።

የአማርኛን ክፍለ ጊዜ ቀንሰው ለሌላ ትምህርት ይጨምራሉ በአጠቃላይ ለአማርኛ በጣም ዝቅተኛ አመለካከት አላቸው። ስድስት መላሾች 100% በማለት መልሰዋል።

ስለዚህ 100% መላሾች በመሰናዶ ትምህርት ቤት የሚገኙ ርእሳነ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ለአማርኛ ቋንቋ ዝቅተኛ አመለካከት እንዳላቸው አረጋግጠዋል።

በአጠቃላይ መምህራን በቃለ መጠይቅ ጊዜ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጧቸው መልሶች እንደሚከተሉ ተጠቃለው ቀርበዋል።

- ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ጥሩ አመለካከት ያላቸው መሆኑ፣
- አብዛኛዎቹ መምህራን የተማሪዎችን ደብተር እንደማያርሙ፣
- ለአማርኛ የተመደበው ክፍለ ጊዜ በቂ አለመሆኑ፣
- የሙያ ማሻሻያ ስልጠናው ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር ምንም ዝምድና የሌለው መሆኑ፣ እንዲያውም አንዳንዶቹ ምንም የሙያ ስልጠና ያልወሰዱ መሆኑን፣
- የመማሪያ መጽሐፉ ለተማሪዎች በሚመጥን ደረጃ አለመዘጋጀቱ፣
- በአማርኛ ፈተና የተማሪዎች ውጤት ጥሩ መሆኑ፣
- ወላጆችና ህብረተሰቡ ለአማርኛ ቋንቋ ጥሩ አመለካከት የሌላቸው መሆኑ፣
- የመሰናዶ ርዕሳነ-መምህራን ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ጥሩ አመለካከት የሌላቸው መሆኑ ተገልጿል።

## የክፍል ምልከታን በተመለከተ

ሀ. ከጠቅላላው ተጠኚ መምህራን መካከል በ6ቱ ለሁለት ለሁለት ጊዜያት ያህል ምልከታ ተካሄዷል። የተገኘው ውጤትም እንደሚከተለው ቀርቧል።

- ለአንደኛው የምልከታ ነጥብ ምልከታ ተደርጎ ከስድስቱ ተጠኚ መምህራን አምስቱ  አሳታፊ የማስተር ዘዴ ተጠቅመው ትምህርቱን ሳቢና ማራኪ አድርገው ማቅረባቸው ተረጋግጧል። ጥሩ የማስተማር ሂደት ደግሞ

ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርታቸው ላይ በጎ አመለካከት እንዲፈጥሩ ይረዳቸዋል፡፡

- በተራ ቁጥር 2፣3፣8 ያሉ ምልከታዎች ከግማሽ በላይ ያህሉ አራቱ መምህራን ሁሉንም ተማሪዎች በማሳተፍ የዕለቱን ትምህርት አከናውነዋል፡፡
- ለ4ኛው ጥያቄ ከምልከታ የተገኘውን ውጤት ስንመለከት አብዛኛዎቹ መምህራን አራቱ በዕለቱ ይዘውት የቀረቡት የትምህርት ይዘት የቋንቋውን ትምህርት ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው በምልከታው ወቅት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- ለጥያቄ 5 ከምልከታው የተገኘውን ውጤት ስንመለከት ሁሉም ተጠኚ መምህራን ስድስቱ በቋንቋው ትምህርት ላይ ያላቸው ዕውቀትና የማስተማር ብቃት ከፍተኛ መሆኑ በምልከታው ወቅት ተረጋግጧል፡፡ ይህ ውጤት ተላውጦ ሁለት ስር ጥያቄ 2.5 ላይ ከቀረበው ሀሳብ ጋር የተጣጣመ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- ለጥያቄ 6፣9 ምልከታዎች የተገኘውን ውጤት ስንመለከት አብዛኞቹ ተጠኚ መምህራን አምስቱ ለመምህርነት ሙያ ከፍተኛ ፍቅር ያላቸውና ለተማሪዎቻቸው ክብር ያላቸው፣ እንዲሁም ተማሪዎቻቸውን ለመርዳት ከፍ ያለ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን በምልከታው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ መምህራን ለተማዎቻቸው ፍቅርና አክብሮት ካላቸው ተማሪዎቹም ትምህርቱን ለመከታተል ፍቃደኞች ይሆናሉ፡፡ ይህም ደግሞ ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት በጎ አመለካከት እንዲኖራቸው አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡
- ለጥያቄ 7 ከምልከታ የተገኘውን ውጤት ስንመለከት አብዛኛዎቹ መምህራን አራቱ የክፍሉን ስርአት የሚቆጣጠሩ ሲሆን ጥቂት መምህራን ሁለቱ ግን የክፍሉን ስርአት ለመቆጣጠር የሚቸገሩ መሆኑን ከምልከታው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ መምህራን የክፍሉን ስርአት ቢቆጣጠሩም ጥቂቶቹ ደግሞ መቆጣጠር ካልቻሉ በመማር ማስተማሩ ላይ ችግር መኖሩን ይጠቁማል፡፡

በተራ ቁጥር 8 ከምልከታው የተገኘው ውጤት ከስድስቱ መምህራን አራቱ አሳታፊ የማስተማር ስልት የሚከተሉ መሆኑን በምልከታው ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል።

በተራ ቁጥር 9 ከምልከታው የተገኘው ውጤት ከስድስቱ አምስቱ ለተማሪዎቻቸው አክብሮት አላቸው። ተማሪዎቹን ለመርዳት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው በምልከታው ጊዜ ለማረጋገጥ ተችሏል።

ለ10ኛው ጥያቄ ከምልከታው የተገኘውን ውጤት ስንመለከት አብዛኛዎቹ ተጠኚ መምህራን አምስቱ በዕለቱ የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ የተጠቀሙበት መሆኑን በምልከታው ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል።

ከዚህ በላይ በዝርዝር ለማቅረብ እንደተሞከረው አብዛኛዎቹ ምልከታዎች አዎንታዊ ሲሆኑ አንዱ ጥያቄ 3 ግን ግማሽ አዎንታዊ ግማሽ አሉታዊ ባህሪ ታይቶበታል። በአጠቃላይ ከምልከታው የተገኘው ውጤት ጥሩ ነው ማለት ይቻላል።

አባሪ 3

## የመምህራ ቃለ መጠይቅ የተጠቃለሉ መልሶች

| ጥያቄ | እምንታዊ | | ለመወሰን እቸገራለሁ | | አሉታዊ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5/4 | % | 3 | % | 2/1 | % |
| 1 | 4 | 66.7 | - | - | 2 | 33.3 |
| 2 | 5 | 83.3 | - | - | 1 | 16.7 |
| 3 | 1 | 16.7 | 2 | 33.3 | 3 | 50.0 |
| 4 | 1 | 16.7 | - | - | 5 | 83.3 |
| 5 | 6 | 100 | - | - | - | - |
| 6 | 3 | 50 | - | - | 3 | 50.0 |
| 7 | 1 | 16.7 | 3 | 50.0 | 2 | 33.3 |
| 8 | 6 | 100 | - | - | - | - |
| 9 | 2 | 33.3 | 1 | 16.7 | 3 | 50 |
| 10 | 5 | 83.3 | - | - | 1 | 16.7 |
| 11 | 2 | 33.3 | - | - | 4 | 66.7 |
| 12 | - | - | - | - | 6 | 100 |

አባሪ 4 ሀ

በመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የተደረገ ዝርዝር የክፍል ምልከታ ውጤቶችን ማጠቃለያ

አብይ ነጥቦች።

ቀን ______________________

ትምህርት ቤት ______________________

የክፍለ ጊዜ ብዛት ______________

አብይ ነጥቦች

## የመምህሩ /ዋ/ የክፍልና የትምህርት አያያዝ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ታይቷል | አልታየም |
|---|---|---|---|
| 1 | አሳታፊ የማስተማር ዘዴ ተጠቅመው ትምህርቱን ሳቢና ማራኪ የማድረግ ብቃታቸው። | | |
| 2 | በክፍል ውስጥ ተማሪችዎን ለማነቃቃት የሚያደርጉት ጥረት | | |
| 3 | ትምህርቱ በሚካሄድበት ወቅት ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ የማድረግ ችሎታ | | |
| 4 | መምህሩ በዕለቱ ይዘውት የቀረቡት የትምህርት ይዘት የቋንቋውን ትምህርት ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ | | |
| 5 | በቋንቋው ትምህርት ላይ ያላቸው ዕውቀትና የማስተማር ብቃት | | |
| 6 | ለመምህርነት ሙያ ያላቸው ፍቅርና ስብዕናቸው | | |
| 7 | የክፍሉን ስርአት የመቆጣጠር ስልትና ተማሪዎቹን የመከታተል ሁኔታ | | |
| 8 | አሳታፊ (Student centre) የማስተማር ዘዴ መከተላቸው። | | |
| 9 | ለተማሪዎቻቸው ያላቸው ክብርና ተማሪዎቹን ለመርዳት ያላቸው ፍላጎት | | |
| 10 | ለዕለቱ የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ የመጠቀም ችሎታ | | |

አባሪ 4ለ

## የመምህራን የማስተማር ሂደት ከምልከታ የተገኘ ምላሽ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ምልከታ ነጥቦች | ታይቷል ብዛት | አልታየም ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | አሳታፊ የማስተማር ዘዴ ተጠቅመው ትምህርቱን ሳቢና ማራኪ የማድረግ ብቃታቸው | 5 | 1 |
| 2 | በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን ለማነቃቃት የሚያደርጉት ጥረት | 4 | 2 |
| 3 | ትምህርቱ በሚካሄድት ወቅት ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ የማድረግ ችሎታ | 3 | 3 |
| 4 | መምህሩ በዕለቱ ይዘውት የቀረቡት የትምህርት ይዘት የቋንቋውን ትምህርት ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ | 4 | 2 |
| 5 | በቋንቋው ትምህርት ላይ ያላቸው ዕውቀትና የማስተማር ብቃት | 6 | 0 |
| 6 | ለመምህርነት ሙያ ያላቸው ፍቅርና ስብዕናቸው | 5 | 1 |
| 7 | የክፍሉን ስርአት የመቆጣጠር ስልትና ማሪዎቹን የመከታተል ሁኔታ | 4 | 2 |
| 8 | አሳታፊ የማስተማር ዘዴ መከተላቸው | 4 | 2 |
| 9 | ለተማሪዎቻቸው ያላቸው ክብርና ተማሪዎቹን ለመርዳት ያላቸው ፍላጎት | 5 | 1 |
| 10 | ለእለቱ የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ የመጠቀም ችሎታ | 5 | 1 |

አባሪ 5ሀ

## የተማሪዎች አመለካከትና የፈተና ውጤታቸውን የሚያሳይ ስታስቲካዊ መረጃ

Paired sample statistics

| | Mean | N | Std Devotion | Std. error Mean |
|---|---|---|---|---|
| Pair 1 Aptitude score | 121.88 | 120 | 11.923 | 1.088 |
| Test score | 71.68 | 120 | 9.486 | 0.866 |

Paired sample correlation

| | N | Correlation | Sig |
|---|---|---|---|
| Pair 1 Aptitude and Test Score | 120 | 0.186 | 0.042 |

Paired sample tests

| | Paired Difference | | | | | t | df | Sig 12 taild |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean | 95% confidence interval of the difference Lower | Upper | | | |
| Pair Aptitude score 1. Test score | 50.208 | 13.789 | 1.259 | 47.716 | 52.701 | 39.888 | 119 | 0.00 |

አባሪ 5ሀ

# የተማሪዎች የአመለካከትና የፈተና ውጤት

| | Name | Sex | Aptitude | Test |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Aklilu Derese | Male | 131 | 74 |
| 2 | Bilen Mulegeta | Female | 133 | 80 |
| 3 | Daneil Haregewon | Male | 130 | 70 |
| 4 | Genet Teressa | Female | 128 | 68 |
| 5 | Haymanot Mekuriaw | Female | 115 | 65 |
| 6 | Lidya Enkubahry | Female | 109 | 80 |
| 7 | Mesay Abenet | Male | 117 | 66 |
| 8 | Sebsebie Abel | Male | 133 | 59 |
| 9 | Tihut Tesfaye | Female | 115 | 75 |
| 10 | Tizazu Fekade | Male | 130 | 84 |
| 11 | Tewodros Gezahan | Male | 112 | 75 |
| 12 | Senait Abebe | Female | 137 | 81 |
| 13 | Aynalem Tegaw | Female | 102 | 67 |
| 14 | Daniel Shimelse | Male | 111 | 69 |
| 15 | Hana Birhanu | Female | 131 | 75 |
| 16 | Henok Addisu | Male | 117 | 77 |
| 17 | Muluken Taddese | Male | 136 | 77 |
| 18 | Medhanit Arega | Female | 123 | 73 |
| 19 | Helen Asfaw | Female | 125 | 82 |
| 20 | Paulos Zemariam | Male | 104 | 78 |
| 21 | Ermias Mengistu | Male | 106 | 60 |
| 22 | Debora G/Dingle | Female | 137 | 83 |
| 23 | Tseganesh Duguma | Female | 103 | 82 |
| 24 | Kidist Eshetu | Female | 102 | 72 |
| 25 | Nahom Tewodros | Male | 131 | 85 |
| 26 | Wegenenesh Mengesh | Female | 134 | 82 |
| 27 | Yordanos Moges | Female | 133 | 74 |
| 28 | Henok Molla | Male | 115 | 63 |
| 29 | Meskerem Teshom | Female | 110 | 82 |
| 30 | Selamawit Lemessa | Female | 111 | 78 |
| 31 | Solomon Getachew | Male | 132 | 85 |
| 32 | Yordanos Kebede | Female | 125 | 78 |
| 33 | Tamene Mesfin | Male | 106 | 73 |
| 34 | Tehitna Alemu | Female | 141 | 78 |
| 35 | Naol Bekele | Male | 135 | 85 |
| 36 | Haftom Abadi | Male | 110 | 78 |
| 37 | Zemzem Keder | Female | 147 | 82 |
| 38 | Ermias Tesfaye | Male | 132 | 84 |
| 39 | Daniel Zewdie | Male | 145 | 88 |
| 40 | Fischa Shimeles | Male | 125 | 52 |
| 41 | Tigist Mekuria | Female | 111 | 82 |
| 42 | Tigist Tilahun | Female | 120 | 78 |
| 43 | Abel Solomon | Male | 125 | 69 |
| 44 | Yosef Desalegn | Male | 135 | 84 |
| 45 | Tirualem Gedamu | Female | 137 | 73 |
| 46 | Zewdu Tinker | Male | 130 | 85 |
| 47 | Alwiya Redi | Female | 103 | 89 |
| 48 | Fasil Samuel | Male | 105 | 72 |
| 49 | Abaynesh Mandefro | Female | 137 | 78 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 50 | Nuredin Redwan | Male | 108 | 66 |
| 51 | Samrawit Kiros | Female | 114 | 68 |
| 52 | Surafel Aklilu | Male | 135 | 80 |
| 53 | Shimeles Taddese | Male | 123 | 85 |
| 54 | Daniel Berecha | Male | 139 | 85 |
| 55 | Mahlet Abebe | Female | 118 | 82 |
| 56 | Endale Abera | Male | 132 | 69 |
| 57 | Mahlet Tesfaye | Female | 113 | 65 |
| 58 | Samuel Abebayehu | Male | 103 | 64 |
| 59 | Saba Tamerat | Female | 135 | 72 |
| 60 | Abera Salah | Male | 131 | 55 |
| 61 | Bemnet Ayalew | Male | 134 | 63 |
| 62 | Degnch W/Senbet | Female | 131 | 66 |
| 63 | Frehiwot Zenebe | Female | 128 | 72 |
| 64 | Habtamu Alemayehu | Male | 117 | 78 |
| 65 | Hanna Asfaw | Female | 107 | 74 |
| 66 | Beza Menberu | Female | 115 | 52 |
| 67 | Kalkidan Babesha | Female | 131 | 84 |
| 68 | Melaku H/Selasie | Male | 101 | 60 |
| 69 | Meron Fekadu | Female | 130 | 73 |
| 70 | Tigist Teshome | Female | 112 | 72 |
| 71 | Wasehun Temare | Male | 132 | 74 |
| 72 | Washun Hailu | Male | 102 | 81 |
| 73 | Tsion Mulugeta | Female | 113 | 83 |
| 74 | Elsa Abrham | Female | 136 | 88 |
| 75 | Ephrem Tesfaye | Male | 119 | 60 |
| 76 | Redeat Abebe | Female | 131 | 75 |
| 77 | Samuel G/Selassie | Male | 125 | 59 |
| 78 | Selam Getachew | Female | 123 | 64 |
| 79 | Bayelegn Taye | Male | 107 | 66 |
| 80 | Hana Girma | Female | 106 | 63 |
| 81 | Rodas Mamo | Female | 108 | 75 |
| 82 | Sadik Nuru | Male | 133 | 54 |
| 83 | Selamawit G/Eggizabe | Female | 113 | 78 |
| 84 | Seyefe Birku | Male | 101 | 54 |
| 85 | Addis Asegahegn | Male | 134 | 69 |
| 86 | Aster Getachew | Female | 133 | 70 |
| 87 | Demesew Temesgen | Male | 110 | 60 |
| 88 | Emebet Getachew | Female | 117 | 75 |
| 89 | Fasil Atnafu | Male | 111 | 52 |
| 90 | FevenAddisu | Female | 109 | 73 |
| 91 | Tigest Mekonnen | Female | 114 | 60 |
| 92 | Maseresha Tesfaye | Female | 134 | 69 |
| 93 | Mehari Getasew | Male | 135 | 70 |
| 94 | Mekedes Dagim | Female | 131 | 59 |
| 95 | Samir Menu | Male | 135 | 65 |
| 96 | Tedenya Elias | Female | 109 | 73 |
| 97 | Hana Abera | Female | 114 | 74 |
| 98 | Hayat Mohammed | Female | 135 | 76 |
| 99 | Meskerem Alemu | Female | 113 | 57 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 100 | Mesfin Andargu | Male | 136 | 55 |
| 101 | Betelehem H/Mariam | Female | 117 | 68 |
| 102 | G/Meskel Mulugeta | Male | 131 | 62 |
| 103 | Hewan Kidane | Female | 114 | 63 |
| 104 | Netsanet Tsegaye | Female | 103 | 74 |
| 105 | Remza Hayder | Female | 136 | 52 |
| 106 | Saba Workagegn | Female | 113 | 55 |
| 107 | Tigist Worku | Female | 131 | 72 |
| 108 | Hiwot Taye | Female | 116 | 67 |
| 109 | Dawit Desalegn | Male | 133 | 56 |
| 110 | Mareshet Abera | Female | 119 | 81 |
| 111 | Zeyneba Hassen | Female | 109 | 66 |
| 112 | Tsion Hailu | Female | 115 | 73 |
| 113 | Addis Taddese | Male | 128 | 70 |
| 114 | Belete Hailu | Male | 130 | 78 |
| 115 | Fasil Awoke | Male | 133 | 74 |
| 116 | Hana Endale | Female | 131 | 85 |
| 117 | Yared Assefaw | Male | 117 | 76 |
| 118 | Kasahun Ketema | Male | 131 | 62 |
| 119 | Ephrem Kefetew | Male | 106 | 66 |
| 120 | Yosef Tena | Male | 115 | 56 |

**Paired Samples Statistics**

| | | Mean | N | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| Pair 1 | Aptitude Score | 121.88 | 120 | 11.923 | 1.088 |
| | Test Score | 71.68 | 120 | 9.486 | .866 |

**Paired Samples Correlations**

| | | N | Correlation | Sig. |
|---|---|---|---|---|
| Pair 1 | Aptitude Score & Test Score | 120 | .186 | .042 |

**Paired Samples Test**

| | | Paired Differences | | | | | t | df | Sig. (2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean | 95% Confidence Interval of the Difference | | | | |
| | | | | | Lower | Upper | | | |
| Pair 1 | Aptitude Score - Test Score | 50.208 | 13.789 | 1.259 | 47.716 | 52.701 | 39.888 | 119 | .000 |

ሰገሬ "5ሰ"

Medhanialem Students Score

**Paired Samples Statistics**

| | | Mean | N | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| Pair 1 | Aptitude Score | 121.33 | 40 | 11.136 | 1.761 |
| | Test Score | 66.85 | 40 | 8.798 | 1.391 |

**Paired Samples Correlations**

| | | N | Correlation | Sig. |
|---|---|---|---|---|
| Pair 1 | Aptitude Score & Test Score | 40 | -.006 | .971 |

**Paired Samples Test**

| | | Paired Differences | | | | | t | df | Sig. (2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 95% Confidence Interval of the Difference | | | | |
| | | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean | Lower | Upper | | | |
| Pair 1 | Aptitude Score - Test Score | 54.475 | 14.234 | 2.251 | 49.923 | 59.027 | 24.204 | 39 | .000 |

Yekatit Student Result

**Paired Samples Statistics**

| | | Mean | N | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| Pair 1 | Aptitude Score | 122.98 | 40 | 12.837 | 2.030 |
| | Test Score | 75.48 | 40 | 8.162 | 1.290 |

**Paired Samples Correlations**

| | | N | Correlation | Sig. |
|---|---|---|---|---|
| Pair 1 | Aptitude Score & Test Score | 40 | .341 | .031 |

**Paired Samples Test**

| | Paired Differences | | | | | t | df | Sig. (2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean | 95% Confidence Interval of the Difference | | | | |
| | | | | Lower | Upper | | | |
| Pair 1 Aptitude Score - Test Score | 47.500 | 12.645 | 1.999 | 43.456 | 51.544 | 23.758 | 39 | .000 |

## ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስምና ፊርማዬን ያስቀመጥኩኝ የድህረ ምረቃ ተማሪ፣ ይህ ጥናት የራሴ ስራና በጥናቱ ውስጥ የተቀምኩባቸውን ፅሁፎችና ምንጮች በትክክል የጠቀስኩ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

1. ሥም አበበ ከበደ
2. ፊርማ
3. አድራሻ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት
በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ለማስተማር

ሰኔ 2003 ዓ.ም